# መንደርደርያ

በገዛ አገራቸውና በገዛ ምድራቸው ላይ እየኖሩ፣ በየዕለቱ የውርደት አተላ የሚጋቱ ወገኖች ቍጥር፣ እየጨመረ መጥቷል። ጥንታውያን ጀግኖች አባቶች፣ ይህን መሳይ ብሔራዊ ውርደትን በመጥላት፣ ለሕዝባቸው ክብርና ለሃገራቸው ነፃነት ሲሉ፣ ከባዕዳን ወራሪዎች ጋር እየመከቱ በየጐራው ሲታገሉ ኖረው ነበር። ዝርዝሮቹን ጐራዎች መጥቀስ ባያስፈልግ እንኳ፣ አድዋንና መተማን ማንሳቱ ይበቃል። የነዚያ ጀግኖች አባቶችን አፅም፣ ገና ያስከበሩት መሬት በልቶ ሳይጨርሰው፣ በአንድ ትውልድ ዕድሜ ውስጥ፣ የሞቱላት ሀገር የባዕዳን ወራሪዎች መፈንጫ፣ የልጆቿ ክብር መረገጫ፣ ለመሆን በቃች።

እነሱ አስቀድሞ ታይቷቸው፣ " የጠሉት ይወርሳል፣ የፈሩት ይደርሳል " ብለው ይተርቱ እንደነበር ሁሉ፣ ዛሬ እኛ ትንቢታዊ ንባበ ቃላቸውን፣ በድርጊት አየን። የፈሩት መድረሱ ቢያስደንቀንም፣ የጠሉት መውረሱ ደግሞ ይበልጥ አስገርሞ አስጨንቀን። ታዲያ ይህን ትንቢት የነበረ የአባቶች ንግርት፣ ለመጭ ትውልድ መዝግቦ ማቈየቱ፣ ፋይዳ ይኖረው ይሆን? አለያስ፣ በትግል ያለውን ተጋዳይ፣ ብሔራዊ ውርደት ያሳደረበትን ቆራጥነት፣ ይበልጥ እንዲቀጥል መራራ ሐሞቱን ሠፍነግ አድርጐ በትግሉ እንዲጠነክር አይረዳው ይሆን? አለያስ፣ በንቃት ማነስ ምክንያት የደበረውን ህዝባዊ ወገን፣ የሀገሩን ክብር ለማስደፈርና ህዝባዊ ልዕልናን ለማፍራት፣ ተጻፍሮና ተባብሮ እንዲነሣ ለመገፋፋት፣ ይህ ዐይነቱ የግፍና የውርደት ታሪክ የርዳታ ድርሻ አይኖረው ይሆንን? እነዚህን ተደራራቢ መጠይቆች፣ መጪው ታሪክ ይመልሳቸዋል።

# የተጣሰ አጥር!

( የመናገሻዬቱ ከተማ ጊዜያዊ ሕይወት ብልጭታ)

" ..... ማርጀትዋ በጃት እንጅ አሮጌት እናቴንም አይለቃትም ነበር ። ትናንትና በዓታ በዓል ለማክበር ስንሔድ፣ ፊት በር ላይ ጂፑን አቁሞ ሴቱን ሁሉ ሲመትር፣ በናቴ የበስ ተጀርባ ሽንጥ ላይ ዐይኑን ጥሎ ነበር ። እኔን ይበልጥ የሚገ ርመኝ በኔ ቤተሰብ ላይ ብቻ ይህን ያህል መቅነዝነዙ ነው ። አንደኛውን ምክንያት እንኳ አውቀዋለሁ ። የኔ ቤተ-ሰብ የው በት መደብር፣ የቆንጆዎች አድባር መሆኑ ነው ። እንዳው ከምን ዐይነቱ ዘመን ላይ ደረስን? ምን ዐይነት የአውሬዎች ጊዜ ላይ ጣለን? ..... " አሉ እንባ እየተናነቃቸው ። በሣሎናቸው እንደ ሀዘንተኛ ጋቢያቸውን ተጀቡነው በመቀመጥ ከእ ማቻቸው ጋር የሚወያዩት፣ ስለተጠለፈባቸው ልጅ ጉዳይ ነው ። ከበስተፊታቸው ካለች ክብ ጠረጴዛ ላይ ሞኝ አንግሥ በጠርሙስ ቀርቧል ። እያንዳንዱን ዐረፍተ ሐሳብ በጨረሱ ቍጥር አንንዳንድ መለኪያ ይጨልጣሉ ። ከበስተጀርባቸውም የሚንጠለጠልበት ጉጠት መሳይ ምስማርም በግድግዳው ላይ ይታያል ።

" ወይ ነዶ! " አሉ ድንገት ከተቀመጡበት ተነስተው በሣሎኑ ውስጥ እየተንጐራደዱ ። " ወይ ነዶ! መንጥር ባትወ ረስብኝ ኖሮ፣ ዘንድሮ ይለይልኝ ነበር! እንዲህ የባዕድ ምናም ንቴ መጫዎቻ አሻንጉሊት ከመሆን ታድነኝ ነበር! ወይ ነዶ! " አሉ እጃቸውን ዘርግተው፣ ጠመንጃቸው ይሰቀልበት የነበረውን ምስማር እየዳሰሱ ። "ወይ ነዶ! ጠላትን ገድሎ መሞት ክብርኮ

ነው! በምውትነት ሕያውነት! ውርደትን ቀጭ ብሎ ከመ
ጋት፣ ምሬቱንም በግዳጅ ከመ ዋጥ፣ ጠላትን አጥፍቶ መሞት፣
ሞትነቱ ከማር ይልቅ ይጥማል። እንደተከበሩ መሞት በክብር
መሞት ያህል ይቆጠራል። አላመቸኝም እንጅ፣ ይህ፣ የጣልያን
ፋሽስት አንገት ሲጐምድ የኖረ ጐራዴም በቀሌን ይወጣልኝ
ነበር!! ” አሉ የሽለላና የቀረርቶ ያህል ስሜታቸው እየሞከራ
ቸውና ጐራዴያቸውን መዘው እያወጡ። “ ወይ ነዶ! የውር
ደት ማኀደር ሆኜ ልቅር! አይደረግም! ግን ያንድ ቀን ጉዳይ
ነው! ሲያመቸኝ አርጄው እሞታለሁ!!......” አሉ ብስጭት
ናላቸውን በጥብጦት እየተወራጩ።

“ አይደለም! እርስዎ ብዙ ነገር አይተዋል! መታገሥ
አለብዎት! የማያልፍ ነገር የለም! የጊዜ ጉዳይ ነው። ትክክልኛ
ፍርድ የምናገኝበት ወቅት ይመጣል። ሩቅም አይመስለኝም።
መታገሥ ግን ይኖርብናል ” አለ አማቻቸው፤ ቆንጆ ሚስቱን
ካስጠለፈ ሣምንት ሆኖት፣ ከባለቤቱ አባት ጋር ስለጉዳዩ ለመወ
ያየት መጥቶ በትካዜ ስሜት ተዝናንተው የተቀመጡ እግሮቹን
እያነዘረ።

“ ትዕግሥትኮ ቁና አለው። መጠኑን ሲያልፍ ታጋ
ሹን ሊያሳብደው ይችላል። እኔ ግን እስካብድ ድረስ መጠበቅ
አይኖርብኝም! ባለቤቴን አርክሶብኛል! የልጆቼን እናት! የእህ
ቴን ባል፣ አድኃሪ የሚል ሰበብ ፈጥሮ እሷን እንደልቡ ለማግ
ኘት ሲል አሳስሮ፣ ይኸው በእስር ቤት ሲማቅቅ ሦስተኛ ዐመ
ቱን ይዟል! ሦስት ሴቶች ልጆች ቢኖሩኝ፣ ሦስቱንም ከናታ
ቸውና ከአክስታቸው ጋር እኩል ወሽሞ እንደ ባዝራ ባሰኘው





ቀጥር ይነዳቸዋል። አንድ ወንድ ልጅ ቢኖረኝ፣ በእህቶቹ፣
በናቱና በአክስቱ መዋረድ፣ በቀላቸውን ለመወጣት በሞከረ
ቀጥር፣ ፀረ ዐብዮት እየተባለ እንደጥጃ በየጊዜው ይታሠራል
ይፈታል።እንዱውም ሰሞኑን ከዚሁ ሰው ጋር ግጭት ፈጥሮ፣
ሊገድለው ዝቶበታል! ታዲያ ታገሥ የምትለኝ የቱን ነው?
መታገሤሥ ምን ሊፈጥርልኝ ነው? ውርደቴ ያደባባይ ይፋ
ከሆነ ሰንብቷል! .....” አሉ በደረሰባቸው ውርደት ተበሳጭተው
እዬዬአቸውን ለማቅለጥ እየዳዳቸው።

“ ዛሬ ደግሞ ምን ሆኑ? ብዙ ጊዜ ታግሠው የለ ምን?
ውርደቱ የመጣው በኛ ብቻ አይደለም። ባገር ላይ የመጣ፣
በየቤቱ የደረሰ ነው። ቆንጆ ሚስቱ ያልተጐሸመች በት፣ ኮረዳ
ልጁ ያልተደፈረችበት፣ በክብር የኖረች እናቱ ያልተዋረደችበት
እንደሌለ ያውቃሉ። ይህ ዐይነቱ ውርደት በሴቶቹ ወገኖቻችን
ላይ የደረሰ ሲሆን፤ በኢኮኖሚያችን መድቀቅ የተነሳ፣ ስንቱ
በረሀብ እንዳለቀ፣ ስንቱ በችግር እንደማቀቀ፤ ስንቱ ጤናውን
አጥቶ እንዳበደ፤ ስንቱ ቤት ሀገሩን፣ ዘመድ ወገኑን ጥሎ
እንደተሰደደ፤ ስንቱ ያለወንጀል በየእስር ቤቱ ያለፍርድ
እንደሚሠቃይ፤ ስንቱ በየመንገዱ ገላመጥከኝ እየተባለ
መከራውን እንደሚያይ፤ እርስዎም ሆኑ ያገሩ ሰው በሙሉ
ያውቀዋል። ታዲያ ለምንድር ነው መበሳ ጨትም? መበሳጨት
ብቻውን፣ ራስን መልሶ ይጐዳል እንጅ ምንም ፋይዳ
አይሠራ። ርግጥ በተለይ በኛ ቤተሰብ ሴቶች ላይ የደረሰው
ውርደት ወደር አይገኝለትም። ባለቤቴ እንደሚያውቁት ሁሉ፣
ከኔ በስተቀር በሕይወቷ ሙሉ ሌላ ወንድ አታውቅም። ምሥ
ክሯ ነኝ! ቀና ብላ እንኳ፣ ወንድ ቀርቶ ሴት አታይም ነበር።
ይኸው ዛሬ የውርደት ሸማዋን ለብሳ የመገን ሾላ መተረቻና

መዘበቻ ለመሆን በቃች ---" እንባው በፊቱ ላይ ኩልልል እያለ መንጠብጠብ ሲጀምር፣ መናገር አቅቶት ይንተባተብ ገባ።

" ሴቶቻችን ተዋረዱ ለምን ትለኛለህ! የተዋረድነው እኛ ወንዶቻቸው እንጅ! እነሱማ ምን ዓቅም አላቸው! የምና ስከብራቸው እኛ ነበርን! ጥንታዊ ብሂሉማ፣ ' መሪን በመን ግስቱ፣ ጐልማሳን በሚስቱ' ሲመጡበት ይሞታል እንጅ አሳልፎ አይሰጥም ነው የሚባለው! ታዲያ ሚስቴን፣ እህቴን፣ ሶስት ልጆቼን ለባዕድ ነጣቂ አስረክቤ እንዴት ታገስ ትለኛለህ! በዚህ ጥቁር የውርደት ህይወት ውስጥስ፣ መኖሬ ምን ትርጉም አለው ትላለህ? ሀገር፣ ነጻነት፣ መብት፣ ፍርድ፣ በኔ በዚህ የጨለማ ህይወት ውስጥ ምን ፍቺ አላቸው? ሰዎች ራሳቸውን እያታለሉ ይኑሩ! ሰዎች እኔንም ያታሉ! እኔ ግን ራሴን ማታ ለል አልችልም! በመሸ በነጋ ቁጥር፣ የነዚህ የሴቶች ወገኖቼ ውርደትና ርክሰት እንደ ትልቅ ገዳም ደወል ጆሮ ግንዴ ላይ እየጮኸ ጤና ከሚነሳኝ ይልቅ፣ ትክክለኛ የሆነ ምርጫየን ማዘጋጀት ይኖርብኛል። ታገሥ ብለህ የምታቀርብልኝን ምክር ህን፣ በውርደቱ ደወል ጩኸት ጆሮየ ስለደነቆረ ልሰማህ ልችልም። ይልቅስ በቀሴን የምወጣበትን ዘዴ ብትመክረኝ ይሻ ላል። እኔ አባትህ እንደሆንኩ ቆርጫለሁ---" ብለው በሣሎኑ ውስጥ እየተንጐራደዱ፣ የያዙትን ጐራዴ እንደ ቀላል ለበቅ ያውለበልቡት ጀመር። ከጐረቤታቸው፣ የታወቀ ካድሬ መኖሩ አላመቻቸውም እንጅ፣ " ገዳይ----ሰው ባገሩ፣ ሰው በወንዙ ቢበላ ሣር ቢበላ መቅመቆ፣ ይከበር የለም ወይ ሰውነቱ ታውቆ--" ብለው ለማቅራራት ነሽጧቸው ነበር። አባትና አማች





በዚህ ሁኔታ እንዳሉ፣ ወንድ ልጃቸው የሣሎኑን በር አንኳክቶ ዘው ይላል። አማችና አባት ያሉበትን ሁኔታ አይቶ ለጊዜው ግር አለው፣-

"ደኅና አይደላችሁም እንዴ?" ሁለቱንም ይጠይቃል።

" አይደለንም! " እየተንጐራደዱ " ደግሞ መቼ ነው ደህና ሆነን የምናውቀው " ለጥያቄው መልስ መሆኑ ነው፣ አባት ተናገሩ።

" የድሮው ትዝ እያላቸው እያወሩኝ ነው " አለ አማች ሁኔታውን ያበረደና፣ ልጁም እንዳያውቅ የሞከረ መስሎት፤

" ኧረ ምን የድሮ፣ የዛሬውን በለው እንጅ! " አሉ ከቁጣ ባላነሠ ተግሳጻዊ አነጋገር።

" እባክህ እንዲታገሡ ምከራቸው " አለ አማች፣ ከመቀመጫው እየተርበተበተ ተነስቶ።

" ስለምን ነበር የምትወያዩት? " አለ በሁኔታው ተደ ናግጦ ልጅ!

" ከቤተ ሰባችን ሴቶች ላይ ስለደረሰው ችግር ነበር " አለ አማች።

" ታዲያ ምን ተወያያችሁ! " ሲል ጠየቀ መነሻውን ለማወቅ።

" ኧረ ተወኝ! እበቀላለሁ ይላሉ " አለ አማች፣ ከመ ቀመጫው እየተርበተበተ ተነስቶ።

" አይ ይኸንንማ ጉዳይ ከኔም ጋር ብዙ ግዜ ተነጋግረን አንድ ሌላ ነጥብ ላይ ደርሰናል! " አለ ረጋ ብሎ ልጅ።

" ምን! የበቀል ርምጃ ለመውሰድ! " አለ አማች ተቻ ኩሎ " ብቻ ሁላችንንም እንዳታስጨርሱን! "

" ማለቅስ አሁንም ቢሆን ሁላችንም አልቀናል " አሉ አባት በሁለቱ መካከል ጣልቃ ገብተው ።

" አይ መጨረሱ የነሱ ፋንታ ነው፣ በኛ በኩል ግን የምናደገውን በደንብ ማወቅ አለብን ። ለማወቅም እንዲረዳን፣ ችግሩን በጠባቡ ሳይሆን በሰፊው ማየትና መመርመር አለብን ። የችግሩን መሠረታዊ ምክንያት ከሥሩ ሰርስረን መረዳት አለብን ። ከአባቴ ጋር እንደተነጋገርነው ከሆነ፣ በቤተሰባችን ሴቶች ላይ ስለ ደረሰው በደል፣ በጠባቡ አይተን የምንቀበልበትን ሁኔታ መንገድ ከማሰብ ይልቅ፣ ለበደሉ መነሻ የሆነውን ዋና ምክንያት፣ ዐቅማችን በፈቀደን መጠን ማናጋቱ ይበልጥ ዋጋ አለው----" ብሎ ገና የጀመረውን ሐሳብ ሳይጨርስ፤

" ሥርዓቱ ነው ጠላታችን ይልሃላ! " አሉ አባቴ እንደ ሥላቅ እየሞከራቸውና ሐሳቡን ለማካኪያስ እየተጣደፉ ።

" ትክክልኛ ነኝ! አልተሳሳትኩም! " አለ ልጃቸው ያለ ማመንታት ።

" ይኸውልሃ ሥርዓቱ ነው ሚስትህን ያስጠለፈው! " አሉ እየሳቁ ።

" አዎ ርግጠኛ ነኝ! ምን የሱ ሚስት ብቻ! በሚልዮን የሚቈጠሩ ሚስቶች ናቸው የተጠለፉት ። ጠምዛዛ ማሽን ግን ያነገባና ገዳዳ ባርኔጣ ያጠለቀ ተራ ወታደር ሁሉ፣ ያልተነኩሳቸው ሚስቶች ቁጥር እግጅ በጣም ትንሽ ነው ። ድሮም ቢሆን ድንቁርናው ሀገር ሲፈታ ምንም ያህል አልቀረው ነበር፣ ይኸው ዛሬ ኃይልና ሥልጣን አግኝቶ፣ በሰፊው ሕዝብ ላይ እየሸናበት ነው " አለ ።





" ሥርዓት የምትሉት የወታደሩን ሥርዓት ይሆን ? " አለ አማቻቸው፣ በቀረበው አዲስ ሐሳብ ውኸንብር ተመቶ!

" እባክህ እሱ የሚያትተው የሥርዓት ዓይነት ብዙ ነው! ከቅድመ ታሪክ፣ ከድኅረ ታሪክ የነበረ ሥርዓት፣ የባርነት ሥርዓት፣ የፊውዳል ሥርዓት፣ የሞናርሺ ሥርዓት፣ የምናምን ሥርዓት እያለ የማይዘበዝበው የነገር ዝግንትል የለም! " አሉ አሁንም በብስጭት የተበረዘ ሣቅ እየሳቁ ።

" ታዲያ የዛሬውን ሥርዓት ምን ሥርዓት ነው የሚሉት፤ እንዲህ የሰውን ሚስት ሁሉ የሚያስጠልፍ? " አለ አማች፤ አባትና ልጅ ተወያይተው ስላልተግባቡበት ሐሳብ እየጠየቀ ።

" ሲያምኑ አልፈለጉም እንጅ፣ በየዕለቱ የምንበላውን እንጀራ የየዘመኑ ሰው በእንዴት ያለ ሁኔታ ሲያገኝ እንደሚችል ዘርዝሬ በመተንተን በበቂ ማስረጃዎችና ማሳያዎች አስረድቻቸው ገብቷቸዋል፤ እህል በጠቅላላውም ለሰው ልጆች የሚያገለግሉ እቃዎች፣ ቆሳቁሶችም ሆኑ ሸቀጣ ሸቀጦች በምን ዓይነት ሁኔታ ተመርተውና ተገኝተው፣ ምን ዓይነት ኅብረተሰባዊና ተግባራዊ ግንኙነት ሲያስገዝፋቸው እንደቻለ፣ እነዚህንም ሲያስገኙ የቻሉ የየዘመኑ ተግባራዊ መሳሪያዎችና ኃይላተ-ምርት ሁኔታ ምን ዐይነት እንደነበሩና ዐይነታቸውም ከዘመን ወደ ዘመን በመደብ ቅራኔዎች ፍጭት አማካይነት እያደገ እንደመጣ በሚገባ አስረድቻቸው ተቀብለውኛል ። ይሁን እንጅ ሐሳቡን ቢቀበሉኝም አላመኑበትም ። ሳያምኑበት መቀበል ደግሞ ብቻውን ፋይዳ የለውም ። ደግሞም--- " ብሎ ሊቀጥል ሲል፤ አማች የሚስቱን አባት የጋለ ሐሞት ያበረደ መስሎት፤

“ ለበቀል ብቻ ቆርጦ መነሣቱ ብዙ አያዋጣም ። ታግሶ፣ አሁን እሱ እንደሚለው ሁኔታውያን ሁሉ በሰፊው በማየትና ለገጠመን ቤተሰባዊ ችግር ብሔራዊ መፍትሔ ለማግኘት መሞ ከር ያዋጣል ” አለ ሲፈራ ሲቸር፣ አማች የሚስቱን አባት ለማ ብረድ የሚጥርው፣ በሚፈጥሩት ጠንቅ፣ ዳፋው እሱም ላይ ሊደርስ እንደሚችል በመፍራት ነው ። በርግጥም የወታደሩ ፋሽስታዊ መንግሥት በእንደዚህ ያለው ጉዳይ ላይ፣ የተለ ምዶ አሠራሩና ተዘውትሮም የሚታየው፣ አንድ ሰው ሲቃረ ነው ያገኘ እንደሆነ፣ ሰውየውን ብቻ ማጥፋት ሳይሆን መላ ዘመዱንና የቅርብ ወዳጆቹን በሙሉ በመደዳ መጥረግ ነው ። ጅምላ ጠረጋ እንጅ ‘ወንጀለኛ’ የሚለውን ብቻ ነጥሎ ማጥቃት አይሆንለትም ። ከዚህም አደገኛ ሁኔታ ለጊዜውም ቢሆን የልጃቸው ሐሳብ አዳኝነት መልክ አለውና፣ የሱን ሐሳብ ይማጠናል ። ”

“ ምናልባት የሱ ሐሳብ አጠቃላይ መፍትሔ ሳይሆን አይቀርም! መፍትሔነቱም በሩቅ ሲታይ እንጅ በቅርቡ ላለው ጊዜያዊ ሁኔታ አይደለም ” አለ ወለል ወለሉን እየተመለከተ ።

“ አዎ የዋሔ! ለሩቁ እንጅ ለዛሬው ችግራችን መፍ ትሔ አይሆንም አልክ! ታዲያማ ምናለ፣ የባዕድ ዲቃላህን እስ ክትታቀፍ ድረስ ዝም ብለህ መጠበቅ ነዋ! እኔስ አይዋጥ ልኝም! የሚስቴና የሦስት ልጆቼ የባዕዳን ዲቃላዎች ቤቴን እስኪሞሉ ድረስ ቁጭ ብዬ ማየቱ አይሆንልኝም ። ከክፉ ዘር እርሾ ለማስቀረትም አይጠቅመኝም ። እኔ አንድ ነጠላዬን የተዋ ረድኩት አንሶኝ፣ የሚቀጥለውን ትውልዴን ክልስ እያሰኘሁ መኖሩ፣ ሳስበው እንኳን ይዘገንነኛል! ሞትን ለምን ብዬ ነው የምፈራው! በመወለዴ መሞቴንም አውቃለሁ ።ታዲያ መሞቴ





ላይቀር፣ ለምን ትርጉም ያለው ሞት አልሞትም? ለምንስ ሚስ ቴና ሴት ልጄ ለተዋረደችበት ወንድ ሁሉ፣ በሞቴ አርአያና ምሳሌ አልሆነውም ። እንዲያው ባታከላክሉኝ ደግ ነው ” አሉ አባት ከንዴታቸው ብዛት የተነሳ አረፋ መሣይ ምራቃቸው በከንፈሮቻቸው ዳርዳር እየተንዘረበረበ ።

“አይሆንም! የርስዎን ቆራጥነት ብቻ አይደለም ማየት! በሆነው ሁኔታ እስኪያልፍ ድረስ፣ እንደሆነው ሆነው መኖር የሚፈልጉ ዘመዶችዎም ይኖራሉና፣ ለነሱም ማሰብ ይኖርብ ዎታል! ” አለ አማች ተዳፍሮ!

“ አይ! ቆራጥነቱስ የምንፈልገው ስሜት ነው! ግን የቤ ተሰባችንን ሴቶች ያባለገ አንድ ደንቆሮ ወታደር መግደልና መሞት ዋጋ አይኖረውም ። የሚፈጥረው ጥቅም ዘለቄታነት የለ ውም ። እሱ ሲሞት ሌላ ፎጠናና ትኩስ ወታደር ሊተካ ይች ላል ። የሴቶቻችንም ውርደት፣ ሰው ቀየረ እንጅ አላከተመም ማለት ነው ። ስለዚህም ነው እኔ መነሳትም ሆነ መቃወም አለ ብን የምለው፣ ሥርዓቱን እንጅ፣ ሥርዓቱ የወለዳቸውን ጥቂት ግለሰቦች አይሁን! ” አለ ልጃቸው አሁንም አቋሙን ለማ ስረዳት እየሞከረ ።

“ እውነቱና ሐቁ ይኸ ይመስለኛል ። ግን ሥርዓቱ ስትል ምን ማለት እንደሆን ለኔ በመጠኑም እንደገና ብታብራ ራልኝ!! ” አማች ጥያቄውን በለዘብታ ያቀርባል ።

“ በገባሩና በጉልተኛው መካከል ያለው መሬት-ጠቀስ ፍልሚያ ገና ገፈቱ እንኳ አልተቀመሰም ። በላብ አደሩና በከበር ቴውም መካከል ያለው የፋብሪካዎችና ኢንዱስትሪዎች ተግባ ራዊ ፍልሚያ ገና እፍታው እንኳ አልተነካም ። በየረድፋቸው ያሉት መሠረታውያን ቅራኔዎች ገና ጥሬ ናቸው ። መፈታት

ቀርቶ አለሰለሱም ። በጊዜያችን የሁለቱም መንፀባረቂያ ሥልተ -ምርቶች በገጠርና በከተማ ጐልተውና ቅልጥጥ ብለው ይታ ያሉ ። ሞፈር ዘመቱ ገበሬ በጅ አዙር አሁንም ከገባርነት ኑሮው አልተላቀቀም ። ሰብሉን በማጭድ አጭዶ፣ ከምሮ ይጐትር እንጅ፣ ባመረተው ምርቱ አላዘዘበትም ። በሰበብ አሰባቡ ለባዕ ዳን ሀገሮች ሳይቀር እየተጋዘበት ነው ። ላብ አደሩ ሠራተኛ በፋብሪካ እሳትና በእንዱስትሪ ኰረንቲ እየተቃጠለ፣ በመዶሻው ቀጥቅጦ ያመረተው እቃ ሁሉ፣ ከበርቴው በፈጠረው ሽርክና ለባዕዳን በርካሽ እየተሸጠ፣ ጕልበቱ ባስገኘለት እቃ ራሱም ሆነ ወገኑ ሊጠቀምበት ካለመቻሉ አልፎ፣ ለላቡ የሚመጣጠን ዋጋ አላገኘበትም ። ይህ ሁሉ ምዝበራና ብዝበዛ፣ ጌልተኞችና ከበር ቴዎች ተባብረው በዘየዱት መላ፣ በዐብዮት ስም፣ አዲስ ጊዜያዊ መንግሥት፣ በሥውር እንዳሉ፣ መቋቋሙን አስነግረው፣ ብዝበዛቸው በአዲስ መልክና አቀራረብ እየተካሔደ ነው ። እንደ እባብ ቆዳ ያረጀው ጉልተኛና ከበርቴ ተገልፍፎ ይውደቅ እንጅ፣ አዲሱና አደገኛው ጉልተኛና ከበርቴ በቦታው ተተክቶ ይገኛል ። ምንም እንኳ በአርሶ አደሩ ገበሬና በጉልተኛው፣ እን ዲሁም በላብ አደሩ ሠራተኛና በከበርቴው መካከል በመፋተግ ላይ ያሉ ቅራኔዎች እድገታቸውን ጠብቀው አንድ መፍትሔ እንደሚያመጡ ቢታመንም፣ ለጊዜውም ቢሆን የቅራኔዎቹን ግለት ያበርዳል በሚል ግምት ጉልተኞችና ከበርቴዎች ከአጋር ባዕዳን መንግሥት ጋር በመዶለት፣ እንደራሴያቸውን ሥልጣን ላይ በማስቀመጥ አዲስ ጊዜያዊ መንግሥት አቋቁመዋል ። ‘ ጌዜያዊ ወታደራዊ መንግሥትም ’ ይባል ‘ደርግ’ በሙሉ ተጠሪነቱ ለአዲሱ የጉልተኛና የከበርቴ መደብ ነው ። በመካከ ላቸውም በወሸመጥ ገብቶ የጥቅምም ሆነ የሥልጣን ተካፋይ



የተጣሰ አጥር

የሆነው፣ በዘመናችን በዓለም ላይ ልዕልናን ለመቀዳጀት ያሰፈ ሰፈው፣ የዘመናዊው ሪቪዥኒዝም ባለቤትና፣ ሶሻል ኢምምፔ ሪያሊስት በመባል የታወቀው የሶቭየት ኅብረት መንግሥስት ነው ። ከኢትዮጵያ ጊዚያዊ ሁኔታ ላይ፣ ባለው መንግሥት አን ፃር እነዚህን ሦስት ጠላቶች ነጥሎ ማየት አይቻልም ። እስከዚህ ድረስ ከተከታተላችሁልኝ፣ ስላለው ሥርዓት እናገራለሁ ።

በበዝባዥ መደብ ደጋፊነት የተመሠረተ ማንኛውም መንግሥት፣ ሕዝባዊነት የለውም ። ሰፊው ሕዝብ ከጭቆናውና ከርግጫው በስተቀር ከእንዲህ መሰሉ መንግስት ሥልጣንም ሆነ ጥቅም አይጋራም ። ኢሕዝባዊ መንግሥትም በመሆኑ የገ ዥውን መደብ እንዳይቀናቀንበት ሲል፣ በመሠረቱ የሕዝብ የሆኑትን ዲሞክራሲያዊ ነፃነት፣ ዲሞክራሲያዊ መብት፣ ዲሞክ ራሲያዊ ፍትህ--- ይነፍጋል ። ተጋፍተው የሚመጡትንም ያጠፋል ። ይህ በመሆኑ፣ በሰፊው ሕዝብና በገዥው መደብ የማያቋርጥ ትግል ይካሔዳል ። የኃይል ሚዛን በሚወስነው መሠረት ይህ ትግል አንዴ ይከራል አንዴ ይረግባል ። አንዴ ይጦፋል አንዴ ይከስማል ። ግን ጨርሶ ሊጠፋ አይችልም ። ከዚህ የትግል ሐረግ ውስጥ አንዲቷን መዘን እስከጫፏ ብንደ ርስ ያቺ የሐረግ ዘለላ ከኛ ቤተሰብ ውስጥ መርታ ታመጣንና በኛና በጠላቶቻችን መካከል ከሚካሔደው ትግል ላይ ታደርሰ ናለች ። የኔን እናት አክስትና ሦስት እህቶች በገዛ ሀገራቸው በገዛ ሕዝባቸው መካከል የውርደት ጋቢ አልብሶ የሚጫወት ባቸው ላለው መንግሥት አጋር እሆንሀለሁ ብሎ በመግባት የሥልጣንና የጥቅም ሙሉ ተካፋይ የሆነው የባዕድ መንግሥት ቅጥር ወታደር ነው ። እናቴንም ሆነ የቀሩት ዘመዶቼን ለስሜቱ ማርኪያ ማድረጉ ከጥቃቅን ጥቅሞቹ እንደአንዱ ሊቆ ጠር ይች

ላል ። ይህንን የማይገባ ጥቅሙን እንዳያገኝ መቆጣ ጠሩም ሆነ
መከላከሉ የኛ ግዴታ ነው ። በዚህም ረገድ አባቴ የሚያደርጉት
የበቀል ዝግጅት ሁሉ ትክክል ነው ። ግን የሐረጉ ግንድ እስካለ
ድረስ አንዲቷን ዘለላና ቅርንጫፍ ለመቍረጥ ማቀዱ ብዙ ረብህ
አይኖረውም ። ስለሆነም ተባብረን ግንዱን መገዝገዝ ብሎም
ቆርጦ መጣል ይኖርብናል ። ይህ ግንድ ሥርዓቱ ነው ። አምባ
ገነን ፋሽስታዊ የወታደር መንግሥት ከአጋር ኃይሎች ጋር
(ጉልተኛ፣ ከበርቴ፣ ሶሻል ኢምፔሪያሊስት) ያቋቋመው ኢሕዝ
ባዊ ሥርዓት ነው ። ባጭሩ ሲካተት፤ በማቆጥቆጥ ላይ የሚገ
ኘውን ቡርዡዋን፣ ሙጥኛ ብሎ የተቆራኘ፣ የቀኝ ክንፍ ንዑስ
ከበርቴ አጋፋሪ የሆነ የፋሽስት መንግሥት ነው ። በነጣላ አምባ
ገነን መሪ የሚነዳው ያስተዳደሩ ጋሪ፣ በየአቅጣጫው ለከፈተው
ጦርነት፣ በገጠርና በከተማ ባሉ ቢሮክራቶች፣ የየቀበሌ ካድሬ
ዎች፣ የሠራተኛ ማኅበራት ሹማምንቶች፣ የገበሬ ድርጅት ተጠ
ሪዎች አማካይነትና ቀጥተኛ ወኪልነት፣ በአዋጅ የወረሰውን
ሀብት ሁሉ ከቍጥጥር ሥር በማዋል ካፒታል ይሰበስባል፣ ቦም
ብና ታንክ ይገዛል ። ሕዝብ ይገድላል፣ ያርዳል፣ ያቃጥላል ።
ቅይር ቋንቋ አምጥቼ፣ " የቀኝ ክንፍ፣ የቡርዥዋ ተቀፅላ ነው"
ስላችሁ ግር ይላልና በግራዝያኒ ይመራ የነበረው የጣልያን
ወረራ በፈጸመው አሠቃቂ ግፍ አንፃር፣ የፋሽስትን ትርጉም
ይበልጥ እንደምትረዱት በማመን፣ ከዚያ አሥር ጊዜ የሚከ
ፋውን የዛሬውን ፋሽስት፣ ከዚያ የጣልያን ፋሽስት ጋር እንድ
ታነፃፅሩት ከመጠቆም ይልቅ ሌላ ያገላለጥ ምርጫ ያለኝ
አይመስለኝም ። በተጨማሪ ልገልፀው የምፈልገው፣ ይህ ሴቶች
ወገኖቼን ያዋረደ ባዕድ ወታደር፣ ጉልበት ያገኘበትን መሣሪ





ያዎች፣ ጠብመንጃም ሆነ ጅፕ ታንክም ሆነ ሮኬት ከየት ያገ
ኘው መሰላችሁ? ፋሽስቶች ባቋቋሙት ሥርዓት አማካይነት
ከሕዝባችን በየረድፋና በየመልኩ ከሚዘረፍ ሀብት፤ ከሶሻል
ኢምፔሪያሊስቶች የተገዛ ነው ። ይህን የሕዝባችንን መዘረፍ
ተባብረን ማስቀረት ብንችል፣ እንኳን ሴቶቻችንን ቀርቶ፣ የጊቢ
ያችንን ዝንብም እሽ ማለት አይችልም! ትሰሙኛላችሁ ---"
አለና ረዥም ዲስኩሩን አበቃ ።

" ምነው ይኸን ሳላይ ቀደም ብዬ በሞትኩ! " አሉ
አባት በትካዜ ባሕር ሰጥመው ። ይህ አባባል፣ ብዙዎች ያገራችን
የጊዜው አረጋውያን፣ በየዕለቱ የሚናገሩት ነው ። መጦር በሚ
ገባቸው ዘመን ብሔራዊ ክብራቸው ተገፎ፣ ሽምግልናቸውም
ሆነ ዜግነታቸው ተንቆ፣ ከሠፍነግ የመረረ ኑሮ፣ በህይወታቸው
መጨረሻ ዘመን ስላጋጠማቸው በምሬት የሚናገሩት ነው ።

ለባላምበራስ ገብርዬ ግን፣ የፊተኛውም ቅድመ ፋሽስት
ዘመን፣ የደስታና የፍስሐ ዘመን አልነበረም ። በተፈጥሮአቸው
ሕዝባዊ ዝንባሌ ያላቸው በመሆናቸው፣ ካለፉትም ባለሥል
ጣኖች ጋር ሳይጣጣሙ የኖሩ ናቸው ። ከግዞት ባላነሰ ሹመት
በዳር አገር ሲንከራተቱ የኖሩ ነበሩ ። መሰል የድሮ ጓደኞቻቸው
ቢትወደድ፣ ደጃዝማች፣ ሲባሉ፣ እሳቸው ግን ተጀምሮ እስኪ
ጨረስ በባላምባራስነት ደረጃ ነው የኖሩት ። የወታደሩ ፋሽስ
ታዊ መንግሥት፣ በጡረታ መልክ እስካወረዳቸው ጊዜ ድረስ፣
ያንድ አውራጃ አስተዳዳሪ ነበሩ ። በአቆርቋዥነት ድምር መዝ
ገብ ውስጥ ያስገባቸው እንጅ፣ ባላምባራስ ገብርዬ ጡረታ
ወጡ በተባለ ቀን፣ ያውራጃቸው ከተማ ሕዝብ ተኩስ ከፍቶ፣
" እስቲ ማነው አስተዳዳሪያችንን የሚሽርብን! " እያለ አንድ
ቀን ሙሉ ሲያንጣጣ ውሏል ። " ለሶሻሊስት ትምህርታዊ ጥም

ቀት እንዲካፈሉ እንጅ፣ ተመልሰው ይመጣሉ ” በሚል ዘዴ የተነሳውን ዐመፅ አበረደው እንጅ፣ በአስተዳዳሪነት ተወዳጅነታቸው ወደር የማይገኝላቸውን ባላምባራስ፣ ከአውራጃው እንዲለዩበት ሕዝቡ አልፈለገም። በተለይም ባላምባራስን ይበልጥ የሚወዳቸው የየባላባቱና የየትልቁ ሰው አንጋች የሆነ ጐረምሳ ሁሉ፣ ወሬሣ ሊመታ ተስማምቶ ዱር እስከመግባት ወስኖ ነበር። ይህ የኅብረተ-ሰብ ክፍል ባላምባራስን እንደነፍሱ የሚወድበት ዋናው ምክንያት የሰውን መሠረታዊ እኩልነት* ላይ፣ የጌቶቻቸውን በቅሎም ሆነ ፈረስ ልጓም ይዘው ግማሽ ቀን ያህል፣ ጌቶቻቸው በእልፍኝ ውስጥ ጠጥተው እስኪረኩ ድረስ መጠበቅ ነበረባቸው። በዚያ አውራጃ ባላምባራስ ገብርዬ ከገቡ ጀምሮ ይኸ ድርጊት አክትሟል። የባላምባራስ አንዱ የትርፍ ሰዓት ተግባራቸው፣ እነዚህን የጌቶቻቸውን ፈረስ ጠባቂዎች፣ በራሳቸው ገንዘብ እየጋበዙ ከጌቶቻቸው እኩል አስቀምጠው ማስተናገድና፣ በየመጠጥ ቤቱ ደጃፍ ላይ ሁሉ የፈረስና የበቅሎ ማሠሪያ ምሰሶ ማስተከል ነበር። ከዐመት ቆይታም በኋላ፣ ይህ ጌቶችና አሽከር፣ አብረው በእኩልነት የመጠጣቱ ጉዳይ የተለመደ ተራ ነገር መሆን ችሏል። ባላምባራስ፣ ለዚህ ድርጊታቸው ቅመም እንዲሆን በማሰብ፣ በየመጠጡ ቤት ለዚህ ተግባራቸው በተሰማሩ ቁጥር የሚያሰዝኗት አንዲት ዜማ ነበረቻቸው፣

“ ጌቶችም ቢሆኑ እንደኛው ሰው ናቸው!
እሜቴም ቢሆኑ እንደኛው ሰው ናቸው!
ከኛ የተለየ ምን እግር አላቸው?

* (የተዘለለ)— በጥቃቅን ምግቢዎች ሳይቀር፣ስላላዩትና ስላልተማሩት ነው። ወትሮ በየጠጁ ቤትና በየመሸታ ቤቱ ደጃፍ.....





ከኛ የተለየ አራት እጅ የላቸው?
በባሕርይ እንጅ የምናከብራቸው!!” ይሏታል በአራራይ ዜማ።

ባላምባራስ ገብርዬ፣ በሚያስተዳድሩት አውራጃ ሕዝብ በጣም የተወደዱና የተከበሩ በመሆናቸው፣ አንድ ቀን ሕዝቡን ያሣምፅና ያስነሣብናል በሚል ፍራቻ ብቻ በጡረታ ተገልለው እግድ የተጣለባቸው አዛውንት ናቸው። ማእከላዊ እድሜአቸውን አገባደው፣ ወደ ሽምግልና ዘመናቸው የገቡ ትክክለኛ ሰው ናቸው።በዚያ ዘመን ሁሉ የሥልጣን ጊዜያቸው፣ የወደሮ መሬት እንኳ በርስትነት የላቸውም። ሌላው ቀርቶ፣ በአውራጃው ውስጥ በአስተዳዳሪነት የኖሩት፣ በራሳቸው ገንዘብ በተከራዩት መለስተኛ ቤት ውስጥ ነው። መተያያም ሆነ ጉቦ ሲያልፍም አይነካቸው። የሚያደርጉት ውሳኔ ሁሉ፣ ሕዝቡ መርጦ በሰየማቸው የጉባኤ አባሎች የሚጸድቀውን ብቻ ነበር። ላጠቃላይ ስብሰባ ጠቅላላውን ያውራጃ ሕዝብ የጠሩበት ጊዜ ጥቂት አልነበረም። የያኔው ማዕከላዊ መንግሥት ያልፈቀደላቸው ሆኖ ነው እንጅ፣ ከበጐ አድራጊ፣ ገለልተኛ መንግሥታት እርዳታና ብድር በቀጥታ በአውራጃው ስም በመጠየቅ፣ ያውራጃቸውን ሕዝብ ኑሮ ለማሻሻል ያልሞከሩት መንገድ የለም። አንዱ የሚያበሳጫቸውና ካለፈው መንግሥት ባለሥልጣኖች ጋር ሲያናቋራቸው የኖረው የዚሁ ሕዝባዊ እቅዳቸው አለመሣካት ነው። ከማስተዋልና ከኑሮ ከቀሰሙት እውቀት በስተቀር መደበኛ ትምህርት የላቸውም። በጐ ፈቃድና ቅን ሐሳብ በባሕርያቸው ላይ የሠፈነ በመሆኑ፣ አለመማር የሚፈጥረው ጥቁር ጠባይ በሳቸው ላይ አልሠረፀም። በሥልጣን ላይ በነበሩበት ጊዜ ሁሉ፣ የግል ኑሮአቸውና ትዳራቸው

ትዝም ብሏቸው አያውቅ ። ያውራጃ ሕዝባቸው በየረድፉ
ሊያድግ የሚችልበትን መንገድ ከማውጠንጠን በስተቀር ፣ ሌላ
ነገር የሚያስቡበት ኀሊና አልነበራቸውም ። ሌላው ቀርቶ ፣
በበዓልም ሆነ በተራ ቀናት የሚለብሱት ልብስ ልዩነት የለ
ውም ። በቅርቡና ባጠገቡ ተገኝቶ ፣ የሕዝቡን ችግርና ብሶት
ለማቃለል ሲሉ ፣ በየሚጢጢዋ ቀበሌና ወረዳ ሲዘዋወሩ ፣
በአውራጃ ቤታቸው የሚገኙበት ወቅት በጣም አጭር ነበር ።
እንዲውም ቤተሰባቸው ፣ ከመለያየት ቆይታ የተነሳ ፣ የሚነፋ
ፈቁበት ጊዜ አለ ። ለሚያስተዳድሩት ሕዝብ ፣ ዘመኑ ከፈቀደ
ላቸው የበጐ ፈቃድ መጨረሻ ክልል ድረስ ፣ ካንጀታቸው
ርዳታ አድርገውለታል ። አንዳንዴም ክልሉን እየጣሱ በመገኘ
ታቸው ፣ በበላይ ባለሥልጣን ተጐሽመዋል ፣ ተኰርኩመዋል ።
ከነበራቸውም ሥልጣን እንዲባረሩ ፣ ካንድ ሁለት ጊዜ ያህል
ተወስኖ ፣ በራስ እምሩ አማላጅነት ታልፈዋል ። ከአውራጃ አስተ
ዳዳሪነት ምድብ ሥራቸው ሌላና ፣ ጠቅላይ ግዛቱና የሀገር
ግዛት ሚኒስቴር ከሚሰጠው የሥራ መምሪያ ክልል ውጭ ፣
ምንም ዓይነት ተግባር እንዳያከናውኑ ፣ ጥብቅ ትእዛዝ በየጊ
ዜው ቢተላለፍባቸውም ቅሉ ፣ ባላምባራስ ግን ሕዝቡን በየአቅ
ጣጫው እያስተባበሩ ለልማትና ለእድገት እንዲሠማራ በማድ
ረግ ፣ ተዝረክርኮ የኖረውን የአውራጃውን ኅብረታዊ ተግባር
ሥርዓት አሲዘውት ነበር ።

አውራጃው በራሱ አስተዳደር እንዲመራ አዘውትረው
በመወትወታቸው ፣ ማዕከላዊው መንግሥት በጣም ይፈራቸው
ነበር ። ለዚህም ፍራቻው ሲል ነው ከሦስት ያላነሱ ምክትል
አውራጃ አስተዳዳሪዎች ሾሞ ፣ ባላምባራስን እንዲቈጣጠሩ ያደ
ረገው ። ባላምባራስ ግን ፣ በየገጠሩ እተየተዘዋወሩ ከገበሬው





ቤት በማረፍ የሚበላውን እየበሉ ፣ የሚጠጣውን እየጠጡ ፣ የቅ
ርብ ችግሩን እየተወያዩ ከጭብጥ ሁኔታ በመረዳት ፣ የሚመ
ኙትን ያህል ሊረዱት ባይችሉም ፣ ለችግሩ ጊዜያዊ መፍትሔ
ከመስጠት አልተቆጠቡም ። የዘለቄታ መፍትሔው ምን መሆን
እንዳለበት ቢያውቁም ፣ በተግባር ለመግለጽ ፣ ካቅማቸው በላይ
በመሆኑ ምን ጊዜም ያዝኑ ነበር ። ሆኖም ያውራጃውን ሕዝብ
በኅብረት እርሻ ለማሠራት የቻሉ ፣ የመጀመሪያ አስተዳዳሪ
ናቸው ። ምናልባትም ለዚህ ውጤት መብቃታቸው ፣
በሚያስተዳድሩት አውራጃ ውስጥ የነበረው የመሬት ሥሪት
የዘር ርስት የሚባለው ዐይነት በመሆኑ ፣ እንደሌላው ክፍለ
ሀገር ፣ የገባርና የጉልተኛ (ጢሰኛና ባላባት) ቁርቋሶ
ስለሚያፅዕበት ይሆናል ። በዚህና በዚህ መሰል ድርጊታቸው ፣
በአውራጃው ሕዝብ ከፍተኛ ተወዳጅነት አፍርተዋል ። ከመወ
ደዳቸው ብዛት የተነሣ ፣ ከሕፃን እስከ ሽማግሌ ፣ ለማረጋገጫ
የሚጠቀምበት መሐላ ሁሉ የሳቸው ስም ነበር ።


በሀገራችን ለውጥ እንዲመጣ ከፍተኛ ምኞት ከነበራ
ቸው ሰዎች ውስጥ አንዱ ባላምባራስ ነበሩ ። ራሳቸው መሥ
ራት እንኳ ባይችሉ ፣ የሚሠሩ ሰዎች ተመርጠው ፣ ያዲስ ሕይ
ወት አዲስ ልማታዊና እድገታዊ ትርዒት ማየት ደስታቸው
ነበር ። በወርኀ የካቲት ፣ የተመመው ሕዝብ ፣ የለውጥ መፈክ
ሩን ይዞ ሲነሣና ፣ አሮጌ ሥርዓት ሲያናጋ በመመልከታቸው ፣
ደስታ ፈንቅሏቸው ፣ ታመው የማያውቁትን ፣ ሁለት ቀናት
ያህል አልጋቸው ላይ አሣልፈዋል ። ይህ በሆነ በዓመቱ ነው ፣
ከእስረኛነት ባልተሻለ ሁኔታ ፣ በጡረታ ተገልለው ፣ ያዲስ
አበባን ከተማ ክልል እንዳይወጡ ታዘው ፣ በሚኖሩበት ቤት
እንዳሉ ፣ አዲሱ መንግሥት ያመጣውን ግፍ እየጐፈነናቸው
በመቅመስ ላይ ያሉት ።

በሀገራችን ጥንታዊ ባህል መሠረት፣ በቁርባን ያገኟቸው ሞንዳላ ባለቤታቸው፣ ባላምባራስን በፀለም መገኘታቸው ከሚያስደስታቸው አንዱ ምክንያት ናቸው። ተፈጥሮ፣ በልዩ ጥበባዊ ኪነቷ፣ ውበትን ደርባ ሠልሟ ስትስልባቸው የኖረች ይመስላሉ። ያያቸው ዐይን ሁሉ በውበታቸው ተደናግጦ፣ ላጭርም ጊዜ ቢሆን ይንሸዋረራል። ተፈጥሮ ተጨንቃ ስትሠራቸው ለመኖሯ፣ ደላንታዊ አፍንጫቸው፣ ዋድላዊ ከንፈራቸው፣ ኩረማሽ ጉንጮቻቸው፣ አዘፀ ሽንጣቸው፣ ጉልህ ምስክሮች ናቸው። ረዥሙ ሐርማ ፀጉራቸው፣ አስር ሺህ የተራቆተ ጉልማሳን፣ ከነስሜቱ ያለብሳል። ስለአቋማቸውና አረማመዳቸው መናገር ከንቱ ነው። ለሰዎች ያልተሰጠ ልዩ ተውህቦ ነው። ባላምባራስ፣ እኚህን መሳይ ባለቤት ለማግኘት የበቁት፣ በጣልያን ጊዜ በፈፀሙት ጀብዱና በአስገኙት ከፍተኛ ዝና አማካይነት ነው። አለያ ወይዘሮ የውብዳርን ማግኘት ቀላል ትግል ብቻውን አይበቃም ነበር። አብረው በኖሩበት ዘመን፣ ፍቅር በቤተሰባቸው ውስጥ ድንኳኒን ጥላ፣ ፍስሓና ደስታን አስፍና ከመኖሯም በላይ፣ ያራት ብርቅዮች ልጆች ባለቤት አርጋቸዋለች። ሲዋደዱና ሲከባበሩ ላያቸው ሰው፣ ምነው እነሱን ባረገኝ እስከማለት ያስቆጯሉ፣ ያስቀናሉም። ሦስት የመጀመሪያ ተከታታይ ልጆቻቸው ሴቶች ሲሆኑ፣ አረተኛውና የመጨረሻ ልጃቸው ወንድ ነው። እነሦስቱን እናታቸውን አይቶ ማየት ነው። ዘመናዊውን ሜክአፕ እየጨመሩበት፣ ከናታቸው አስበልጦ ፍፁም መላእክት አስመስሏቸዋል። ሁለቱ የተዳሩ ሲሆኑ አንደኛዪቱ ገና ናት። የመካከለኛዪቱ ልጅ ባል፣ ባልታወቀ ምክንያት ተገድሎ ከሞተ ስድስት ወራት አልፎ





ታል። በፀረ አብዮት ተሳቦበት፣ በባእድ ወታደሮች በጩቤ ተዘክዝኮ፣ አይሞቱ ሞት እንደሞተና በዚያው በሞተበት ምሽት መኪናውም ተቃጥላ መገኘትዋ፣ ላዲስአቦች ያደባባይ ትንግርት ሆኖ እንደታሪክ የሚነገር ግዳይ ተደርጓል። የሞተበት መሠረተ ምክንያት ግን እንደተባለው በፀረ ዐብዮትነት ሳይሆን፣ ውብ ሚስቱን ለማስከበር ባደረገው ቆራጥ ሙከራ ነው። ሚስቱ ሁለተኛዪቱ የባላምሪስ ልጅ ስትሆን፣ የሦስት ውብ ልጆቻቸው ኮከብ ናት። ባሏ ከሞተ ጀምሮ የምትኖረው ከባሏ ገዳይ ጋር ነው። ይህም የውዴታ ሳይሆን የግዴታ ነው። ይኸው አስገዳጇ የባዕድ ወታደር፣ በሷ አሳቦ፣ ጠቅላላ የቤተሰቧን ሴቶች፣ እክስቷንም ሳይቀር ወሽሞ በፈለገው ሚና እየንዳቸው ነው። ትንሿን ሴት ልጅ ገፈርሳ በሚገኝ ቪላ ውስጥ ቅምጥ አርጓት ዐመታት አልፈዋል። የእክስቷን ባል በፀረዐብዮት ስም አራተኛ ክፍለጦር ውስጥ፣ ያላንዳች ፍርድ አሟስሮ፣ የባል ያህል ካክስቷ ቤት ይወጣል ይገባል። እናታቸውን ሲፈልገው በስልክ፣ ሲያሻውም ከቤታቸው ደጃፍ እየመጣ፣ ያመላልሳቸዋል። አንድ የቀረችው የመጀመርያ ልጃቸው ነበረች፣ እሷንም ከባሏ ላይ ጠልፎ በመውሰድ፣ ነፋስ ስልክ ከሚገኝ ከአንድ ደጃዝማች የተወረሰ ቪላ ውስጥ ካስቀመጣት ሣምንት ሆኗታል። ስለተጠለፈች ሚስቱ ለመወያየት መጥቶ ነው፣ አማች ካባቷ ቤት እንዳለ፣ ቀደም ሲል ሲነጋገሩ ያገኘናቸው። በዚያን ቀን፣ ልጅ፣ አባት አማች ሆነው ባንድነት የጦፈ ውይይት በማካሔድ ላይ እንዳሉ፣ የጅፕ መኪና ጥሩምባ፣ ከውጭ፣ ሦስቱም ይሰማሉ። እንደለመደው እናትን ሊወስድ፣ መጥራቱ ነው። አባትና ልጅ ጥሩምባውን ለምደውታልና፣ ይኸውልህ ሊወስዳት መጣ! ብለው ለአማች ይነግሩታል። አማችም "እስቲ ስለሚስቴ ሁኔታና ደኅንነት ልጠይቀው! መቸም ከሱ ሌላ



# ችካል

ተክለው የማይተውት፣ተቸክሎም ላይቀር፣
በነጋ በጠባ፣መሮጥ ለመቀርቀር፣
ሞራል ኤቲክስ ገድሎ፣ ያን ስሜት ለማክበር፣
ሙስናን አንግሦ፣ኀሊናን ለመቅበር፣
አለ ሲያደዘድዝ፣ሲያሽቃብጥ በሀገር፣
አረም በቀል እንጨት፣ ከመራጃው ጭምር፣
ችካሉ ናዚራ፣ የወሲብ ድንብርብር!!





የሚደፍረን የለም!" ብሎ፣ ደመ-ነፍሱን የሳሎኑን በር ከፍቶ፣ ወደ ዋናው አጥር በር ያመራል።

" ባትዋረድ ደግ ነው!" አለ የባላምባራስ ልጅ፣ የሳሎኑን መስኮት ከፍቶ ወደ አማቹ እያቀና።

" ደኅንነቷ ብቻ ለመጠየቅ ነው! " አለ አማች የሚስቷን አቃጣይ ፍቅር፣ ውስጥ ውስጡን አንፍሮት ማልቀስ እየቃጣው።

የውጭውን በር ከፍቶ እንደወጣ፣ መረመንድ ግንድ የሚያህል ሰው፣ ጅፒን ተደግፎ ከውጭ ቆሞ ያገኛል። ዐይኑ ላይ ጥቁር መነጥር ገትሯል። በቀኝና በግራው ሽንጡ ላይ ከጠመንጃ የሚስተካከሉ ሁለት ሽጉጦች ታጥቋል። ያደረገው ጫማ ቅልጥሙን በሙሉ ሸፍኖ ከጉልበቱ ሎሚ ይደርሳል። የለበሰው ዥጉርጉር ነብርማ ካኪ ሲሆን፣ ጕፈሬውን የምትሟገት ኮፊያ ራሱ ላይ ጣል አርጓል። ሥንዝር የሚያህል የትንባሆ ሲጋር አፉ ላይ ለጉሞ ጢሱን ያቦናል። ደረቱ ላይ ያለው ፀጉር እመጫት ድመት ከነልጆቿ ይደብቃል። ካንገቱ ሥር፣ ያልተደረደረ የወርቅ፣ የብር፣ የነሐስ ጌጣ ጌጥና ሐብል አይገኝም። ከግራ እጁ ላይ ቋጥኝ የሚያህል ሰዓት አሥሯል። ከሰዓቱም አጠገብ አምባሮች ተደርድረዋል። አስሩም ጣቶቹ በተሸከሙት የቀለቤቶች ብዛትአለመድከማቸው መጥኔውን ይስጣቸው።ደረቱ ላይ፣ ያቡነ ሰላማን ጢምና ሪዝ የሚስተካከለውን የዕንቶኔን ገፅታ የሚያሳይ ምስል ለጥፏል። በዚህ ሁኔታ ከባላምባራስ ደጃፍ ላይ እንዳለ ነው፣ አማች ሆዬ ሲፈራ ሲቸር ለማነጋገር የከጀለው።

" ጉድ ሞርኒንግ ሰር " ይላል እንደባሕሉ እጅ እየነሳ አማች፤

" የስ ጉድ ሞርኒንግ! " ይላል ከግልምጫ ጋር፣ ወታደሩ!

" አይ ሀቭ ኤ ፕሮብሌም " አለ አማች እየተሽቆጠቆጠ

" ሁዋት ፕሮብሌም? " አለ ጥምባሆውን በብዛት እያቦነነ

" ማይ ዋይፍ ኢዝ ሎስት " አለ አማች ሚስቴን መልስ ልኝ በማለት ፈንታ ።

" አር ዩ ክሬዚ! ሺት! " ሲጋሩን አጭሶ ሲጨርስ ነበረና፣ ቀሪዋን ቁራጭ ይወረውርበታል ። ወደ አማችም ይበልጥ ቀረብ ብሎ " ጎ አንደ ቴል ቱ ቤንጂስቶ! አይ ዶንተ ኬር!" አማችን አንድ ካልቾ አቅምሶ ካጠገቡ እንዲሄድ ያዘዋል ።

አማችም በሁኔታው ተደናግጦ ወደ መጣበት ሊመለስ በሩን ሊከፍት ሲል፣ የባላምባራስ ሚስት ተዘጋጅተው ሲወጡ ያጋጥመዋል ። ይህም ሁናቴ ተጨማሪ ማስደንገጫ ሆነበት፣ እናቱ እንደጠፋችበት ሕፃን፣ እሪ ብሎ ሲጮህና፣ ጅፑ አማቴን ጭኖ ይዞ ሲሔድ እኩል ይሆናል ። ጩኸቱን የሰሙ አባትና ልጅ ከቤት ሮጠው ቢመጡ፣ አማቻቸው፣ የቀጠቀጡትን ያህል ተዝለፍልፎ ደጃፍ በመውደቅ ሲያላዝን ያገኙታል፣ ደጋግፈው ከቤት ካገቡት በኋላ፣

" ነግሬህ ነበርኮ! " አለ ልጃቸው ። አማች ግን ሊያዳምጠውም አልቻለም ። ትንሽ ቆይቶ ነፍሱን ሲዘራ፣

" ባላምባራስ ትክክል ናቸው! " አለ እቅታ እየሞከረው ።

" አሁን ገባህ መሰለኝ!" አሉ ባላምባራስ እየተኰራሩ!!

" እኔና ርስዎ እንበቃለን ። ሐረጉን እንቆርጣለን ። ልጅዎ እንደሚለው፣ እሱም ግንዱን ይቍረጥ! " አለ ንዴትና ብስጭት በሸፈነው ለቅሶ እየተንሠቀሠቀ ።





" ጥሩ፣ ሁለታችንን አያቅተንም! አፈር እናስግጠዋለን!" አሉ ባላምባራስ፣ በስተኋላ ሐሰባቸውን የደገፈላቸውን አማቻቸውን እያፅናኑ ። ታዲያ ማውደም ያለብን እሱን ብቻ ሣይሆን፣በሚረጨው ገንዘቡ ባሪያው ያረጋቸውንና የኛን ቤት ሴቶች ጠቁመው ያሳዩትን ካድሬዎችና የቀበሌ ሹሞች ጭምር ነው " አሉ ባላምባራስ፣ በንዴት ።

" እርስዎ እንዳሉ! ቁርጥም ቁርጤ ነው! " አለና ተስማሙ ። በዚያንው እለት መንፈቀ ሌሊት ላይ፣ ሚስታቸውን ወደ ቤታቸው ሊመልስ ሲመጣ፣ በጐራዴና በጦር ሊበቀሉት ወስነው፣ ቀኑን ሙሉ ዝግጅት ሲያካሔዱ ዋሉ ። እቅዳቸውም እሱን ካረዱ በኋላ፣ ወደ ጠቋሚ ካድሬዎችና የቀበሌ ሹማምንት ቤት ሌሊቱን ለመሔድና ተመሳሳይ ግዳጅ ለማከናወን ነበር ። ግን ምን ይሆናል፣ በዚያን ዕለት ማታ በአማቻቸው ልፍስፍስነት እቅዳቸው ሁሉ ከሸፈ፣ የባላምባራስ ጐራዴ ብቻ፣ የወታደሩን ጆሮ ግንድና ግራ ዓይን ሲበቀል፣ አስከትሎት መጥቶ የነበረው የወታደሩ ጓደኛ፣ ተወልደው ባደጉበት፣ ተድረው በወለዱበት፣ በገዛ ሀገራቸው ከተማ፣ በተፈጠሩበት ምድር፣ በኖሩበት ቤት ደጃፍ ላይ፣ ባላምባራስን የሽጉጥ ጥይት አርከፍክፎባቸው ጠላታቸውን ሳይገድሉ ወደቁ ። ተገደሉ ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላም፣ ምድረ ወታደር፣ ምድረ ነጭ ለባሽ ግቢያቸውን ወረረው ። አማቻቸው በጥይት ቆስሎ፣ ከነጦር ኤግዚቢቱ ተያዘ ። የባላምባራስ ሬሳም ለምርመራ ተወሰደ ። እቤታቸው የነበረ ሰው ሁሉም ሲያዝ፣ ያ ልጃቸው ብቻ፣ በማይሳካ እቅዳቸው ቀንም ቢሆን አልተስማም ነበርና አምልጧል ። እስከዛሬም ይኑር ይሙት አይታወቅም፣ ተፈልጎ አልተገኘም ። በማግሥቱም፣ ጋዜጣውም ሬድዮኑም ቴሌቪዢ

ኑም በሙሉ ባላምባራስ ባላምባራስ ሸተተ። የለየላቸው አድ ኃሪ! ታዋቂውን ተራማጅአጋራችንን ሊገድሉ ሲሞክሩ ተገደሉ አለ። በምሽቱም ፕሮግራም ላይ፣ ሊገደል ሙከራ ስለተደ ረገበት የቅጥሩ ወታደር ዝናና ታሪካዊ ተግባር መግለጫ ተነገረ። ስለ ሶሻሊስት ዲስፕሊኑ፣ ስለ ኢንተርናሽናል ሰብዕ ናው ወደር የማይገኝለት ተራማጅ ወታደር ስለ መሆኑ ተተ ረከ።-------

ይህ ወታደር የኢትዮጵያን ዐብዮት ለመጠበቅ ከውጭ የመጣ "ተራማጅ" ነው። የሻለቃነት ማዕርግ አለው። ስሙ ሻለቃ ፔርኖ ይባላል፤ ሻለቃ ፔርኖ በጮሌነቱና በደፋርነቱ በሩሲያውያን ከፍተኛ አማካሪዎች የታወቀና፣ አንጐላ በነበረ በትም ዘመን በወሰዳቸው የጨካኝነት ግዳጆቹ ዝና ያተረፈ በመ ሆኑ፣ በሹመት መልክ ተዛውሮ አዲስ አበባ ከመጣ ዐመታት አልፈውታል። የመናገሻይቱን የአዲስ አበባ ከተማ ፀጥታና ዲስ ፕሊን የማስከበር ኃላፊነት የተሰጠው፣ ከበላይ ሊቆምበር ቤንጂስቶ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት በፈለገው ጊዜ የማድረግ መብ ትና ሥልጣን ያለው የውስጥ ባለሟል ነው። ለከተማይቱ ፈላጭ ቆራጭ ሆኖ፣ ያሻውን ሁሉ ሲያደርግ የራሽያ ከፍተኛ አማካሪዎች ሁሉ ሳይቀጥሩ፣ የውሳኔው ተገዥዎች ናቸው። በቀዩ ሽብር ጊዜ ባስገደለው ታጋዮች ቁጥር ብዛት ከበላይ አካል ሊቆምበርና ከብሬዥነቭ እንዲሁም ከሀገሩ ልዩ ልዩ ሽልማቶች ተበርክተውለታል። በየቀበሌው የግሉ ወኪሎች አሉት። በእበላይነት ያሠፈሠፉትን ምድረ ካድሬዎችና የቀበሌ ሹሞች እንደፈለገው ያዛቸዋል። ይነዳቸዋል!

አንዳንድ የዋሐን ያዲስ አበባ ነዋሪዎች ብሶታቸውን ሊያቃልል የሚችል እየመሰላቸው፣ በደላቸውን ለማመልከት





በሔዱ ቍጥር፣ " አድኃሪ ነህ ይበልህ! አቆርቋዥ ነህ፣ መደብ ደቡ ደግ አርጓል! " የሚል መልስ በመስጠት፣ በጥፊ መል ውሎ ይመልሳቸዋል። መጠጥ ቤት ገብቶ ወይም ከሱቅ እቃ ገዝቶ፣ ዋጋውን ቢሞት አይከፍልም። ደፍረው የሚጠይቁት ሲኖሩ " ሔዳችሁ ቤንጂስቶን ጠይቁ! " የሚል በትዕቢት የተወጠረ መልስ ይሰጣቸዋል። ትክክል አለመሆኑን ለመግለጽ የሚሞክር ሰው ባገኘ ቍጥር፣ ቢፈልግ ያስደበድበዋል፣ ከፈለ ገም ላልተወሰነ ጊዜ ያሣስረዋል። ተናዶ ዐይኑን ያፈጠጠ እንደሆነ፣ ዘሎ ለመዋጥ ያደባ አዞ ምሥጋን ይንሣው። ምን አለፋችሁ፣ ያላመረረውና ያላለቀሰበት፣ ድፍን ያዲስ አበባ ሰው አይገኛም። በተለይም ያዲስ አበባ ሴቶች፣ በተለይም ያዲስ አበባ ልጃገረዶች--- በሥጋቸው ብቻ ሳይሆን፣ በነፍሳቸው ጭምር ነው ያላገጠባቸው።

ሻለቃ ፔርኖ ፣ የክልስነት መልክ ያለው የስፓንሽ ዲቃላ ነው። ጥሩ ስፓንኛና ፈረንሳይኛ እንግሊዝኛ ካገሩ ቋንቋ ጋር መናገር ይችላል። ባገሩ፣ የኤለመንተሪ ትምህርት የጨረሰና በዘመድ ረዳትነት ሥልጣን አግኝቶ፣ ወደ ውጭ የተጓዘ ነው። አንጐላ ውስጥ በነበረበት ጊዜ ብዙ የመግደል ሙከራዎች ተደርጐበት ነበር። አዲስ አበባም ቢሆን፣ ሦስት ጊዜ ተሞክሮበት ለጥቂት አምልጧል። ለጥበቃ እንዲያመች ተብሎ፣ አራት ቦታዎች እየተዘዋወረ እንዲኖር ጥሩ ጥሩ ቪላዎች ተሰጥተውታል። ዋና መቀመጫ ሔድኳርተሩ ስላይ ኛው ቤተ-መንግሥት ጐረቤት የሆነው ከሒልተን ሆቴል ነው። የፈለገውን ማድረግ እንዲችል፣ ሊቆምበር ነኝ ባዩ ፣ ልዩ ሥልጣን ሰጥቶታል። በዚህም ሥልጣኑ፣ ባዲሳቦች ላይ ከሽንት አልፎ አርቶባቸዋል። በእምቢታ ያስቸገሩትን ቆነጃጅት

ሲገል፣ ቀጥሩ ከመቶ ይጠጋል። ሊቋቋሙት የሞከሩትን ሁሉ " አድኃሪ ኤለመንት ነው! " እያለ እንዳሻው መንጥሯል። በዚሁ ሰበቡ አማካይነት በመጠቀም፣ በየእሥር ቤቱ የሚያማ ቅቃቸው የቆነጃጅት ባሎች ቀጥሩ አይታወቅም። ምን አለፋ ችሁ፤ በአዲስ አበባ ውስጥ፤ ከበላይ አካል ልዩ ሹሞች ይልቅ በጣም የሚፈራው፣ ሻለቃ ፔርኖ ነው።

እንደውም አንድ ቀን፣ ሁለቱም በለመዷት ሴት ተጋ ጭተው፣ ሻለቃ ፔርኖ፣ ሊቆምበር ን " ክብርህን ብትጠብቅ ይሻላል! የሥልጣኑ ኃይል ቀልፍ ያለው በኔ እጅ ነው! ብንከባበር ይሻላል! " የሚል ማስጠንቀቂያ ከሰጠው ወዲህ፣ ባገኘው ቀጥር ሲሸቆጠቆጠለት ሌላ ነው አሉ። ከቶውንም የቅርብ ጊዜው አነጋገሩ " ሒድና ለቤንጂስቶ ንገር! እኔ የምፈራው መሰለህ! " ሆኗል፣ የልቡን ሠርቶ የሚያማርርበት ሰው ባጋጠመው ቀጥር ነው ይህን ማለት የጀመረው፤ ባላም ባራስ ግራ ዐይኑና ግራ ጆሮውን በጐራዴያቸው ከከሉት ወዲህ፤ ይህ የደረሰበት አደጋ፣ ለአብዮታዊነት ግዳጁ እንደ ከፍተኛ መሥዋዕትነት ተቆጥሮለት፤ ከብሬዥኘነቭ በመሪው በኩል በተቀዳጀው ታላቅ የኒሻን ሽልማትና፣ ባገኘው የኰሎኔልነት ማዕርግ ነው። የደረሰበትንም ከፍተኛ የአካል ጕድለት ለመታ ከም፤ ልዩ የቀዶ ጥገና ስፔሲያሊጥቶች በብሬዥኘነቭ ታዘውለት፤ ለሦስት ወራት ያህል በሞስኮ የታወቀ ሆስፒታል ሲታከም ቆይቷል። ሐኪሞቹም፣ የባላምባራስ ስል ጐራዴ፣ በስላች የጐረዳቸውን ግራ ዐይንና ግራ ጆሮ መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል ብዙ ጥረት ቢያደርጉም ሊሳካላቸው ባለመቻሉ፣ በፍ የል ወጠጤ አዋጅ በዚያን ሰሞን ከተረሸነ ያንድ ተጋይ ሬሳ ላይ የተወሰደ፣ ትኩስ ዐይንና ጆሮ በቀዶ ጥገና ጥበብ ተተክ





ቶለት ከዳነ በኋላ፣ ሀገሬ ለወራት ጊዜ ያህል ረፍት ሲያረግ ቆይቶ አዲስ አበባ ተመልሷል። ሥጋው ከሥጋ፣ ነርቡ ከነርቭ ኅብሩ ከኅብር፣ መጠኑ ከመጠን ሊመሳሰልለት ባለመቻሉ፣ በቀዶ ጥገ ናው አማካይነት የተተካለትን የታጋይ ጆሮና ዐይን ለመሸፈን፣ ልዩ ባርኔጣና ልዩ መነፅር ተሠርቶለት፣ መነፅሩ ገት ሮና ባርኔ ጣውን ቀሥሮ፣ መላ አዲስ አበባን፣ ከንጦጦ እስከ ቦሌ፤ ከገፈርሳ እስከ ኰተቤ፣ ከመቸውም በበለጠ ፍጥነት ሲያስስ ይውላል። የሚፈጽመውም ግፍና ጭከና፣ ከወትሮው ከሮ፣ እጥፍ ድርብ ሆኗል። ዛሬ በአዲስ አበባ፣ የኰሎኔል ፔርኖ ን የግፍ ፅዋ፣ መጠኑ ይለያይ እንጅ፣ ያልቀመሰው ሰው አይገኝም። አዲስ አበባም፣ እንደፈለገው የሚምነሸነሽባት አዲስ አበባው ሆናለታለች። ማን አለብኝ ብሎ፣ ልቡ ያበጠበትና ደረቱ የተነፋበት ደንቆሮ የባዕድ ወታደር፣ በዚያ ክቡር ሕዝብ መካከል ተገኝቶ፤ ተከብሮ ለዘመናት ያልኖረውን ያህል፣ ብሔ ራዊ ክብሩን በመድፈር፣ ያልዘለለው፣ የባሕል ዕድሞ፣ ያልተራ መደው፤ የኢኮኖሚ ግንብ፣ ያልጣሰው ሰብአዊ የፍትህ፣ የመ ብት፤ የነፃነት፣ የእኩልነት አጥር አይገኝም። ይህን ማየት አንችልም ያሉ ኢትዮጵያውያን ልጆቿ ታርደዋል ወይም ተሰደ ዋል። ሁሉ ያልፋል፣ በማለት ተስፋ ያረጉም እየተረገጡ አሉ። ይህን ብሔራዊ ውርደት ለመቋቋምም ጥቂቶች ጫካ ገብተ ዋል። አልተቋጨም እንጅ፣ በከተማም ሆነ፣ በገጠር፣ ፔርኖ ና አምላኪዎቹን ባፍ ጢም ለመድፋት፤ ሁልጊዜ ትግላዊ ሙከራ እንዳደረጉ ናቸው። አንድ ቀንም በቀዶ ጥገና የተተካለትን፣ የታጋይ ዐይንና ጆሮ ነፃ ለማውጣት ብቻ ሳይሆን፣ እንዲያ በኢትዮጵያውያን ጭቁን ሕዝቦች ላይ እንዲጫወት የፈቀ ደለትን የፋሽስት ሥርዓት፤ ከነቁንጮው ጭምር፣ ገነጣጥሎ እንደ ሚጥል፣ ታሪክ የሚከስትለት የታጋዩ ኢትዮጵያዊ የትግል

እውነት ነው ። ይህ ታሪካዊ ክሥተት ነገ የምናየው ድላዊ ሐቅ ነው ።-----

ባላምባራስ ገብርዬ፣ ከገዛ ደጃቸው ላይ፣ በአረመኔው ጥይት፣ በግፍ ተደብድበው፣ ለሞት ሲያጣጥሩ በነበሩበት ወቅት፣ አንድ ከፍተኛ ኃይለ ቃል ተናግረዋል ። ይኸውም የሚከተለው ነበር፣-

" ያለፉት ኢትዮጵያውያን አባቶቼ፣ ያለፈው ትውልድ ያገሬ ሕዝቦች፣ ይህን መሳይ ባዕዳን ወለድ ውርደት እንዳይደ ርስባቸው በመጠንቀቅ፣ ባላቸው አቅም ሁሉ፣ በደማቸውና ባጥንታቸው ሲከላከሉ ኖረዋል ። ዮሐንስ በመተማ፣ ቴዎድ ሮስ፣ በመቅደላ፣ ምኒልክ በአድዋ የተጋደሉት፣ ይህ የሀገራችን ብሔራዊ ክብር እንዳይጣስ ነበር ። የሕዝባችን ብሔራዊ ባሕል እንዳይደፈር ነበር ። አዲሱ ትውልድ፣ ዘውድ በመጫናቸው ብቻ ሊያከቸለችላቸው ቢቃጣም፣ ሀገራቸውንና ሕዝባቸውን ከብሔራዊ ክብሩና ከብሔራዊ ባሕሉ ጋር፣ ታሪክ ባቀረበ ላቸው ግዴታ መሠረት፣ በነበሩበት ዘመን አንፃር፣ እስከዛሬ ጠብቆ በማቆየት፣ የባዕዳንን ወረራ ሁሉ በየአቅጣጫው ለማጨ ናገፍ፣ የከፈሉትን መሥዋዕትነትና የፈፀሙትን መራራ ተጋድሎ ታሪክ ሊፍቀው አይችልም ።ታጋይ ሕዝብም ከጐናቸው ነበር ። ዛሬ፣ የዓለም ታናናሽ ሀገሮች፣ ሦስተኛ ምርጫ ባጡበት ዘመን፣ ለምዕራብ ወይም ለምሥራቅ ኃያላን በዝባዥ መንግ ሥታት፣ በጥገኝነት መንበርከክ፣ ግዴታ መስሎ ቢታይም፣ ይህ የወረርሽኝ ግዴታ፣ ለጀግኖቹ ኢትዮጵያውያን ዕድል ፈንታ አልነበረም ። ይሁን እንጅ እድሜ ደጉ ሁሉን አሳየን ። በአንድ ትውልድ እድሜ ውስጥ፣ እኒህ በዝባዥ መንግሥታት በእር





ዳታና በሥልጣኔ እድገት አማካሪነት ስም፣ በሀገራችን ውስጥ ሠርገው በመግባት፣ ወኪል፣ መሪዎቻቸውን በመንግሥት ሥልጣን ላይ አስቀምጠው፣ የሕዝባችንን ላብና ደም እንደ ጥገት ላም በፈራረቃ ሲያልቡት አየን ። ገና አንዱ ጅብ ጓዙን ጠቅሎ በፊት በር ሊወጣ ሲዘጋጅ ሳለ፣ ሌላው ጅብ በጓሮ በር ሲገባ ተመለከትን ። ዛሬ ሀገሬ ከሦስት ሺ ዘመናት በኋላ፣ የደርቡሾችን ምጣት ሳይቀር ያልተቋቋመችውን ያህል፣ በዐብ ዮት ስም ተደፈረች ። የውስጧን ብሔራዊ ችግሮችና ድክመ ቶች ልጆቿ፣ ራሳቸው በራሳቸው፣ በውስጣዊ ትግል፣ ከጊዜ በኋላ ይወጡት ነበር ። ይህንንም፣ የራሳችንን ችግር በራስ የመ ወጣት እውነታ፣ የባዕዳኑ ጊዜያዊ ወረራ ከመቸውም ይልቅ፣ ሓቅነቱን እያጐላ አምጥቶታል ።

ይህ የዛሬው ትውልድ፣ የተጣሰውን ብሔራዊ አጥር ለማስከበር፣ ከመቸውም የበለጠ ግዴታና ኃላፊነት አለበት ። የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ፣ ለባዕዳን ቀርቶ፣ ለሀገሩ ጨቋኝ መሪዎች እንኳ እንደማይተኛ አውቃለሁ ። ታሪክም ደጋግሞ መሥክሯል ። ያገሬ ሕዝብ የትግል ባሕርዩ እንደኑግ፣ እንደሠሊጥ ያለ ነው ። በወቀጡት መጠን፣ የድል ቅባት ያመጣል ። ምንጊዜም ቢሆን ይሸነፋል ብዬ አላምንም ። ይህን እምነቴንም አጥንቴ ሣይቀር ከሞትኩ በኋላም ይመሠክራል ። የጊዜውን መርዘምና ማጠር አላውቅም እንጅ፣ የኋላ ኋላ፣ ይህ ዛሬ፣ ባዕዳን ከብሔራዊ ጭፍሮቻቸው ጋር የጣሱትንና የመነቃቀሩትን ብሔራዊ ክብር፣ ነፃነት፣ መብት፣ ፍትህ፣ ጭቁኑ ያገሬ ሕዝብ፣ ባጥንቱ ሽከላነትና በደሙ ሲሚንቶነት እንድገና ገንብቶ እንደሚያስከብረው፣ ሕያው ትንቢቴ ነው ። ብሬዥኔቭና ጭራዎቹ፣ በዐብዮታውያን ወታደርነት ስም

የላኳቸውም አለሌ ኰርማዎቻቸው፣ በጋለ የሀገሬ ታጋዮች ብረት፣ የሚኰላሹበት ጊዜ ሩቅ አይደለም። ያ ልጅ የተናገረ ውም ትክክል ነው። ሕዝባችን ሥርዓቱን በመቃወም ማመፅ ይኖርበታል። ብሔራዊ አጥሩ ተጥሶበት በሶሻሊዝም ስም ሲበዘበዝ የኖረው የምዝብር ሕዝብ፣ የወጠነውን የትግል ጅምር ተማሳሳይ ችግር የደረሰባቸው ኢትዮጵያውያን ያካት ቱታል እንጅ፣ የተጣሰው አጥር እንደተመነቃቀረ አይሰነብትም።


--- ስትሞቂኝ የኖርሽ ያገሬ ፀሐይ፣ ብርሃንሽን ስትለ ግሽልኝ የኖርሽ የሀገሬ ዥንበር፣ አዝርዕቱንና ዕፀዋቱን ስታበረክችኝ የኖርሽ ያገሬ ምድር፣ ስተነፍስህ የኖርኩ ያገሬ ዐየር፣ ስጠጣህ የኖርኩ ያገሬ ውሃ---- ለባዳን ወራሪዎችና ለሀገራችን ፋሽስቶች፣ የተፈጥሮ ልግሥናችሁን እንዳትገብ ሩላቸው ተስፋዬም እምነቴም ነው።" የተጣሰው አጥር፣ " በቅርብ ጊዜ ውስጥ፣ በጭቁን ወገኖቼ አጥንትና ደም ከአዲስ ነፃነቱ፣ ዲሞክራሲው፣ ፍትሁ፣ መብቱ እኩልነቱ፣ ይዞታዊ መልኩ ጋር ይገነባል። የብሔራዊ ክብራችንን አጥር ለመድፈ ርና ለመጣስ ምክንያት የሆኑ ሁሉ፣ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ሕዝ ባዊ ፍርዳቸውን ያገኛሉ!" የባላምባራስ ኑዛዜ መሆኑ ነው።

" ወጋ ወጋ አድርጐ እዚያም እዚህ ምድር!
የኔም ሆነ ያንቺ ግዴታኮ ነበር!
ማንም የጣሰውን እንደገና ማጠር! "

ተፈጸመ



# ሞኝ ባገኝ





ምድረ በዳ-ወለድ፣ ትል ይሉ ወይ ትንኝ፣
ስንቱን ወገን ቀጨ፣ አዲስ ሕይወት ሲመኝ!?
ስንት ለም እያለ፣ የሚታረስ መሬት፣
ለማራቅ ተብሎ፣ ታጋይ ትኩስ ወጣት፣
ሲሣይ ሆኖ ቀረ፣ ለበረሐ ነፍሳት!

(የጠፍ. ቁ.5)

# መንደርደሪያ

እበላ ባይ የገዥ መደብ አሠፍስፎ በሚቧግትበት ወቅት፣ የብዙዎች ንፁሐን ሕዝባዊ ሕይወት በጥቃቅን ምክንያቶች መነሻነት ይጠፋል። የሕዝብ ሕይወት፣ በቀላሉ ቍጥጥር ሥር ሊውሉ በሚችሉ ደዌያት ይበከላል። ግቡና ዓላማው የራሱን ግላዊ ፍላጐት ለማርካት ብቻ እስከሆነ ድረስ፤የገዥው መደብ፣ ለግል ስሜቱ እርካታ ሲንዘላዘልና፣ ጥንብ እንዳየ አሞራ ጥቅም ባለበት ቦታ ብቻ ሲያንዣብብና ሲያደዘድዝ፤ በመሐሉ " በሥርዓት አስተዳድረዋለሁ " ብሎ ቃል ኪዳን የገባለት የሕዝብ ሕይወት መቅኖ ያጣል። መቅኖ ማጣት ብቻ ሳይሆን፣ የመኖር ዋስትናው እየተናጋ፣ ያለዕድሜው እየተቀጨ ያልቃል። ሕይወትን ያህል የምድራችን ትልቅና ክቡር ፀጋ፣ በማይረቡ ጥቃቅን ምክንያቶች ከማጣት የከፋ፣ ሌላ ምንም ነገር አይኖርም።

የገዥ መደቦች፣ ሆን ብለው የሚፈጥሩአቸው አንዳንድ ረጋ-ሠራሽ ወጥመዶች፣ ለብዙ ሕዝቦች መጥፋት መነሻዎች እንደነበሩ፣ የየጊዜው ታሪክ አሳይቷል። የዘመናችን ፋሽስቶችም በየወቅቱ ያጠመዷቸው የመቅሰፍት ወጥመዶች፣ ምን ያህል አሠቃቂ እንደነበሩ ማሳየት ያደባባዩን እውነት ይበልጥ ለማጉላት ይረዳ ይሆናል እንጅ፣ በማንም ዘንድ የታወቀ ነው። ሆኖም፣ ለዝክረ-ነገር መዝግቦ ማቆየቱ፣ መጭውን ትውልድ ከመሰል ሥቃይ ለማዳን ማንጠንቀቂያ እንዲሆንና " እንዳይ ሞኝም ይረዳዋል " ተብሎ ይታመናል።

ይህ ሐተታዊ መጣጥፍ ባቀራረቡ ክልብ ወለድ ታሪክ

ይለያል። ካጭር ልብ ወለድ፣ ለየት ባለ መልክ በጣልቃነት እዚህ መቅረቡ፣ አንባብያንን በባሕርያት ትረካ ላለማሰልቸት ተብሎ ነው። ጽሑፉ በተናጠል የሚያጤኑት መሪ ባሕርይ የለውም። አንባብያን ይህን ነቁጥ አስመልክተው እንዲያነቡት ይጠየቃሉ። ይህን ዐይነት አፃፃፍ ካጫጭር ታሪኮች መካከል ጣልቃ ማስገባቱ፣ ሌላው ምክንያት ደግሞ አንድን ትንግርት በሌላም ያፃፃፍ መልክ ማቅረብ እንደሚቻል ለማሳየትና ባንድ ዐይነት ጽሑፋዊ አቀራረብ ብቻ ላለማሰልቸት ሲባል ነው።





# ሞኝ ባገኝ

"አጥፍቼው ልጠፋ ከነቃም ሊያጠፉኝ
ደሙን ተዋህጄ ጉልጥምቱን ልል ሙጥኝ
በክሥተቱ ዝፍኩ ለመኖር ካልበጡኝ
ብልጡማ አያስጠጋም ምናልባት ሞኝ ባገኝ! -----"

ቀትር ቀን ላይ ነው። ዝምበር ሙሉ ፀዳሏን ፈንጥቃለች። ለምልክት ያህል እንኳ፣ ከሀዋ ደጃፍ ላይ ደመና አይታይም። ደረቱን ገልብጦ ለሰጠው ያዲስ አበባ ከተማ ምድር፣ በፍፁም ለጋሥነት ያቺ ፀሐይ ስጦታዋን ስታበረክት፣ ያ ፀሓያማ ቀን የመጀመርያ ቀን ይመስላል። ጉብሎችና ኰረዶች በስሪኳርተር መኪና ላይ ተጭነው በማሽንገን ተከበዋል። ቍጥራቸው ከአስር በላይ ይሆናል - መኪናዎቹ! የሚያሳዝኑ ዐይኖች፣ በሌሎች ያጐረጡ ዐይኖች ይገለመጣሉ። ግማሹ ልጁን፣ ግማሹ ወንድሙንና እህቱን፣ የተቀረውም የዘመዱንና ባልንጀራውን ለመሸኘት፣ ካራተኛ ክፍለ ጦር ደጃፍ ላይ ጢም ብሏል። በስሪኳርተር መኪናዎች ላይ ተጭነው የነበሩ ወጣቶች ሁኔታ፣ ተመልካቹን ሁሉ በማሳዘን ላይ እንዳለ፣ ይግረማችሁ ብሎ፣ ወደ ሀምሳ የሚጠጋ የማክ ትሬንታ ቍጥራቸው ይህን ያህላል ብሎ ለመገመት የሚያስቸግር የወጣቶች መዓት ጭኖ ካልተወቀሥፍራ እየገሠገሠ መጥቶ ካራተኛ ክፍለ ጦር በር ላይ ተደረደረ። የነዚህ ሁሉ ወጣቶች መነሻ ስፍራ ባይታወቅም፣ ለተወ

ሰኑ ዐመታት እስር ቤት የማቀቁ ለመሆናቸው መልካቸው ያስረ
ዳል ። ፊታቸው ፣ ሆነ ብለው ጭስ ላይ የሠቀሉት ብቅል ይመስ
ላል ። ፍፁም ጥቀርሻ ሆነዋል ። ያካል ሥጋቸው አልቆ አጥን
ታቸው ብቻ እርቃኑን ቀርቷል ። የዓፅረ ሞት ምስል ይመስ
ላሉ ። በገፅ አጥንቶቻቸው መካከል ጨርሰው ያልጠፉ ዐይኖ
ቻቸው ፣ ረዳት ጉልበት የሚመኙ ይመስል ፣ ክብልል ክብልል
ይላሉ ። ሽፋሽፍቶአቸውና ቅንድቦቻቸው ፣ ለምልክት ያህል
እንኳ ከቦታቸው ላይ አይታዩም ። ጆሮዎቻቸውና አፍንጫ
ዎቻቸው ቢሆኑም ለወጉ ያህል ጉች ጉች አሉ እንጅ ፣ ጎል
ተው አይታዩም ። መከራና ሥቃይ ያንገላቱዋቸው እነዚህ ወጣ
ቶች ፣ በዚያን ዕለት አራተኛ ክፍለ ጦር እንዲመጡ የተደረ
ገው ፣ በሦስተኛው የናት ሀገር ጥሪ- " በአረንጓዴው የልማት
ዘመቻ " - መሠረት ፣ ገጠር ለማልማት እንዲካፈሉ ተወስኖ ፣
ለሥምሪቱ እንዲዘጋጁ ታስቦ ነው ።

ቀደም ሲል ፣ በአሥር ስሪኳርተር መኪናዎች ተጭ
ነው ፣ ከክፍለ ጦሩ ግቢ ውስጥ ሠፍረው የነበሩት ወጣቶች ግን
በቀበሌዎችና ሌሎች ድርጅቶች አማካይነት ተመንጥረው የታ
ፈሱ ፣ ተማሪዎች ፣ ሥራ አጦች ፣ ሴትኛ አዳሪዎች ፣ ረዳት የለሽ
ወገኖች ናቸው ። የልጆቻቸውን ለዚህ ዘመቻ መታፈስ የሰሙ
ወላጆችና ዘመዶች ፣ እንባቸውን እያነቡ ፣ ከውጭ ሆነው ለዘ
መቻ የሚነሱበትን ሰዓት ለማየት አኰብኩበው ይጠባበቃሉ ።
አብዛኛዎቹም እናቶች ነበሩ ። የዘመኑ መዓት የጠበሳቸው!!

አንዳንድ ሁኔታው ያላስቻላቸው እናቶች ፣ ከክፍለ ጦር
ደጃፍ ላይ ተምበርክከው ፣ የየግል ሙሾአቸውን መደርደር
ጀምረዋል ።በዚያ ቀውጢ ዘመን ፣ እንኳንስ ተለይተዋቸው ሩቅ
ሀገር መሔዳቸው ይቅርና ፣ እዚያው እጉያቸው ተደብቀው የነ





በሩ ልጆቻቸው ፣ በየምክንያቱ እየተወሰዱ መረሸናቸውና ፣ አን
ዳንዶቹም ድንገት ወጥተው ፣ እውስጥ ይግቡ ሰምጥ የት እንደ
ደረሱ ሳይታወቅ የውሃ ሽታ ሆነው መቅረታቸው ፣ እናቶችን
እየታወሳቸው ነበር ። ለነዚያ ሩቅ ሀገር ተወስደው ፣ ዱር ለመ
መንጠር ፣ በረሐ ለማልማት ያስገደዷቸው ምስኪን ልጆቻ
ቸው ፣ የሚገጥማቸው ሥቃይና መከራ እየታያቸው ነበር የሚያ
ለቅሱት ። ያልቅሱ እንጅ ፣ ልቅሶአቸውን ቁምነገሬ ያለው የወታ
ደር ባለሥልጣን አልነበረም ። እንዲውም እዚያ ክፍለ ጦር
በር ላይ ተሰብስበው ፣ በልጆቻቸው ላይ መጥፎ እድል የሚያሟ
ርቱ እናቶችን ሁሉ ፣ በደረጃቸው ፀረ-ዐብዮተኞች ናቸው ተብ
ለው ፣ ልጆቻቸው ለሞትም ይሁን ለሕይወት ፣ በወጉ ሳይሸኙ ፣
በቅፅበት ከዚያ አካባቢ እንዲባረሩ ፣ አንድ ዩኒት ጦር ታዘዘ ።

ከዚያማ ምኑ ይነገራል ? የታዘዘው ዩኒት ፣ ደካማዋን
እናት ከብርቱዋ እናት አልመረጠም ። ዝም ብሎ መደዳውን
በሠደፍ መጥረጊያና በሳንጃ መሠቅሠቂያ ፣ እየጠቀጠቀ ጠረጋ
ቸው ። የዚያ የታዘዘ ዩኒት ጦር የማምሻው ተግባሩ ፣ እነዚያን
መከረኞች እናቶች የማጉላላትና የማንገላታት ሥምሪት እንደ
ነበር ፣ ካካባቢው የነበረ ወጭ ወራጅ መንገደኛ ሳይቀር ተመለ
ከተ ። በዚያ ዕለት ምሽት ፣ መሿለኪያ የተባለው ሥፍራ ፣ የሽብ
ርና የግርግር ቦታ ሆኖ ከወትሮው ብሶበት ነበር ። ደም የተለቀለ
ቀው የናቶች እንባ እንደ ጐርፍ ፈሠሠ ። የድሮ የራሔል የእ
ናትነት ታሪካዊ ዋይታና ስለልጆቿም ስትል የመሠቀቿ ትራዠ
ዲያዊ ድራማ ፣ በዚያ ምሽቱ ያራተኛ ክፍለጦር ደጃፍ መድ
ረክ ላይ ባዲስ መልክ ቀርቦ ታየ ። ተባራሪ ተመልካችም ፣ በኣን
ክሮ ሳይሆን ፣ በሀዘንና በብስጭት ተመለከተው ። ጥይት ባይተ
ኰሱባቸውም ፣ በመከረኞቹ እናቶች ላይ የሠደፍና የሣንጃ እሩ

ምታ ወርዶባቸዋል። በዚያ ምሽት፣ በዚያ ሥፍራ የተገኙ መከረኛ እናት ሁሉ፣ አንድም ቆስላለች፣ አንድም ያበጠ ዐካል አትርፋለች። ከዱላው ፋሽስታዊነት የተነሳሣ መላወስ ያቃታ ቸው፣ በወሣንሳ እየተነሱ፣ በአንቡላንስ የተወሰዱት ቍጥራ ቸው ትንሽ አልነበረም። ከማንጃው አረማዊነት የተነሣ ዐይና ቸው ሳይቀር የቈሰሉ እናቶች ብዛታቸው አንስተኛ አልነበረም።

በዚያ ዐይነት የምንጠራ ሥምሪት፣ የታዘዘው ዩኒት ጦር፣ የክፍለ ጦሩን ደጃፍ ካፀዳ በኋላ፣ የዕለቷ ዠንበር ጠልቃ፣ ምሽቱ ጨለምለም ሲል፣ ለዘመቻው የተዘጋጁት የታ ፈሱና በእፃለር ቤት የቆዩ ወጣቶች መንቀሳቀስ ጀመሩ። የት እንደሚወሰዱና ለምንስ እንደሚጓዙ የማያውቁ፣ እነዚያ አሳዛኝ ወጣቶች፣ ዝምታና ፀጥታ ውጧቸዋል። ብቻ አልፎ አልፎ አን ዳንድ ወጣት፣ ድምፁን ከፍ እያረገ፣ ደኅና ክረሙ! እኛ ወደ እልቂታችን መሔዳችን ነው! ይል ነበር። ከናቶች ዋይታ በስተ ቀር፣ ሊያስጥል የሞከረ ወንድ አልነበረም።

ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ገደማ ላይ፣ እነዚያ ስሪ ኳርተ ሮችና የማክ ትሬንታዎች፣ የሒትለርን የሥንቅ ማጓጓዥ ይመ ስል፣ ተያይዘው ፣ በዐብዮት አደባባይ፣ በአስመራ መንገድ፣ በየካ፣ በኰተቤ፣ በላምበረት አድርገው ነጐዱ። በላዮቻቸው ላይ እንደሰርዲን ታምቀው የተጫኑት የሚያሳዝኑ ዘማቾችም፣ የሌሊቱን ቍርና የቀኑን ሐሩር መከላከያ ሳይሰጣቸው፣ የደረቀ ሞፎ እየጋጡ፣ ካሥር ቀናት ጉዞ በኋላ፣ እንዲያለሙ ከተወሰ ነላቸው በረሐ ደረሱ። ለምን ያንን በረሐ ለማልማት እንደ ተወሰነ፣ ባይገለፅላቸውም፣ ሰው የሌለባቸው፣ ደጋና ወይና ደጋ ሰፋፊ መሬቶችን እየዩ እንደመጡ፣ በጉዞአቸው ላይ ተመ ልክተዋል።





የሠፈሩበት በረሐ፣ ከዚህ በፊት የሰው ልጅ እግሩን ያልረገጠበት ምድረ በዳ ነው። የሱዳን ጠረፍ በሩቅ ይታያል። ከሁመራ አልፎ፣ አብደራፊን ተሻግሮ ጭው ካለው በረሐ ላይ ነው። ከዚህ ቀደም ሰው ያልረገጠውና ያልሠፈረበትም በመ ሆኑ ሥፍራው " ስም የለሽ " ነው። ከዚህ በረሐ ዳርቻ ላይ አንድ ከፍተኛ ዱር አለ። ከሠፈራው ቦታ ወደዚያ ዱር ለመድ ረስ አንደ ቀን ይፈጃል። የበረሀው መለስተኛ የውሃ ምንጭ እስከተገኘበት ቅርብ ጊዜ ድረስ፣ የሠፈረው የልማት ሠራዊት እየተቆነነ ሚሰጠውን ወሃ የሚያገኘው፣ ከዚያ ዱር ውስጥ ከምትገኝ አንዲት ትንሽ ምንጭ ነበር። ምድብ ሥራቸው ውሃ ማመላለስ የነበሩት ዘማቾች፣ ፣ በየሦስት ቀኑ ውስጥ፣ አንድ ቀን ሙሉ መጓዝ ነበረባቸው።

መቸም አንድ ያንን መሰል ትልቅ የልማት ዘመቻ እቅድ ሲታሰብ፣ ማንም እንደሚያውቀውና እንድሚያምንበት ሁሉ፣ በተቀዳሚ መዘጋጀት ያለባቸው ብዙ ተግባሮች፣ ፕሮጀክቶች፣ መሠናዶዎች፣ አሉ። ቢያንስ ቢያንስ፣ ጊዜያዊ መጠለያ ቤቶች የመጀመርያ እርዳታ መስጫ ክሊኒኮች፣ ዶክቶሮችም ባይገኙ ድሬሰሮች ሥንቅና በተለይም ውሃና አስፈላጊ ልብሶች እንዲኖሩ ግዴታ ነው። እነዚህ ከሞላ ጐደል መገኘት አለባቸው። በተ ጨማሪም ፣ ለዘመቻ መሥፈሪያ የሚመረጠው ሥፍራ፣ አስቀ ድሞ በተለያዩ ባለሙያዎችና ኤክስፐርቶች ተጠንቶ፣ አመችነቱ መረጋገጥ አለበት። ሥፍራው ጤነኛ አከባቢ መሆኑ ብቻ እንኳ አይበቃም። መጓጓዣ ሊገባው ይችላል ወይ? ሊመረት የሚችለውን ምርት የሚጠናወት ያካባቢ አውሬ፣ ተውሣክ፣ ፀረ

ምርት ነፍሳት አሉ ወይ? ለሠፈረው ሠራዊትስ፣ አካባቢው የጤንነት ዋስትና ሊኖረው ይችላል ወይ? ለማልማት የታቀዱትን አዝርዕቶች ያካባቢው አፈር ይቀበለው፣ ይስማማው፣ ይዋሐደው ይሆን ወይ? የእነዚህ ጥያቄዎች መልሶች ወሣኞች ናቸው።

ልማትን ያህል ትልቅ ፕሮጀክት አቅዶ፣ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን መሠናዳዎች በሚገባ ሳያዘጋጁ፣ ባዶ እጁን ያለ፣ ወጣት የልማት ሠራዊት፣ በግዳጅ ወስዶ ጭው ካለ በረሀ ላይ ማፍሰስ፤ “ልማት ” ከሚለው ክቡር ዓላማና ግብ፣ በይዘትም ሆነ በቅርፅ የተለየ፣ ሌላ ምክንያት ሊኖረው ይችላል። “ ሊበሉት ያሰቡትን እሪያ፣ በገ-ሰማይ ይሉታል “ እንደሚባለው ያለ - ወጣት ተራማጅ አልባ አዲስአበባ ለመፍጠር?

እነዚያ የፈረደባቸው ምስኪን ወጣት የልማት ዘማቾች ከዚያ ምድረ-በዳ ተጥለው፣ አሣራቸውን ያቦኩ፣ ፍዳቸውም ይዝቁ ጀመር። ሌቱ መሽቶ በነጋ ቍጥር፣ ምሕረት በሌለው መሃይምን ካድሬ መጨቅጨቅና መነረት፣ የዘወትር ምሣቸው ሆነ። ምግብ ይሉ ልብስ በሥርዓት አይሰጣቸውም። ከሥራ ድካምና ከጤንነት ጉድለት የተነሣ፣ መሥራት ሲሳናቸው፣ በዐብዮቱ የሚለግሙ አድኃሪዎች እየተባሉ፣ እዚያው በተሠራ ወኀኒ ቤት ተልከው ይማቅቃሉ። ከመድኃኒት ይሉ መድኃኒት፣ ከሐኪም ይሉ ሐኪም ስለሌለ፣ ከጤነኛው ዘማች ይልቅ፣ የሕመምተኛው ቍጥር ይበልጣል። ለወጉ ያህልማ፣ የሚሰጡትን ክኒን ዐይነትና ምንነት በደንብ ለይተው የማያውቁ፣ አምስት የጤና መኰንኖች አሉ። ለዚያውም ክኒናቸው ቢሆን፣ የዘማቹን እጅ ያያሉ።

መጠለያ ተብሎ የተሠራላቸው ቤት ያው እነሱ ከደረሱ በኋላ ያዘጋጁት ጊዜያዊ ማረፍያ ነበር። ከተራ ዳስ አይሻልም።





ጕረቤታቸው ካለው ዱር በሽክም ከመጣ እንጨት የተዋቀረና ግድግዳው ባጋምና ባልታወቁ ቅጠሎች የተሸመጠጠ ሲሆን፣ ጣራው በተጣጣፈ አሮጌ የድንኳን ሸራ የተሸፈነ ነው። ለዚያውም ቢሆን፣ ግማሹን ጣራ ሸራውን አላዳርስ ብሎት፣ የበረሀ ሣር ተረብርቦለታል። የበረሀው ሐሩር ቃጠሎው በሚብስበት ወቅት፣ በሣርና በቅጠል ብቻ የተሸፈነው የጣራው ክፍል፣ ሰደድ እሳት የለኰሱበት ይመስል ቢል ብሎ የነደደበት ወቅት ነበረ። ደግነቱ ያ ወቅት፣ መላው ሠራዊት ለሥራ በሚሠማራበት በቀኑ የሥራ ሰዓት መሆኑ በጀ እንጅ፣ ስንት ዘማች በቃጠሎው በነደደ ነበር።

የዘማቾቹ መጠለያ የተሠራው፣ ከበረሀው መሐል ላይ ስለነበረ ( ለማምለጥ ለሚሞክሩ ዘማቾች እንዳያመች ተዘይዶ ነው!) ቃጠሎው በተነሣ ቍጥር ለማጥፋት በጭራሽ አይሞከርም። በመሆኑም ያ ዳሳቸው ብዙ ጊዜ እየተቃጠለ፣ የሚኖሩት ኋላ ላይ በመጡ ድንኳኖች ውስጥ ነው። ድንኳኑም በበኩሉ ከበረሀው ንዳድና ሐሩር የተነሣ ወበቁና ሙቀቱ አየድርስ ያሰኛል። ትንሽ ቀዝቀዝ ብለው የሚታዩት አንድ ክፍል ወጦቹ ዛኒጋባዎች ናቸው። እነዚህ ዛኒጋባዎች፣ ጣራቸው በደርብ እንጨት ተሠርቶ፣ በአሸዋ የለበሱ በመሆናቸው፣ ውስጣቸው መለስተኛ ቅዝቃዜ ይሰጣሉ። እንዲውም የበረሐው ሪፍሬጀሮች የሚል ስም በዘማቾች ተሰጥቷቸዋል።

ይሁን እንጅ፣ ዕድል አጋጥሞት በውስጣቸው የሚኖር ተራ ዘማች እጅግ በጣም አነስተኛ ነው። እነዚህም ቢሆኑ ከዘመቻው መሪዎች ጋር ልዩ ግኑኝነት ያላቸውና፣ በወራዳ ጠባያቸውም የታወቁ እበላ ባዮች ብቻ ናቸው። እንደግል ቤታቸው ቆጥረው አዘውትው የሚወጡባቸውና የሚገቡባቸው፣ ብዙም

ቀናት የሚዝናኑባቸው፣ ከዘማቾች ሴቶች ውስጥ በመልክ ቀናን
ታቸው ተመርጠው፣ ለካድሬዎቹ የዘመቻው ሹሞች፣ ያለውል
የተዳሩት ቅምጦቻቸው ናቸው። እነሱም ቢሆን የግዴታ "እመ
ቤቶች " የተደረጉ ናቸው። እነዚህ የበረሐ ሴት ወይዘሮዎች፣
ለምድብ ሥራቸው እንኳ፣ ከዚያ ቀዝቃዛ ጐጆዎቻቸው ውስጥ
ብቅ የሚሉት፣ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ነበር። በሥራ ምድባቸውም
ቢሆን፣ እንደሌላው ተራ ዘማች፣ የውሃ ጉድጓዶች ቁፈራ ተግ
ባር፣ የበረሐ ጉርባዎችና ዲቦችን ለርሻ የመስተካከል ከባድ
ሥራ፣ ወይም ከዚያ ሩቅ ዱር ለሁለትና ለሦስተ ቀናት ዕድሜ
ተጉዞ ጫካ መመንጠር ሳይሆን፣ ለዘማቹ ምግብ ማዘጋጀት ብቻ
ስለሆነ፣ ባካባቢው የኑሮ ደረጃ አንፃር፣ በኑሮአቸው የሚንቀ
ባረሩ ቅምጥሎች ናቸው። በአንጻራቸውም በሔዋንነታቸው
ማራኪ ያልሆኑቱ ወገኖች፣ ከወንዶቹ እኩል በሥራ ይማቅ
ቃሉ።

በነዚያ ቀዝቃዛ ዛኒጋባዎች ለመኖር፣ዕድል የተሰጣቸው፣
ሌሎች እበላ ባዮች ደግሞ፣ በወራዳ ተግባራቸው የዘመቻ መሪ
ዎቹን የሚያገለግሉ ቡችሎቻቸው ናቸው። አብዛኛዎቹ በዘማቹ
ሠራዊት ውስጥ በሰላይነት የተሠማሩ፣ ባብሮ ዘመት ጓደኞ
ቻቸው ላይ በወራዳ ተግባራቸው ሹመት ያገኙ ዘማቾች
ናቸው። እነዚህም የውስጥ ጠላቶች፣ በሚፈሩትና በሚጠሉት
ጓደኞቻቸው ላይ ሳይቀር፣ የውሸት ወንጀል እየፈጠሩ፣ " ሲያ
ሳድም አገኘነው! ሊሰደድ ሲዘጋጅ ደረስንበት፣ ፀረ-ዐብዮት
ወሬ ሲነዛ ያዝነው--- " ከሚለው ክስ አንስቶ እስከ " ፍቅረ
ኛዎን ሲያባልግ ሲያጨልግ፣ ሲያባብል ደረስንበት! "
እሚለው ወንጀል ድረስ፣ በብዙዎቹ ጓደኞቻቸው ላይ ደባ
የሚፈፅሙ ናቸው። እነዚህም እበላ ባይ ንዑሣን ሹሞች፣ የሚ





በሉት ምግብና የሚመገቡበት ሥፍራ ሳይቀር፣ ከተራው ዘማች
ሠራዊት የተለየ ነው። ከዋናው ማዕከላዊ የዕድገት መሥሪያ
ቤትና የዘመቻ መምሪያ የሚላክ ማንኛውም ዳረጐትና ገፀ
በረከት ሳይደርሳቸው አያልፍም። ከበላይ አለቆቻቸውም ጋር
አልፎ አልፎ፣ እግር ከጣለው የኮንትሮባንድ ነጋዴ ላይ ከሚወ
ረሰው ልዩ ልዩ እቃ ውስጥና እንደውስኪ ያሉት መጠጦች
ሲወረሱ፣ እነዚህም እበላ ባይ ጥቃቅን ሹማምንት የመጠጣት
ዕድል አላቸው።

በተቀዳሚ ስለ ተራው ዘማች ቤትና ጠቅላላ ኑሮ ሁኔታ
ተነገረ እንጅ፣ የዘመቻውን መሪዎች የበረሐ ኑሮ ሁኔታ ቢነሳ፣
ሌላ ሆኖ እናገኘዋለን። ለመጀመሪያው አንድ ወር ያህል ብቻ
መለስተኛ የቤት ችግር ደርሶባቸው ነበር። ከዚያ በኋላ ግን፣
ከማዕከላዊ መ/ቤት የተላኩ፣ ተጓዥ ቤቶች ስለደረሰላቸው፣ ከከ
ተማ ባላነሰ የኑሮ ሁኔታ ይኖራሉ። ሪፍሪጅረተር ሳይቀር አላ
ቸው። ትኩስ በቆርቆሮ የታሸጉ ምግቦች በየጊዜው ይደርሳ
ቸዋል። ለነገሩ ያህል " የዘመቻ መሪዎች " ተብለው፣ ምድብ
የሥራ ቦታቸው በዚያ በረሐ ይወሰን እንጅ፣ በሥራና በስብሰባ
ምክንያቶች እያሳበቡ፣ አብዛኛወን ጊዜ የሚያሳልፉት፣ ጐንደር
ከተማ ወይም አዲስ አበባ ነው። ቍጥራቸው አይብዛ እንጅ፣
በምሥራቅ ጀርመን መንግሥት የተሰጡ፣ በረሐ ተጓዥ የሆኑ
ልዩ ልዩ ጅፖች አሏቸው። ቅርባቸው ሆነው በአዝማችነት
እንዲመሩአቸው የተመደቡትን ዘማቾች ግን፣ ረስተዋቸዋል።
ምናልባትም ጠቅላላውን የዘማች ሠራዊት የሚገናኙበት ጊዜ
ቢኖር፣ አልፎ አልፎ በየወሩ መጨረሻ ላይ በሚደረገው አጠ
ቃላይ ስብሰባ ጊዜ ብቻ ነው። ለዚያውም ቢሆን፣ አንድ የተለየ
የበላይ ትእዛዝ ካልመጣና፣ ለሠራዊቱ መንገር ካላስፈለገ በስተ

ቀር፣ ይኸንንም የመገናኛ ወቅት እንዳሻቸው ይሠርዙታል።

ዘማቹ ሠራዊት ከዕለታዊ ሥቃዩ ጋር፣ እነሱም እንደ
አዛዦነታቸው ከቅምጥል ኑሮአቸው ጋር እንዳሉ፣ ወራት አለ
ፋና የበጋው ጊዜ አልቆ የክረምት ወቅት ገባ። ያ በረሐ ባለው
የተፈጥሮ የቆየ ልምዱ ክረምትነቱን የመሰከረው፣ ለግማሽ ወር
ያህል፣ ከተራ ማርከፍከፍ አንስቶ ለጥቂት ቀናትም የዶፍ ዝናም
ባወረደበት ወቅት ነው። ያ ለረዥም ወራት፣ በሐሩር ብዛት
ሲጋይ የቆየ የበረሐ አሸዋ እንኳንስ በዝናሙ ውሃ ሊርስ ቀርቶ፣
ጥማቱንም አላረካ። ብቻ በክረምቱ ዝናም የተነሳ፣ ዘማቹም
ሆነ አዝማቹ ከዚያ በፊት በአካባቢው ያላወቁት አንዳች ነገር
ተከሠተ።

ለዐይን ጐልተው የማይታዩ ረቂቃን ነፍሳት ርጥበት
ከተሰማው የበረሐ አሸዋ ላይ እንደ መዓት ፈሉ። ደግነቱ የበረ
ሐውን ሙቀት መቋቋም ባለመቻላቸው ብቻ ይመስላል፣ ፈል
ተው በታዩበት በሦስተኛው ቀን ዶጋመድ ሆነው ይጠፋሉ።
ይሁን እንጅ፣ ከእነዚህ ጥቃቅን የበረሐ ነፍሳት ጥቂቶቹ፣ ለዘ
ማቹ ሠራዊት ውሃ አመላላሽ በሆኑ በቅሎዎችና አህዮች ኰቴ
ስር ተለጥፈው፣ ከጋለው የበረሐ ሐሩር ወደ ቀዝቃዛው
ምንጭ ያለበት ያካባቢው ዱር በመወሰዳቸው፣ ከቅዝቃዜው፣
ነፍስ ዘርተው በሕይወት መትረፋቸው፣ መርዛቸውን ለማጕ
ልበት እስከቻሉበት ወቅት ድረስ በምንጩ አካባቢ በማደጋ
ቸው፣ ለከፍተኛ ወረራ የተዘጋጁ ሆኑ።

የነዚህን መርዘኛ ነፍሳት አደገኛነት፣ ለግዳይ ከመሠማራ
ታቸው በፊት፣ ከዘማቹም ሆነ ከአዝማቹ መካከል፣ የተረዳ አን
ድም ሰው አልነበረም። እነዚህ መርዘኛ ነፍሳት፣ በተቀዳሚ መር
ዘው የከረቡት፣ ወሃ አመላላሽ የነበረች አንዲት በቅሎ ነበር።





ውሃ ለማምጣት ከሔደችበት የዱር ውስጥ ምንጭ አልተመለ
ሰችም። አገልግሎቷን በቅርቧ ሆነው የሚያውቁ፣ የውሃ አመላ
ላሽ ምድብ ሠራተኞች፣ አንድ ሰው የሞተ ያህል በመቍጠር ፣
ለበቅሎዋ አልቅሰው በወግ ቀብረዋታል። ይህ በሆነ ባራተኛው
ቀን ደግሞ ሦስት አህዮች በዚያው በዱሩ ምንጭ አጠገብ፣
ውሀ ለማምጣት እንደሔዱ ሞቱ። ያንጊዜ ነበር የውሃ አመላ
ላሽ ምድብ ሠራተኞች ፍራቻ፣ የተጠነሰሰው።

ከዱሩ እንደተመለሱ፣ ወዲያው በማግስቱ፣ ጉዳዩ ለሚ
መለከተው የዘመቻ ባለሥልጣን ሪፖርት አቀረቡ። ጥቆማ
ቸውን ሰምተው አስቸኳይ ርምጃ እንዲወስዱ የሞከሩ፣ የዘመ
ቻው ባለሥልጣኖች ግን አልነበሩም። ሁኔታው በዚሁ መልኩ
እንዳለ፣ ከውሃ አመላላሽ ምድብ ሠራተኞች ውስጥ አንድ
ዘማች፣ሦስት አገልጋይ ከብቶቻቸው በሞቱ ሣምንት ባልሞላው
ጊዜ ውስጥ፣ ከውሃ ማምጣት ተግባሩ በተመለሰ በሁለተኛው
ቀን፣ ተኝቶ ካደረበት ከኬሻ መኝታው ላይ መነሳት ሳይችል
ቀረ። እነዚያ የጤና መኰንኖች፣ ያለ የሌለ ኪኒን ቢያቅሙትም
መንቀሳቀስ ሳይችል፣ ምን እንደነካው እንኳ መናገር እንዳ
ቃተው፣ በሚያሳዝን ሁኔታ ተሠቃይቶ ሞተ። ይህም ዜና በመ
ላው የዘማች ሠራዊት ውስጥ ተሰማ። ይሁን እንጅ፣ በየምክ
ንያቱ በየጊዜው የሚሞተው ዘማች ቍጥር ትንሽ ስላይደለ፣
ጕዳዩ ብሎ እጅግ የተጨነቀበት አልነበረም።

ያ ዘማች በሞተ በሦስተኛው ቀን አምስት ሌሎች የውሃ
አመላላሽ ምድብ ሠራተኞች ታመው ተኙ። ብዙም ቀን አልቆ
ዩም፣ አምስቱም ዓረፉ። የሠራዊቱን ካምፕ ያናጋው፣ የነዚህ
ዘማቾች ባንድ ጊዜ የመሞታቸው ዜና ነበር። ሁሉንም ሽብር
ለቀቀበት! ይበልጥም የካምፑን ሠራዊት ያነቃነቀው፣ እነዚያን

በድንገት የሞቱ ጓደኞቻቸውን በሕክምና ለመርዳት ሒደው የነበሩት ሁለት የጤና መኰንኖች፣ በጠና መታመም ነው። እነሱም ብዙ አልቆዩ፣ ተከታትለው ሞቱ። ከዚያ በኋላማ፣ ምን ይወራል፤ ቍጥር የለሽ ዘማቾች እንደቅጠል ረገፉ። በዚያ አጋጣሚ የሚይዙትና የሚጥሉት መላቅጥ የጠፋባቸው፣ የዘመቻው ባለሥልጣኖች ስለተደናገራቸው፣ ብዙ ዘማቾች በቡድን በቡድን እየሆኑ፣ ቍጥጥሩ በላላበት አካባቢ እየመረጡ " እግሬ አውጭኝ " አሉ። ዐይናቸው እያየ ከሚሞቱ ይልቅ፣ የሚሒዱበትን ሳያውቁ መጥፋትን መረጡ። በየሁለት ወር ተረኛነት፣ በፈራረቃ የዘመቻውን ሠራዊት በታማኝነት ለመጠበቅ ይመጡ የነበሩትም ከገበሬውና ከባላገሩ የተመረጡ ሚሊሺያ ዘበኞችም በበኩላቸው፣ " ነፍሲ አውጭኝ " እያሉ መፈርጠጥ ሆነ። ይህም ለዘማቹ ሠራዊት የማምለጫ ሽንቁር ስለቀደደለት፣ በየዕለቱ እየጠፉ የሚሰደደውን ዘማች ቍጥር በጥፍ አሳደገው። ለማምለጥ ያልሆነለትም ቢኖር ሞቱን ይጠብቅ ጀመር።

ከሞት ያመለጡት ሦስት የጤና መኰንኖችም የበሽታውን ምንነት አጥንተውና ተረድተው ሳይሆን፣ ለራሳቸው ሕይወት ጭምር በመፍራት፣ በዘመቻው ካምፕ ውስጥ፣ " ተላላፊ በሽታ " መግባቱን በጽሑፍ በመግለጽ፣ ለዘመቻው ባለሥልጣኖች ካምፑ እንዲዘጋና፣ የቀረውም ሠራዊት ባስቸኳይ ወደ ሌላ እንዲዛወር አመለከቱ። ራሳቸውም የዘመቻው ባለሥልጣኖች ለራሳቸው ጤንነት ሲሉ፣ ሌላ የሚወስዱት የተሻለ ምርጫ ስላልነበራቸው፣ በጤና መኰንኖቹ ውሳኔ ተገደው፣ ዘማቹን ሠራዊት ወደ ሌላ ስፍራ ለማንቃንቅ፣አስቸኳይ መልእክት አዲስ አበባ ለሚገኘው ማዕከላዊ የዕ





ድገት መምሪያ መ.ቤት አስተላለፉ። አስፈላጊው ውሳኔና ትዕዛዝ ከዋናው መ.ቤት እስኪመጣ ድረስ፣ የየዕለቱ የሞት ፍጥነት *(death rate)* ከአምስት ወደ አስር አደገ። እንደሠንሠለት ተቆላልፎ የሚርመሰመሰው አጅሬ ቢሮክራሲ፣ "ለበላይ አካል" በሚል ፈሊጡ እየፈተለ ሲያጠነጥንና ሲያስተላልፍ እርስ በርሱ ሲተሻሽ ከረመ። የታች አካል ከበላይ አካል ውሣኔ ለማግኘት አንጋጦ ሲጠብቅ፣ ቀናት ተቃጠሉ።

እንዳጋጣሚም፣ ከአዝማቾቹ አንዱ ተጋደመ። ይህም አስደንጋጭ ሁኔታ በፈጠረው ድፍረት፣ የቀሩት የዘማች ባለሥልጣኖች፣ በረሓውን ለቆ የመውጣት ግላዊ ውሣኔ አስተላልፈው፣ የበላዮቻቸውን ትዕዛዝ ሳይጠብቁ፣ ጉዞውን ባስቸኳይ ጀመሩ። በየመንገዱ እየተንጠባጠበ የቀረውን ሟች ቍጥር ማወቅ ባይቻልም፣ በያቅጣጫው እየጠፋ የተሰደደውን ዘማች መጠን ሳይ ጨምር፣ ሰው ከሚኖርበት ካቅራቢያው መንደር ነፍሱን ይዞ የደረሰው ዘማች፣ ብዛቱ እጅግ በጣም ትንሽ ነበር።

ከዚህ የተላላፊ በሽታ መዓትና ሞት ቀደም ብለው ካምፑን ጥለው ከሸሹት ዘማቾች ውስጥ፣ ሱዳን ውስጥ ገብተው ኖሮ፣ የሰጡት የበረሐ እልቂት ሁኔታ በሬድዮና በጋዜጣ ለዓለም በመሠራጨቱና የማዕከላዊውን መንግሥት የጫፍ ባለሥልጣኖችም ዜናው ያሳሰባቸው በመሆኑ፣ ለሚፈሩት ፕሮፓጋንዳ ብቻ ሲሉ፣ በነፍስ የተረፉትን ዘማቾች ከሚገኙበት ቦታ ላይ፣ በሔሊኮፕተር ሳይቀር ተፈልገው ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ አስቸኳይ ትዕዛዝ አስተላለፉ። ( የዚህን ምንጭ ለኔ የጠቆሙት ከሱዳን ስደተኞች አንዱ ነው።) በዚህም ትዕዛዝ መሠረት፣ በሕይወት የተገኙ የዘመቻው ተራፊዎች ሦስት ቀን

ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አዲስ አበባ ገቡ። በጣም የሚገርመው ግን፣ እነዚህን የበረሐ ስደተኞች፣ ቢቻል ሆስፒታል ገብተው በምርመራ እንዲቆዩ፣ ወይም የተለየ ማረፊያ ተመድቦላቸው የጤንነታቸው ሁኔታ እስኪረጋገጥ ድረስ፣ በሐኪሞች ጥበቃ ስር እንዲቆዩ በማድረግ ፈንታ፣ ገና እንደመጡ ለየቤተሰቦቻቸው እንዲሰጡ መደረጉ ነው። በዚህም ውሣኔአቸው የተነሣ፣ ያ የሰሜን በረሐ የወለደው መርዛማ ነፍሳት ያስገኘው ተላላፊ በሽታ፣ ከሀገሪቱ መናገሻ ከተማ፣ ያላንዳች እክል ከአዲስ አበባ ሰተት ብሎ ገባ። በበረሐው ውስጥ ልጆቿን የጨረሰው አንሶት፣ በሀገሪቱ እንብርት ላይ ተገኝቶ፣ ሕዝቡን ያተራምሰው ጀመር። መፍትሔው ታውቆ መከላከል እስከተቻለበት ድረስ የጨረሰውን ወጣት ኢትዮጵያዊ (ት) ቍጥር፣ ቤቱ ይቍጠረው ከማለት በስተቀር መገመት አይቻልም።

ከጊዜ በኋላ የወጣለት ስም " ሞኝ ባገኝ " ይባላል። " የወረርሽኝ በሽታ " ስም ነው። ከተገኘለት መፍትሔ ጋር የተዛመደ ሥያሜው ነው። ይህ በሽታ በያዘ በሦስተኛው ቀኑ ለጥብስ እንደሚያደርስ ተነግሮለታል። በነዚያ ሦስት ቀኖች ውስጥ፣ ከማጥወልወል አንስቶ፣ ደረቅ ራስ ምታት በማስከተል፣ ሁለንትናን ቀስፎ በመያዝ፣ ወደ ላይ ያስመልሳል፣ ወደ ታችም ያስቀምጣል። " <u>ሞኞችና የዋሀን ይተወናል ብለው ችላ ሲሉ፣ በሦስተኛው ቀን ይዞአቸው ይሔዳል። "</u> ብልጦቹ ግን ሦስት ቀን እንዲቆይ ዕድል አይሰጡትም። ገና በሽታው ሲጀምራቸው፣ ቶሎ ብለው ከግራ እጃቸው በክርናቸው በስተጀርባ ላይ የተጋደመውን የደም ሥር፣ በተገኘው ስለት ያለፍርሃት ይበጡታል። ወዲያው ጥቁር ደም ፈን ብሎ ይፈሳል።





የዚህ ጥቁር ደም ባስቸኳይ መፍሰስ፣ የበሽታውን ቅጽጽበታዊ ፈውስ ይዞ ይመጣል። ከዚያም በኋላ፣ ያንን ሰው፣ እርም ብሎ ተመልሶ አይነካውም። ሞኞች ግን በዚህዘዴ፣ በፍራቻም ሆነ በሌላ ምክንያት ስለማይጠቀሙ፣ ተላላፊው በሽታ እነሱን ባገኘ ቍጥር ድል ይመታል። በሽታው ይህን " ሞኝ ባገኝ " የተሰኘ ሥያሜውን ሊያተርፍ የበቃው፣ ባጭር አገላለፅ፣ በተጠቀሰው ምክንያት ነው።

ይህ በሽታ ከነበረው አስደናቂ ጠባዮች አንዱ፣ ለወጣቶች ብቻ ውሉን መሆኑ ነው። የበሽታውን መግባት የሰሙ ቤተ ሰቦች ሁሉ፣ መፍትሔውን በወቅቱ ለማግኘት፣ ያልደረሱበት ቦታ፣ ያልጓጠጡት ኮረብታ፣ ያልቀነጠቡት ዕፀዋት፣ ያልጨለፉት ዥረት፣ አልነበረም። ከነዚህም በተጨማሪ የየሆስፒታሉ ዶክቶሮችና፣ የየመንደሩ ጠንቋዮችና መጣፍ ገላጮች ይገኙበታል። አንዳንድ የሕክምና ሊቃውንትም፣ "ታላላቅ የዘመኑ ቦምቦችና ሮኬቶች የሚፈተኑት ከበረሐ ላይ ነው" የሚለውን ጭብጥ ይዘው፣ ምናልባት የበሽታው ምንጭ " ሬድዮ አክቲቭ" የፈጠረው ጠንቅ ነው ብለው፣ እስከመራቀቅ ደረሱ። አንዳንዶቹም ከዚሁ ባልራቀ ግምገማ፣ በሽታው ከመነጨበት አካባቢ ብዙ ዐይነት ጦርነቶች የተካሔዱበት ስለሆነ፣ የዘመናይ ጦር መሣሪያዎች ያስከተለው አደገኛ መርዝ ነው ያሉ አሉ። የተቀሩትም እንዲያ ያለ " ቫይረስ "፣ ከዚህ ቀደም በዓለም ላይ ያልነበረና ሕክምና ጠበብቶችም ያልደረሱበት በሽታ ነው ሲሉ፣ ገለልተኛ አስተያየታቸውን ሠነዘሩ። ይህ ዐይነቱ የሐኪሞች አስተያየት ትክክለኛነቱ ቢያጠራጥርም እንኳ፣ እንደ

ሙያቸው አስተሳሰብ የተሠነዘረ በመሆኑ፣ ተቀባይነት ባያገኝም
“እንኪያ ሰላንቲያ ” ይባልበታል ። በጣም የሚገርመውና የሚያ
ስቀው ግን የኢትዮጵያ ወታደራዊ ዐብዮት በሚሰጡት ተግባ
ራዊ ድርሻ አምኖ በመቀበል ምንም ዐይነት እርምጃ ያልወሰ
ደባቸው፣ የየመንደሩ ጠንቋዮች፣ ባለውቃቤዎች፣ መጣፍ ገላ
ጮች፣ ስለበሽታው የሰጡት አስተያየት ነው ።

መቸም የጨነቀው ሰው፣ የደረሰበትን ጭንቀት ለማስ
ወገድ የማይደርስበት ቦታና የማይሞክረው ዘዴ የለምና፣ በተላ
ላፊው በሽታ ልጆቻቸው የተያዙባቸው ቤተ ሰቦች፣ ልጆቻ
ቸውን ለማዳን ያልደረሱበት ድቢ ደብዳቢ፣ ያልረገጡት የጠን
ቋይ ደጅ፣ ያልተሳለሙት የመጣፍ ገላጭ በር አልነበረም ።

ዛሬም እንደወትሮው፣ የባለውቃቤነት ዝናው በዓብዮ
ታዊት ኢትዮጵያ ጭምር በጣም ገናና ሆኖ የሚገኘው የቁራው
ቀበሌ ጠንቋይ፣ ለዚህ ተላላፊ በሽታ መፍትሔ ይሆናል ብሎ
የሰጠው መድኃኒት “--- የጥንጁት ቅጠል፣ የሠንሠል ስር፣
የውሻ ኩስ፣ የዝንጀሮ ንፍጥ፣ ባንድ ላይ አድርቆ አድቆና
ሠልቆ፣ ወደምሥራቅ በሚፈስ የወንዝ ወሃ በጥብጦ በፍንጃል
ማጠጣት ነው ” የሚል ነበር ። ሌላዋ የዶሮ ማነቂያ ባለ አዶከ
ብሬዋ ጫት ቃሚ፣ ለተጠቀሰው ተላላፊ በሽታ የበኩሏን
መፍትሔ ስትናገር፣ “ ከበረሀ የመጣን እንግዳ፣ ቄጠማ ጐዝጉ
ዛችሁ፣ ጠጅ ሣሩን ነስንሳችሁ፣ አረቄውን ከርክፋችሁ፣ እጣ
ኑን፣ ከርቤውን፣ ሠንደሉን እያጨሳችሁ በመቀበል፣ ያዳል
ሞቴን፣ የራሔሎን፣ የአውልያን፣ የሌጌዎንን፣ የመጀንን
ምሶች በማቅረብ ማስተናገድ ነው ። እንግዳው ቂመኛ አይደ
ለምና በሰላም እንደመጣ በሰላም ይመለሳል ” በማለት ነበር
የመረቀነችው ። እንደሌሎቹ ግብረ አበሮቹ ሁሉ የእንጦጦው





መጣፍ ገላጭም፣ ስለተላላፊው በሽታ ሲፈላሰፍ ያተተው
“--- ያለንበት ሐራ ዘመን ወልጋዳ ነው ። ዐውደ ወርኁም
ዐውደ ፀሐዩም ከውሉ ስቶ ያፈነገጠበት ቀውጢ ዘመን ነው ።
ዑደተ ከዋክብቱም ከኬሮስ ይልቅ ለኬንትሮስ አጋድሏል፣
ከሠሌዳ- ሰማይ እንደሚታየው ከሆነ፣ ቀመሩ ጐደሎ ነው ።
ከሓሳበ ሕይወት ይልቅ ሐሳበ ሞት ጐልቶ ይነበባል ። ከፀጋ
ማይ ይልቅ ለየማናይ ይቀናል ። መላውን ሠንጠረዥ አመላ
ክተን በከሠተው ቅምር ሲገደፍና መባጃ ሐመሩ ሲሰላ፣ ለዘ
መኑ የሚላከውን መቅሠፍት ወለል አርጐ ያሳየናል ። ከሐዘሎ
በረሐ የመጣው ተላላፊ ደዌ ብዙ ጊዜ አይሰነብትም ። በዚያው
አጭር ጊዜ ውስጥ ግን ብዙ ይቀጫል ። በፊደል ትርጁማን
ሲታተት፣ “ሽ” ንና “አ”ን አይደፍርም ። “ ሕ” ንም አይነ
ካም ። የሚረፈርፈው ግን “ወ” ና “ዘ”ን ነው ። መዳኛው
መፍትሔ አንድ ብቻ ነው ። ይኸውም የመብረቅ ክሰል መታ
ጠን ። ወዲያው ለቆ ይበናል ይተናል! --- ” የሚል ነው ።

ሁሉም አዋቂ ነኝ ባይ፣ ጨንቆት ለጠየቀው ሕመምተኛ
የየበኩሉን እንደመሰለው ቀባጠረ ። ሌላው ቢቀር፣ “ ዐብ
ዮታዊው መንግሥት ” እምኖበት ለተቀበለው ሙያው፣ በየወሩ
ለሚያስከፍለው የሥራ ግብር የሚያሟላበትን ዲናሮች ቀር
ጭሟል ። በዚህም ተግባራዊ አገልግሎቱ፣ ዐብዮታዊ ግዴታ
ውን እንዳበረከተ፣ ገንዘብ የከፈለበት ካርኔ ሳይቀር ያረጋ
ግጥለታል ።

በተግባር ላይ ውሎ፣ ለተባለው ተላላፊ በሽታ ፣ ሙሉ
መፍትሔ ሊያስገኝ የቻለውን፣የክንድ ደም ስር የመብጣት ሕክ
ምናዊ ዘዴ፣ ማን እንዳስገኘው፣ በውል ባይታወቅም፣ “ ዐብ

ዮታዊው መንግሥት " ፤ የሥራ ግብር የሚያስከፍላቸው አባይ ጠንቋዮች እንዳይደሉ ተረጋግጧል። ምንም እንኳ፤ ያስተካከሙ ዘዴ ከዘመናዊው ሕክምና ቴክኒክ ጋር የጠበቀ ዝምድና የሌለው ቢመስልም፤ እስከፈወሰ ድረስ፤ በሕመም ተኞቹ ዘንድ ተቀባይነትን ካገኘ፤ መድሐኒትነቱን መካድ አይቻ ልም። ምናልባትም፤ ለተላላፊ በሽታዎች መከላከያ እየተባለ ክትባትስ ይደረግ የለ ! የደም ሥር መብጣቱም የዚያ ብጤ ይሆናል። ጥቁር ደም ግን ፊን ብሎ መውጣቱ፤ ታንኪር ሊያ ሰኝ ነው !!

ይህ ተላላፊ በሽታ በተስፋፋበት ሰሞን በሕክምና ሊቃ ውንት አካባቢ ከፍተኛ ጉምጉምታ ተፈጥሮ ነበር። ከቶውንም ስብሰባ ብጤ ተደርጐ፤ ከበሽታው ጠባይ ዐይነት አንስቶ፤ መከ ላከያውን የማጥናትና፤ በመጨረሻም ስለበሽታው ምንጭ ምር ምር ድረስ የጦፈ ውይይትና ክርክር ተካሒዶ ነበር። ያም ስብ ሰባ፤ " የተባለውን ተላላፊ በሽታ ምንነት ለማወቅ፤ ምንጩን መረዳት አማራጭ የሌለው መዳረሻ ዘዴ ነው......" የሚል ውሳኔ አስተላልፎ ነበር። ይህም ውሳኔ፤ የሳበውን ሁሉ ስቦ፤ ከፍተኛ መዘዝ በማስከተሉ አንዳንድ በስብሰባው ላይ ቀንደኛ ተካፋይ የነበሩትን ሐኪሞች እስከማሣሠር አብቅቷል። ዋናው መነሾ፤ በስብሰባው ላይ የተነሱት፤ ጥያቄዎች እንደሠንሠለት እየተያያዙ፤ ለበሽታው መፈጠር ምክንያት የሆኑትን ምንጮች በመጠቆማቸው ነው። ስብሰባው ካነሳቸው ጥያቄዎች ውስጥ፤ ሐኪም "በሽታው በአሁኑ ወቅት የትኛው ሥፍራ ላይ ይታያል? "

አዝማች_" አዲስ አበባ ከተማ ላይ። "

ሐኪም_" በምን አካባቢ ? "





አዝማች_" በእድገት ዘማች ቤተሰቦች ውስጥ!"

ሐኪም_" እዚያ ቤተ ሰብ ውስጥ ብቻ እንዴት ሊገኝ ቻለ? "

አዝማች_" ዘማቾች ይዘውት መጡ። "

ሐኪም_" ከየት ክፍለ ሀገር ? "

አዝማች_" ከበረሐ። "

ሐኪም_" ዘማች ለምን በረሐ ሔደ ? "

አዝማች_" የልማት ሀገራዊ ጥሪ ግዴታ ለማሟላት። "

ሐኪም_" በረሐው ነዋሪዎች ነበሩበት? "

አዝማች_" ምድረ-በዳ ነው። "

ሐኪም_" አካባቢው በተቀዳሚ ተጠንቶ ነበር?

አዝማች_" አናውቅም! "

ሐኪም_" ከዘመቻው ተጠሪ፤ ማብራርያ ይቅረብልን !..."

ከዘመቻ ዋና መምሪያ ባሉ የበላይ ባለሥልጣኖች፤ ለቀረቡ ጥያቄዎች፤

የዘመቻ መሪ_" ከተባለው ሥፍራ፤ በተሰጠኝ ትእዛዝ መሠረት አዝምቻለሁ--- "

ተጠሪ ሓኪሞች_" ስለዘመቻው ቦታ አስቀድሞ መጠናት የሚ ያውቁት አለ?።

የዘመቻው መሪ_" አይመለከተኝም። የበላዮቼን ጠይቁ! "

ተጠሪ ሐኪሞች_" ማን የሚያስረዳን ይመስልዎታል? "

የዘመቻው መሪ_" ምናልባት የመምሪያው ኃላፊዎች!"

ተጠሪ ሐኪሞች_" ስለመልሶችዎ እናመሰግናለን!ይበቃናል!

የመምሪያ ኃላፊ_"ለጥያቄው እንደፈለጋችሁኝ አንድ የመምሪያ አባል ነገረኝ "

ተጠሪ ሐኪሞች_" አዎ አዝማች ስለነበረበት በረሐ፤ አስቀድሞ

መጠናትና አለመጠናቱን ለማወቅ ፈልገን ነበር። እንደሚያውቁት የተላላፊ በሽታ ከዚያ---- ”

የመምሪያ ኃላፊ__“ይህን ጥያቄ እንዳነሳችሁበት አዝማቹም ነግሮኛል። ግን አንድ ያልተገነዘባችሁት ነገር አለ። የዐብዮት ጥሪ ቦታ አይመርጥም። ሆኖም ያነሳችሁት ጥያቄ ከኔ ዐቅም በላይ ነውና፣ ለበላይ ባለሥልጣን አስተላልፋለሁ። ማብራሪያውን ከሳቸው ታገኙ ይሆናል። ”

የበላይ አካል__“የደርግ አባል ነኝ። የማዕከላዊ ኮሚቴም አባል ነኝ። የኢሰፐአኮም አባል ነኝ። ለጥያቄ እንደምፈለግ ተነግሮኝ ነው የመጣሁት።

ሐኪሞች__“ በጣም አደገኛ ሆኖ ስለተገኘው፣ የተላላፊ በሽታ፣ መከላለከያ መፍትሔ ለማግኘት ጥናት ላይ ስላለን፣ ለዚሁ ዝግጅት እንዲረዳን፣ የዘመቻው ቦታ፣ አስቀድሞ መጠናትና አለመጠናቱን ለማወቅ ፈልገን ነበርና ---”።

የበላይ አካል__“ መቸም ያን ያህል ቍጥር የያዘ ዐብዮታዊ ዘማች ሠራዊት፣ ካንድ ቦታ ሲላክ ያለጥናት የሚሠማራ አይመስለኝም። ይኸ መቸም ዋናው መሠረታዊ ጉዳይ ነው። ያለጥናት የተደረገ በዐብዮታችን አንድም ነገር የለ። አምናለሁ ቦታው ተጠንቷል። ይሁን እንጅ ዝርዝሩ እንዴት እንደሆነ፣ እኔን ስለማይመለከት፣ የበላይ ባለሥልጣን ሊያስረዳ ይችላል። ይህንም የመጠየቅ ፍላጎታችሁን አቀርባለሁ። ”

ዋና ፀሓፊ__“ ዋና ፀሓፊ ነኝ። ጥያቄያችሁን ሰምቻለሁ። እኛ ብዙ ከፍተኛ አጣዳፊ ጉዳዮች በየቀኑ ስላሉብን፣ እንዲህ ያለውን ዝርዝር ተግባር ለማወቅ፣ ጊዜም ዐቅምም ዕድልም የለንም። ቢሆንም ለንዲህ ያለው ዝርዝር ተግባር እቅድ ሁሉ፣





አጠቃላይ መምሪያ ያለ በመሆኑ፣ ዘመቻው ላንድ ቦታ ( አካባቢ) ጥናት የተወጠነ አይመስለኝም። ለሁሉም ምድብ የየዘርፉ አማካሪዎች ስላሉ፣ የበላዩን ከመጠየቁ በፊት፣ ስለጉዳዩ የሚያውቁትን እንዲያብራሩላችሁ፣ ሁለንም በየተራ እልካለሁ-----”

አማካሪ__“ በምሕፃር ስሜ ቫራዎቭ እባላለሁ። ሩሲያዊ ያለም አቀፍ ወዳጅነት አማካሪ ነኝ። ጥያቄአችሁን ፀሓፊው ነግሮኛል። ግን ስለጉዳዩ ምንም የማወቀው ነገር የለም። በርግጥ ያለ ተቀዳሚ ጥናት ተዘምቶ ከሆነ ከፍተኛ ስሕተት ነው! ”

አማካሪ__“ራውል ቫልዲስ ቪቮ እባላለሁ። ኩባዊ ነኝ። የቀረበልኝ ጥያቄ እኔን አይመለከተኝም። እንደማይመለከተኝ ልነግራችሁ ነው የመጣሁት። አማካሪነቴ ለጦር ነው። ”

አማካሪ__“ምሥራቅ ጀርመናዊ ነኝ። ሆረሰት ይሁሉስ እባላለሁ። በዐብዮት ኪደት ውስጥ ብዙ ስሕተቶች ሊደረጉ ይችላሉ። ይህንንም ሐቅ ባለፉት ዐብዮቶች ታሪክ ውስጥ በየምዕራፉ ዐይተናል። ግን ዋናው ቁምነገር፣ ከትክክለኛው ተግባር ይልቅ ስሕተቱ ያነሰ መሆን ነው። ስለዚህም ነው ሕዝቦች ድል የሚያገኙት። ወደ ጥያቄአችሁ ልምጣና፣ ጥያቄው ትክክለኛ ይመስለኛል። ግን እኔን ስለማይመለከተኝ መልሱን ልሰጣችሁ አልችልም። በነገራችሁ ላይ የኔ ሙያየና ሥምሪቴ፣ በፀጥታ ተግባር ላይ ነው። ሌሎቹን አማካሪዎች መጠየቁ ያዋጣል! ”

የነዚህ የሦስቱ አማካሪዎች ምላሽ ተሰምቶ እንዳበቃ፣ የሓኪሞቹ ስብሰባ ቀጥሎ ነበር። በዚያው በውይይታቸው ላይ እንዳሉ፣ ድግን መትረየስ በያዙ ወታደሮች ተከበው፣ ዋና ዋናዎቹ ቀንደኞች ተነቅሰው፣ ወደ ማረፊያ ቤት እንደተወሰዱ፣ ስብሰባው ወዲያው ተበተነ። በቋሚ ተጠሪም የተስተናገዱ

ነበሩ። ስብሰባው ይበተን እንጅ፣ ባልታሠሩት ጥቂት ሐኪሞች፣ በጉዳዩ ላይ ግለኛ ትችት ቀጥሎ ነበር። ሁኔታው በጣም ያበሳጫቸው፣ " ዐብዮታዊ ጥሪ እንዴት ቦታ አይመጥርም ይባላል? ያን ያህል ወጣትና የተማሪ ጉልበት የትም በረሐ ያለ ተቀዳሚ ጥናት መስደድ፣ ዐብዮታዊነቱ ከምኑ ላይ ነው?ስንት ደጋና ወይነ ደጋ መሬት፣ ደረቱን ገልብጦ፣ የሠራተኛ ያለህ እያለ ሲጮህ፣ ያን ሁሉ ሠራዊት ንዳድ ከሚፈላበት ምድረ በዳ መስደድ፤ ዐብዮትነቱ ከምን ላይ ነው? ለዚሁ ዐይነት ዘመቻ ' የዐብዮት ጥሪ፣ የቀይ ኮከብ ጥሪ ' እየተባለ በሙገሣ ሲዘፈንለትና ድርሰት ሲደረስለት፣ መስማትም ሆነ ማየት ወንጀል ነው። አስቀድሞ ባልተመረመረና ባልተጠና በረሐ፣ ወጣት ታዳጊዎችን ወስዶ ያለዕድሜአቸው እንዲቀጩና እንዲያልቁ ማድረግ ይቅርታ የማያልፈው በደል ነው። ይህንን መሰል አሠቃቂ ኢሰብአዊ በደል የሚፈጽም መንግሥት፣ "ዐብዮት " የሚለውን ክቡር ቃል እንኳንስ ሊጠቀምበት ቀርቶ፣ በሕልሙ ሊያየው አይገባም። በዚህ ተላላፊ በሽታ ተለክፈው፣ ያለዕድሜአቸው የተሠዉ ወጣት መገኖቻችንን፣ የሀገራችን የወደፊት ተራማጅ ታሪክ ሲያስታውሳቸው ይኖራል።

በዐብዮት ስም ለተፈፀመው እልቂትና ፋሽስታዊ ደባ ግን ምን ጊዜም ቢሆን ተጠያቂዎቹ ፋሽስቶቹ ባለሥልጣኖችናቸው። በፈፀሟቸው ፋሽስታዊ ግፎች ሁሉ፣ ተጠያቂነታቸው አጋልጧቸው፣ አንድ ቀን ለፍርድ እንደሚቀርቡ፣ በማንኛውም አመዛዛኝ ኅሊና ውስጥ የሚጉላላ እውነታ ነው። የስንት ንፁሐን ለጋ ወጣቶች ሕይወት፣ ሰው ባልደረሰበት ምድረ-በዳ ውስጥ፣ እንደጣሉት ቅራቅንቦ ቆሳቆስ ተንከታክቶ ሲወድም





ማየት፣ የብዙ መጭ ትውልዶች ታሪክ የሚያስታውሰው የሚዘገንን ትዝብት ነው።

ይህ አሰቃቂ ድርጊት ከኛ የሕክምና ሙያ ተግባር ጋር በተዛመደ አጋጣሚ የተከሠተ በመሆኑ፣ ለተላላፊው በሽታ መንሥኤ የሆነውን " ዐብዮታዊ የልማት ዘመቻ " የሚሉትን ፈሊጥ፣ ዐቅማችን የፈቀደልንን ያህል በመቃወም፣ ፋሽስታዊ ባህርዩን ማጋለጥ አለብን። ለዚህም የማጋለጥ ትግላችን የሚረዳን፣ በዐብዮት ስም ተሠልፎ ፋሽስታዊ ደባ የሚፈጽመውን መንግሥት አንዳንድ እበላ ባዮች፣ በራሳቸው ግላዊ ጥቅም አንፃር ተነስተው ሲያሞግሱና ሲቀድሱት፣ ሲዘምሩለትና ሲዘፍኑለት ባየን ቍጥር፣ ሕዝቡ ከመሰበኩ በፊት፣ ተገቢውን ሓቀኛ ጐዳና በማሳየት የሰባኪዎቹን ተንኰል ያጋለጥን እንደሆን ነው።

ይህ በዐብዮት ስም የሚነግድ መንግሥት፣ ፋሽስታዊ ሸፍጡን ጭኖ ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ፣ በግዴታ በሕዝቡ ላይ ለማራገፍ፣ ያልተጠቀመበት ዘዴ የለም። በተለይም ደራስያንና ጋዜጠኞችን፣ ሠዓልያንና ሙዚቀኞችን፣ እንዳሻው አገላብጦ ተጠቅሞባቸዋል። ከየቦታው የተለቃቀሙ እበላ ባይ ቱኪዎቹም፣ እድሜውን ያስረዘሙለት መሰሏቸው፣ ያልቀባጠሩለት ቱማታና ያልነፋለት እንቢልታ የለም። የፋሽስቱን ሸቀጥ ለማዋደድ፣ አሻሻጭ ቅጥረኞች በመሆናቸውም፣ ያልደረደሩለት ሪከለምና ያልጀነጀኑለት ማስታወቂያ አይገኝም። ፋሽስታዊነቱን፣ በዐብዮታዊነት ለመተካት ያልመቱለት የውሸት ነጋሪት፣ ያላስተጋቡለት የውሸት አዋጅ፣ ያልነፋለት የዕድገት ቱልቱላ አይገኝም።

ፋሽስታዊው መንግሥት በየዕለቱ ያርዳል፣ ይረሽናል፣
ያቃጥላል። ፋሽስቱ በየዕለቱ የሚፈፅመውን፣ በተለይም ይህንን
ኢሰብአዊ ግብር፣ ይህንን አመፃዊ በደል፣ ይህንን በዐብዮት
ስም ያሚፈፀም ግፍ፣ ይህንን ያደባባይ ፋሽስታዊ ደባ፣ በጽሑ
ፋዊ መጋረጃቸው የሸፈኑለት መስለው፣ አንዳንድ የኪነት ውር
ውር ባይ ፋሽስት አደር ደራስያንና አርቲስቶች እንደቃተቱ
አሉ። በተለይምለፊውዳሉ ባለሥልጣኖች ጋሻ ጃግሬ ሆነው፣
ተራማጆችን ነዳፊዎች ሲከላከሉላቸው ኖረው፣ ዛሬ ደግሞ
በተራው ለፋሽስት ባለሥልጣኖች ባለሟል ሆነው ሥሉሣቸውን
ያዞሩ፣ የኪነት ሰዎች፣ ወላዋይ አቋማቸው የሚያጠያይቅ ከመ
ሆን አልፎ፣ ተገቢ ዋጋቸውን እንዲያገኙ አሳሳቢ ከሆነ ደረጃ
ላይ ደርሰዋል። ፋሽስቱ መንግሥት የግፍ ድርጊቱን በሶሻሊ
ዝምና በዐብዮት ካባ ሸፍኖ በየዕለቱ የሚፈፅመውን ዳባ፣ "ከ ሀ
ሁ ጀምሮ፣ በአቡጊዳ በኩል፣ የቀይ –ኮከብ ጥሪ " እስከሚለው
ድረስ፣ የፋሽስቱን ደባዊ እርምጃዎች ሁሉ፣ ተራማጅ ድርጊት
ለማስመሰል ሞክረዋል። ጭብጡንና ሐቀኛውን የኢትዮጵያ
ጭቁን ሕዝብ ጊዜያዊ ሁኔታና ኑሮ፣ የሚያውቅ ሁሉ፣
የእነዚህ እበላ ባይ ደራሲዎች እሪታ፣ የገደል ማሚቶ መሆኑን
በግልፅ ሊረዳው ይችላል። የነሱ የውሸት ድርሰታዊ አዋጅ፣
የኢትዮጵያን ጊዜያዊ አሳዛኝ ሁኔታ ሊለውጠው አይችልም።
በተለይም፣ የፋሽስቱን መንግሥት ለማንበርከክ የሚታገሉትን
ተቃዋሚ ኃይሎች ለማዳከምና፣ የሴሰባቸውንም ባሕርይ ለመስ
ጠት ከመጠን በላይ፣ በድርሰታቸው ውስጥ ጥረዋል።

ያራምባና የቆቦውን እየቀባጠሩ፣ " በሕይወት ያልነበሩ
ሰዎችን " ባሕርይ እንገልፃለን ቢሉም፣ ራሳቸው የሚገኙበት





የንዑስ ከበርቴነት ወላዋይ ጠባያቸው፣ በውሸታምነት ያጋልጣ
ቸዋል። ከሁሉ ይልቅ በጣም የሚያስገርመው፣ በፍጹም ቆራጥ
ነት ኢሕዝባዊውን መንግሥት ለመቋቋምና ለመቃወም ባጭሩ
ታጥቀው የተሠለፉበትንና፣ ለጭቁኑ ኢትዮጵያዊ ወገናቸው
አጋር የሆኑትን ታጋዮች፣ በገዛ ራሳቸው እበላ ባይነት ዐይነ
ልቦናቸው ተመልክቶ፣ እበላ ባዮች አድርገው ለማሳየት መሞከሩ
ነው።

የዘመኑን የስነ-ጽሑፋዊ ይዘት በዐይነሕሊና ብንመረ
ምር፣ የፋሽስት መንግሥት ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ እያደገ የመ
ጣውን የሥነ ጽሑፍ መጫጫት በጉልህ የሚያሳይ ማስረጃ
ነው። ኪነትም በድርሻዋ በወታደር አፈ-ሙዝ ፋሽስታዊ
ስለት ተገዝግዛለች። በተረፈ ግን፣ የፋሽስቱን የጉልበትና የደን
ደስ አገዛዝ፣ " የናት ሀገር ጥሪ፣ የዐብዮት ጥሪ፣ የቀይ ኮኮብ
ጥሪ፣ የእድገት ዘመቻ፣ የልማት ዘመቻ-- " እያሉ ሶሻልስታዊ
መልክና ስም በመስጠት፣ ለማስመሰል የሚምክሩትን ሁሉ፣ የፈ
ጠረውን ልዩ ልዩ፣ የድህነት፣ የድንቁርና፣ የኀባርነት፣ የበሽ
ታና የእልቂት ጠንቆችን በማስረጃነት በማሳየት፣ ፕሮፓጋ
ንዳን፣ በጥልቅ ሁኔታዎች በመመከት፣ ማንኛውም ተራማጅ
ወገን ሊቋቋማቸው ግዴታ አለበት። እኛም በበኩላችን፣ ይህን
የተላላፊ በሽታ መሠረተ-ምክንያት መነሻ በማድረግ አቋማች
ንን በይፋ ለመግለጽ ሠላማዊ ሠልፍ እናደርጋለን!" ብለው
ለረዥም ጊዜ ሲወያዩ ከቆዩ በኋላ፣ የሚከተሉትን መርሖዎች
ለሠልፋቸው አዘጋጁ።

" ለተላላፊ በሽታ ምክንያት የሆኑ ለፍርድ ይቅረቡ! "
" ከጭብጥ ሁኔታ የራቀ ፕሮፓጋንዳ ይወገዝ!"

“ የእበላ ባዮች ደራሲያን መጻሕፍት ባደባባይ ይቃጠሉ! ”

“ በሕዝባዊ ጉዳዮች ላይ ሕዝቡ የመወሰን መብት ይኑረው!”

“ አስመሳይ ሶሻሊስቶች ይውደሙ!”

“ በበረሐ ለተሰዉ ወጣት ወገኖቻችን መታሰቢያ ይቁም! ”

“ ሶሻሊስታዊ እውነት ምንጊዜም ትኑር!--- ”

እነዚህን የመቃወሚያ መርሖዎቻቸውን በሠሌዳ ላይ ፅፈው ካዘጋጁ በኋላ፣ ለሚያደርጉት የመቃወሚያ ሰላማዊ ሠልፍ፣ አጃቢ ደጋፊዎችን ለመሰብሰብ፣ የጥሪ ወረቃታቸውን በድብቅ በተኑ ።

ምንም እንኳ ኢሕዝባዊ መንግሥት በጉዳዩ ነቅቶ፣ ሠልፋቸውን በጠመንጃ አፈሙዝ ደግኖ ቢያጨናግፋቸውም፣ በተባለው ቀንና ሰዓት ሰልፉን አካሒደው፣ የጠበቁትን መለስተኛ ውጤት ለማግኘት በቅተዋል ። ይሁን እንጅ ያን ውጤት ለማግኘት የከፈሉት መሥዋዕትነት ቀላል አልነበረም ። በሰላማዊው ሠልፍ ላይ የተገደሉም የቆሰሉም ነበሩ ። በተለይም፣ በልዩ ዝግጅት “ ድንቄም ሶሻሊዝም ” የተባለ የፀጉር አሠራር በመጠቀም፣ የፋሽስቱን አቋም ለማጋለጥ፣ በየዕለቱ ግንባር ቀደም ላይ ተሠልፈው የነበሩ፣ የተላላፊ በሽታው ልጆቻቸውንና ወንድሞቻቸውን የገደለባቸው፣ እናቶችና እህቶች ሞተዋል፣ ቆስለዋል፣ ታስረዋል ።

ሰላማዊውን ሠልፍ ካዘጋጁት የሕክምና ዶክተሮች ውስጥ፣ ዋናዎቹ መሪዎች፣ ከዚያ ቀን ጀምረው የት እንደ





ደረሱ አይታወቅም ። የዚያን ከፍተኛ ሰላማዊ ሠልፍ መልእክት ለማድበስበስና፣ ባሕር ማዶ ድረስ አምልጦ የወጣውን የዘማቾች እልቂት ዜናና ያስከተለውንም የፕሮፓጋንዳ ተፅዕኖ ለመቋቋም በታሰበ እቅድ፣ የኢሕዝባዊው መንግሥት ባለሥልጣኖች የ “ ሞኝ ባገኝ ” ን ተላላፊ በሽታ ምንጭላለማሳየትና በዚያም አካባቢ አንድም የዘማች ቡድን እንዳልተሠማራ ለማሳመን፣ ለውጭ ሀገር አምባሣዶሮችና ለታወቁ ጋዜጠኞች ከስፍራው ድረስ ጉዞ አዘጋጅቶ አስተናገደ ። ቢያለበትም በተፈለፈሉት የቀበሌ ኪነት አባሎች አማካኝነት፣ “ ተላላፊው በሽታ ጠፍቷል”፣ “ በሶሻሊስት ሀገር ሞኝ የለም! ” የሚሉ የፕሮፓጋንዳ መዝሙሮች አዘመረ ። ላንዳንድ የተረፉ ዘማቾችም የዐብዮት መዳልያ ሸለመ ። ከነዚህም ማደናገሪያዎቹ ይበልጥ ያስደነቀው፣ ራሱ ለፈጠረው ግዳይ የተጠቀመበትን የበቀል ርምጃ ነው ። ይኸውም ለተላላፊው በሽታ መነሻ ምንጭ የሆነችው ያች የበረሐ መርዘኛ ትንኝ፣ መናኻሪያዋ ነው በሚል ግምት፣ ያን የሚያሳዝን የዱር ሀብት፣ ሠደድ እሳት ለቆበት፣ ዘሬም እንደነደደ አለ ።



# ሩቢያ



ሰውጥ አለ ይሉናል ሰማን እንጅ አላየን!
ባላገር እኛ ግን እንዳለነው አለን!
ሙቀጫና ወፍጮ ቁናና እንሥራ እያላገጡብን!

(የጠፍ. ቁ.6)

# መንደርደርያ

ከመጻሕፍት ብቻ ከተቃረመ ድፍን ንባበ-ቃላት በመመራት፣ የሕዝብን ያካባቢ ጭብጥ ሁኔታዎች፣ በባሕሉ፣ በልምዱ፣ በእምነቱ አንፃሮች ያሉትን ጊዜያዊ ኃይሎችና ድክመቶች፣ በሚገባ ሳያጠኑ፣ እንዲው ዘለው ከኅብረተ-ሰቡ ውስጥ በመግባት፣ ሥር ነቀል ለውጥ እናድርግ ለሚሉና ለሚያተራምሱ የበታች ሹማምንት (ካድሬዎች) ትምህርትና ተመክሮ ይሆናል። በሌላ ጐኑ ደግሞ፣ እነዚህን መሰሎቹ ተምኔታውያን ካድሬዎች፣ በዓብዮት ስም ለሚፈፀሙት ሕዝባዊ በደል፣ የስንቱ ቤት ትዳርና ንብረት መፍረስ እንደቻለ የሚያሳይ፣ የወርኀ ማዕዶት ( የሽግግር ዘመን ) ችግር ማንፀባረቂያ መስተዋትም ነው።



"ዚአኪ ለዚአየ"፣ እንዳለው ያ መጣፍ፣
ነውሩ ምን ላይ ይሆን? በወል መደጋገፍ!
አጥቤሽ ብታጥቢኝ፣በኩልነት ብናርፍ፣
"አንድ አካል"ስ ማለት፣ነው ወይ ከዚህ የሚያልፍ?

# ሩቢያ

.... ካፌ-ድስት ባላነሰ ትልቅ ማሠሮ ውስጥ ውሀ ጥዳ ለች። እንጨት እንደልብ መቍረጥ ከተከለከለበት ጀምሮ፣ የጕልቻ ላይ ማሠሮዎች በእሳት ነበልባል ከመጠን በላይ መለብለቡ ቀርቶላ ቸው፣ መዝናናት ከጀመሩ ዐመታት አልፏቸዋል። አዘውትራ "ለማ ሰሮዎች እንኳ ጊዜ ይውጣ! " የምትለዋ ሩቢያ፣ እንደልቧ የምት ማግደው እንጨት እንደወትሮው ባለመገኘቱ፣ የምትጥደው ሁሉ ቶሎ አልበስል አልፈላ እያላት በሚያስከትለው ምሬት እየበሸቀች ነው። ማድቤቷ በዚያው በትልቅ ሠቀላ ቤቷ ውስጥ፣ ካንደኛው ጥጋት ላይ ነው። ሲቀመጡ እግር ሊያስቆም የሚያስችል ያህል ክብ መደብ በምድጃው ዙሪያ አለ። በረባዳው ምድጃ ላይ ዘወትር የምትዝቀው የታመቀ አመድ ይገኛል። በመሐሉም ላይ የኰረዳ አጐጠጐጤ ጡቶች የሚመስሉ ሦስት የድንጋይ ጉልቻዎች ጉብ ጉብ ብለዋል። ያ ለባል እግር ማጠብያ እንዲሆን የሚዘጋጀውን ውሃ በማሞቅ ላይ የሚገኘው ማሠሮ ተንዘራፍጦ የተቀመጠው በነ ዚህ ጉልቻዎች ላይ ነው።

ከምድጃው በስተቀኝ ጥግ ጥጉን ይዞ መጠናቸው የተለያየ ጋኖችና ድብኝቶች ተደርድረዋል። የእህል ማከማቻዎቻቸው መሆ

ናቸው ነው። ከምድጃው በስተግራ፣ ከቤቱ ግድግዳ ጋር ተደግፎ የተተከለ ወፍጮ ቆሟል። ለሩብያ እህል የምትፈጭበት ወፍጮ ቤቷ ብቻ ሳይሆን፣ መንፈቀ ሌሊት በደረሰ ቍጥር፣ ከእንቅልፏ ተነስታ ዝማሬዋን የምታቀልጥበት የምሽት ክበቧ ጭምር ነው። ኑሮዋን የሚያስመለክት ደመ-ነፍስ ሐሳቧን በዜማ የምታን ጐራጉርበት የሙዚቃ አደራሿ ነው። መንፈቀ ሌሊት ላይ መጇን ይዛ ለወፍጮ በምትዘጋጅበት ቍጥር፣ ድንገት የሚፈልቅ ዘፈኗን በቅኝት ስታንጐራጉር፣ ወፍጮና መጅ በበኩላቸው በሚፈጥሩት ጃዛቸው ያጅቧታል። ታዲያ የዘንድሮ እንጕርጕሮዋ ይዘት ከወት ሮው ለየት ይላል። በየቀኑ መንፈቀ ሌሊት ላይ ለወፍጮ ተግባሯ በተሠማራች ቍጥር፣መልሳ ቀልሣ፣ ደጋግማ ሠልሳ የምታዜመው

“ ለውጥ አለ ይሉናል ሰማን እንጅ አላየን፣

ባላገር እኛ ግን እንዳለነው አለን፣

ሙቀጫና ወፍጮ፣ ቁናና እንሥራ፣ እያላገጡብን። ”

የምትለውን ነው። ዜማዋን ለሰማ ልቅሶውን ለመቆጣጠር አይችልም። ሩቢያ ይህንን ይዘት ያዘለ እንጉርጉሮዋን ስታዜም ካን ጀቷ ስለሆን፣ የሰሚውን ማንኛውም ሰው አንጀት ስለሚበላ፣ ከፀ ፀት ነፃ አይሆንም። ከላኛውም እንጉርጉሮዋ ጋር እያይዛ የምታ ዜመው ፣

“ ምን ዐይነት ለውጥ ነው ያላጠሩ ቅማል፣

ምን ዐይነት ለውጥ ነው የሚያጣላ ክባል፣

ምን ዐይነት ለውጥ ነው፣ ማምጣት ያልሆነለት፣ ከድሮው የሚሻል

ዝምብሎ ባዶውን ባየር የሚፎልል! ” ብላ በዕዝል የምትዘመውን እንጉርጉሮ ወደ ንጋቱ ላይ፣ ያካባቢዋ ወፎች ሳይ ቀሩ በዝማሬአቸው ያጅቧታል። እንጉርጉሮዋ መሥጧት ሞቅ





ያረጋት ጊዜም፣ መጇን ከደረሰበት ላይ ታቆምና፣ ሽንጦቿን በጆቿ ደግፍ “ እሽክም እስስ! እሽክም እስስ!...” እያለች እስክስታዋን ታስለነካዋለች። አልፎ አልፎም ራቅ ብሎ ደረቅ መደብ ላይ ተኝቶ፣ የንጋት እንቅልፉን ሲለጥጥ ያለ ባሏን፣ በዚሁ እስክስታዋ የምትቀሰቅስበት ጊዜ አለ።

ሩቢያ የሰላሣ ስምንት ዐመት እድሜ ያላት፣ የገበሬ ሚስት ነች። ባሏን ካገባችው አምስት ዐመታት ቢያልፏትም፣ ከአምስት ዐመታት በፊት ከወለደችው ወንድ ልጇ በስተቀር ሌላ ልጅ የላ ትም። እሱንም ቢሆን ማደጐ ሰጥታዋለች። ተወልዳ እስካሁን የምትኖረው በደቡብ ኢትዮጵያ በሚገኝ፣ በአንድ የክፍለ ሀገር ገጠር ውስጥ ነው። ባሏ ሞፈር ዘመት ገበሬ ሲሆን፣ “በለውጡ ” ጊዜ በተላለፈው አዋጅ መሠረት፣ ከጢሰኛነቱ ነፃ ወጥቶ፣ የኩር ማን መሬት ባለርስት ሆኗል። በገዛ ርስትነት ላምስት ዐመታት ቢጠቀምበትም፣ ኩርማኑ መሬት ባስገኘለት ምርቱ ተደስቶ አያው ቅም። የምርትነቱ ማነስና መብዛት ሳይሆን፣ የሚያናድደው፣ አዋጅ በሰጠው ሀብት ሊያዝበት አለመቻሉ ነው። የጋራ ጐተራ፣ የመ ዋጮ፣ የርዳታ.... እየተባለ፣ ላቡ ያስገኘለትን ምርት በሙሉ ሊያገ ኘው አልቻለም። “ብዝበዛ መልኩንና ባሌበቱን ቀይሮ መጣ” ነው የሚለው የሩቢያ ባል፣ ንዴቱ ገንፍሎ በቃላት እስትንፋሱ ሁኔታ ውን ለመግለጽ ሲሞክር።

በዚያን ዐመት አንድ ዕለት፣ በጥማድ በሮቹ እርሻ ውሎ ማታ ወደ ቤቱ ይመለሳል። በዚያን ዕለት ከወትሮው የተለየ ድካም ተሰምቶት ነበር። “ ቤቴ ቶሎ ደርሼ፣ የጣመነ እግሬን ሚስቴ እንደተለመደው እሽትሽት አርጋ አጥባኝ፣ ” እያለ ሲገሠግስ ቤት ይደርሳል። እንዳጋጣሚ በዚያንው ዕለት፣ የገጠር ሴቶች ማኅበር

ስብሰባ አድርገው ኖሮ፣ ከመንግሥት በተላኩ ሴቶች ካድሬዎች አማካይነት " ስለ ሴቶች እኩልነት " ጉዳይ የመጀመሪያው ከፍተኛ ውይይት ሲደረግ ውሎ፣ ሩብያም በዚህ ስብሰባ የመገኘት ግዴታ ስለነበረባት፣ እዚያው ውላ፣ ቀደም ሲል ገና ከቤት መድረሷ ነበር። እሷን ይበልጥ ያደከማት፣ ወደ ስብሰባው ስትሔድና ስትመለስ የተጓዘችው የሩቅ መንገድ ጣመን ሳይሆን፣ በስብሰባው ላይ ስትሰማ የዋለችው የካድሬዎች ዲስኩር ነው። ለጆሮዎቿ እንግዳ የሆኑ አዳዲስ ሐሳቦች ከከተሜዎቹ የሴቶች ሹማምንት ሲንቆረቆርላት ውሎ፣ መንፈሷ ተሸብሮ ሰውነቷን እጅግ አዝሎታል። ይሆናል ብላ የማታስበው፣ ወርቃ ወርቅ ሐሳቦች፣ ሲምቦለቦሉላት በመስማቷ፣ መንታ ስሜቶች ባንዴ መንፈሷን ወረዉት፣ አለቅጥ ስለረበሻት፣ አለወትሮዋ በሐሳብ ሰጥማ ታሰላስል ነበር። " እነሱ እንዳሉትማ ቢሆን ኖሮ፣ ሕይወት ምንኛ በሠመረ! ግን በኑሮአችን አካባቢ ውስጥ ገዝፈው በየዕለቱ የምናያቸውን ጉልህ ችግሮች፣ እንዴት ልንወጣቸው ችለን ነው፣ ለዚያ ከፍተኛ ተግባራዊ እኩልነት የምንበቃው? " እያለች፣ ኰርኩረዋት የማያውቁ አዳዲስ መሠረታውያን ጥያቄዎች በልቧ ውስጥ እያነሣች ትጥላለች። አለወትሮዋም የነበራት ንቃት ሁሉ ከሁለንተናዋ ደብዝዞ መጥፋቱ፣ እንደ ገበሬ ሚስትነቷ የነበሩባትን የምሽት ተግባሮቿን ዘንግታቸው፣ ብቻ ለባሏ እግር ማጠቢያ የሚሆነውን ውሃ በማሠሮ አድርጋ ከምድጃው ላይ መጣዷ ይታወሳታል።

ባሏ ጥማድ በሬዎቹን እየነዳ፣ " ካሁን አሁን ቤቴ ደርሼ፣ ጣመኔን ተወጥቼ፣ " በሚል ተምኔቱ ሲገሠግሥ ቆይቶ ደጃፍ ላይ ይደርሳል። እንደደረሰም፣ ባለቤቱን ባካባቢው ለማግኘት በዐይኖቹ ይመትራል። ለወትሮው፣ ሚስቱ ከደጅ ራቅ ብላ በመሔድ፣ የደ





ከመ ባሏን ትቀበለው ነበር። ብዙ ጊዜም ከንፈሮቹን ሳይሆን፣ አፈር ሲቅሙ የዋሉ ጉንጮቹን ሙጭጭ አርጋ በመሳም፣ " የደጎና ገባህ " ምኞቷን ትገልጽለት ነበር። ወዲያውም፣ እሱ የተጠመዱትን በሬዎች እስኪፈታ ድረስ፣ ጅራፉንና ጠዋት ምሳ የወሰደበትን አገልግልና ቅል ተቀብላ፣ ወደ ቤት ትመለስና፣ እቃዎቹን በየቦታቸው ታስቀምጣለች። ያላት ለታም እንደገና ተመልሳ፣ ሞፈሩንና ቀንበሩን ቅትርቱንና ወገሉን.. ከባሏ ተቀብላ ከቤት በመውሰድ በቤታቸው ውስጥ፣ በተለይ ለእቃዎች መስቀያ በተዘጋጀው፣ በቤቱ እንብርት ላይ በቆመው፣ ባለባላ ምሠሦ ላይ ታ ስ ቀምጣቸዋለች። በዚያን ዕለት ማታ ግን፣ ሌላው ትርፍ ተግባራዊ ርዳታዋ ቀርቶ፣በተለምዶ ምድብ ሥራዋ የነበረውን፣ ሲያርሱ ለዋሉት በሬዎች መቀቢያ የሚሆን የድርቆሽ ሣር እንኳ በግርግማቸው ውስጥ አላስቀመጠችም ነበር።

ባሏ ከቤቱ ደጃፍ ደርሶ፣ መላ ገረገንቡን በዐይኖቹ ሩቢያን ቢያፈላልግ ሊያገኛት አልቻለም። " ምናልባት ከስብሰባው አልተመለሰች ይሆናል " እያለ ጥቂት እንዳመነታ፣ የተጫነው የድካም ጣመን አላስችል ብሎት፣ ከደጃቸው ላይ ለጥጃዎች ማሰርያ ተብሎ ከተጋደመው ግንድ ላይ፣ አረፍ ለማለት ቍጭ ይላል። ምንም ያህል አልቆየ፣ የምሽቱ አጋጣሚ አበሳጭቶት፣ ሚስቱም እንደእሱ ስብስባውና መንገዱ አድክሟት፣ ቤት ውስጥ ተኝታ ይሆናል በሚል ጥርጣሬ፣ ድምጹን ከፍ አርጎ፣

" ሩብያ! ሩብያ!...... " ብሎ ይጣራል።

" አቤት! " ከእንቅልፏ የቀሰቀሳትን ያህል ቀኑን ስትሰማው የዋለችውን ሐሳብ ስታሰላስል ከነበረችበት ምድጃ አጠገብ አፈፍ ብላ ትነሣለች።

" ሩብያ! ሩብያ! " ደግሞ ይጠራታል፣ በጨረፍታ የሰማው ድምፇ እውን ይሁን አይሁን እየተጠራጠረ።

" መጣሁ! አቤት፣ ጌትዬ! " የላላ መቀነቷን እያጠበቀች፣ ከቤት ባሏ ወዳለበት ቦታ እየሮጠች ትመጣለች።

" ጉባኤው አደከመሽ እንዴ? ደጅም ሆነ ቤቱ በጣም ጭር አለብኝ " እንደስመመን፣ ከቤታቸው ክፍክፋት ላይ ብን ብን የምትለዋን አነስተኛ የምትዝለገለግ ጭስ፣ በሩቅ ጣራጣራውን እያየ።

ሩብያ ወዲያው ተፍ ተፍ ብላ፣ ጅራፉንም፣ ጠዋት ይዞት የሔደውን የስንቅ መያዣ አገልግልና ቅል ትቀበለዋለች። ባልየዋ ግን አሁንም ተደናግሮታል። ለወትሮው፣ እርሻ ውሎ ሲመጣ፣ ከቤቱ ደጃፍ ላይ ይጠብቀው የነበረው መቀበያ ሁሉ አልነበረም። ሲኖር ጠላ፣ ሲኖር ትኩስ ወተት፣ አለያም እርጎ፣ እነዚህ ሲጠፉ ደግሞ ቅራሬ ወይም አሬራ ማግኘት ነበረበት። በዚያን ቀን ምሽት ግን፣ ሌላው ሁሉ ቀርቶ፣ ለመኖሩና ለህላዌው ተስፋና አለኝታ የነበረው የሩብያን ከንፈር ስሚያ አላገኘም። ይህንንም በማጣቱ፣ ሁኔታው ይበልጥ ተባብሶበት፣ ከመደናገር አልፎ መርበትበት ጀመረ። ሩብያ የስንቅ መያዣዎቹን ከቤት አስቀምጣ ስትመለስ፣ ባሏ ሮጥ ብሎ ጣመን ባብረከረካቸው እጆቹ፣ ሁለት የሩብያ ትከሻ ዎቿን ያዘና፣

"እመቤቴ! ዛሬ ምን ነካብኝ ይሆን! መሳሙንም ረሳሽው!" አለና አፈር ሲቅሙ በዋሉት ከንፈሮቹ፣ የቀኝ ጉንጯዋን እንደቆላሎሚ ምጥጥጥጥጥጥ ሲያደርግ፣ ሰዓት ያዥ ተቆጣጣሪ ባጠገባቸው አልነበረም እንጅ፣ መምጠጡን ሲያቆም አሥር ደቂቃዎች ብሎ በመዘገበ ነበር።





" ጌትዬ!" አለች ሩብያ የተመጠጠው ጉንጯዋ ከፈጠረው ስሜት ጋር፣ መላ ፊቷን ፍም አስመስሎት " ጌትዬ! ዛሬ እንደማ ትቀየመኝ እምናለሁ! " አለች በባሏ ከንፈሮች እንደዋግምት ተስቦ የወጣው ውስጣዊ ስሜቷ፣ ቁና ቁና ያህል እያስተነፈሳት።

" ታውቂያለሽ ሩብያ፣ እኔ ላንቺ ብቻ ብዬ፣ በዚህ ዐይነቱ ኑሮአችን በሥቃይ እንደምኖር! ታውቂያለሽ! ያላንቺ ጠቅላላው ዐለምና ተፈጥሮ ከነዝግንትሉ፣ ምናምንቴ ዐይነት ነገር መስሎ እንደሚታየኝ! ታውቂያለሽ! እኔ የምመለከትሽ፣ በተራ መውደድ ሳይሆን፣ በተለየ ፍቅር እንደሆነ! በርግጥም ታውቂያለሽ፣ ብርሃንና ዐየር፣ እፀዋትና አዝርእት ሌሎችም የተፈጥሮ በረከቶች ሁሉ፣ አንቺ በሌለሽበት ወቅት ሁሉ ለኔ ምንም ዐይነት ትርጉም እንደማይሰጡኝ' ታድያንን ዛሬ ምን ነካብኝ ይሆን፣ እንዲህ ጣምኜ ስመጣ፣ ነፍስ ትዘራብኛለሽ ብዬ ሳስብ፣ ከደጅ የጠፋሽብኝ! " አለ፣ ፍቅር ባጕላላው አንደበቱ በመንተባተብና በደረቷ ላይ እንደበሰለ ብርቱካን ትምቡክ ትምቡክ የሚሉ መንታ ያጕበሩ ጡቶቿን እየዳሰሰ።

" አንተዬ እንዳትቀየመኝ ብዬሃለሁኮ! ጌታዬ፣ ሁለታችንም ብንሆን፣ ፍቅር አገብሮን እንጅ፣ በእንደዚህ ዐይነቱ ኑሮ መኖር እንደማንችል ብዙ ጊዜ ተነጋግረንበታል። የኔ ፍቅር ምንጊዜም ቢሆን ተከብሮልህ እንደሚኖር መሐላ አያሻውም። በሁለታችን መካከል ያለውን የፍቅር መተማመን፣ ከሁለታችን ሌላ፣ ማንም ሰው እንደማያውቀው ታምናለህ። ሌላው ቀርቶ፣ ወላጆቻችን እንኳ፣ ውጫዊውን ፍቅራችንን እንጅ ውስጣዊውን የነደደ ስሜታችንን አያውቁትም። እንዴውም… " ብላ ልትቀጥል ስትል፣ አንድ ነገር ትዝ አላትና " በሞትኩት! ጌትዬ አፈር በበላኝ! " ብላ

ይተሻሻት ከነበረው ሰውነቱ ላይ ተመንጥቃ፣ ወደ ቤት እየሮጠች ገባች። አልቆየችም፣ ትልቅ ቅል በሁለት እጆቿ ይዛ ወደ ደጅ እየመጣች " ሞት ይርሳኝና ጌትዬ ረሳሁህኮ! ለዛሬ የሚደርስ ጉሽ ጠላ ነበረኝኮ! ዛሬ ምን እንደነካኝ አላውቅም፣ ደክመህ ስትመጣ፣ ምንም ሳልልህ ቀረሁ!" ትሰጠዋለች።

ከመቀመጫ የሚያስነሳ ጠላ ኖሯል። ገፈት ገፈቱን አጥልላ፣ ሁለቱም ደጃቸው ላይ በተጋደመው ግንድ ላይ ቁጭ ብለው፣ ተራ በተራ እየተፈራረቁ፣ ያን የቅል ጠላ አሉት። ሁለቱም ጠላይቱን ከቀማመሱ በኋላ፣ በለመዱት ዐይነት መሳሳም፣ እርስ በርስ ተጨረ ማምተው ሲግጠጡ፣ ስልምልም ብለው ቀሩ። ቆይተው ቆይ ተው፣ ፍቅር የደበተው መንፈሳቸው እንደገና ሲመለስ፣

" አንቺዬ! ምንም ነገር ደብቀሽኝ እንደማታውቂ አውቃ ለሁ። ወደፊትም ቢሆን በዚሁ ባሕርይሽ እንደምትቀጥዪ አምና ለሁ። ዛሬ፣ በተለይ ዛሬ፣ የሆንሽው ነገር አለና፣ ሳትደብቂኝ ንገ ሪኝ! " ሲል ተማጠናት።

" አንተዬ! በኔና ባንተ የፍቅር መዝገበ-ቃል ውስጥ፣ ለም ሥጢር ቦታ የለውም። ግን ጌትዬ ቡዳ ነህ! አውቀህብኛል። ስብ ሰባቸው ነዝሮኝ ነው የመጣሁት። እኔን ሳይሆን አንዳንድ ሐሳቦቼን ጐሻሽመውብኛል። መለስተኛ ሽብርም ሞክሮኝ ነበር " አለች። የሆነችውን እፍረጥርጣ ልትነግረው እየተዘጋጀች።

" አንቺዬ፣ ለመሆኑ ብዙ ሴቶች ተሰበሰቡላቸው? ለመሆኑ እነዚህ ስብሰባውን የመሩት የሴቶች ካድሬዎች የት የሚኖሩ ናቸው? የትስ የተማሩ ናቸው? " ሲል ጠየቃት፣ ማምሻውን ሻጉራ አድርጓት የቆየውን ምክንያት፣ በስተዙርያ ለማውጣጣትና ለማወቅ ጓጉቶ። እሷም፣ ሲተሻሹ ላልቶ የወደቀውን መቀነት ከመሬት አንስታ እንደገና ወገቧን እያሸመች፣





" ጌትዬ ዘርዝሬ አጫውትሐለሁ! ቆይ መጀመሪያ ከጠላው ልድገምህ!" አለች። ባዶውን ቅል አንጠልጥላ ወደ ቤት ገባችና፣ ወዲያው ይዛ ከተፍ አለች። ቅሉን ለባሏ እንደሰጠች፣ ካጠገቡ ጠጋ ብላ ቁጭ አለችና የስብሰባውን ዝርዝር ሐተታ ትዘከዝከው ጀመር።

" ያልተሰበሰበ ያካባቢያችን ሴት የለም። ብቻ ሁለት ሴቶች 'ስብሰባው ላይ መገኘት የለብሽም ' በሚል የባሎች ተቃውሞ በተነ ሳው ጠብ ባገወራዎቻቸው ተፈንክተው እዚያ ማዶ ካለው የጤና ጣቢያ ተወስደዋል አሉ! " አለች ስትጀምር።

" አንቺየ! ደግ አላረጉም! ምናለ ቢፈቅዱላቸውና ቢሔዱ ኖሮ " አለ ባል።

" አንተም ሳታውቃቸው አትቀር፣ እነግራዝማች ውቤና እነአለቃ ፍስሐ ናቸው አሉ፣ ሚስቶቻቸውን የፈነከቱት " አለች መሣቅ እየሞካከራት።

" እሃሃሃ ያደርጋሉ! እነሱስ እንዲህ እንዲህ ያለው፣ የሴቶች ቅሥር ቅሥር ማለት አይዋጥላቸውም " አለ ከት ብሎ እየ ሣቀ። ወዲያው " ዛሬስ አንቺም ጠምቶሻልኮ፣ የስንቶቹን ዲስ ኩር ያለወትሮሽ ስትሰሚ ውለሽ " አለና ከቅሉ ሦስት አራት ጊዜ፣ በጁ እንደያዘ ጠላውን አስጐነጫት። እንደመብቃት ሲቃጣትም ለገታት።

" ለስድስት ወራት ለከፍተኛ ትምህርት መስኮብ ደርሰው የተመለሱ ናቸው አሉ፣ ስብሰባውን የመሩት የሴቶች ሹማምንት " አለች ሩቢያ።

" ስንት ነበሩ? " የሹማምንቱን ብዛት ለማወቅ? ባል ያቀረ በው ጥያቄ ነው።

" አምስት ነበሩ። ግን የሚገርምህ  አምስቱም ስለ ባላገሩ

ኑሮ የማያውቁ፣ ከተማ ውስጥ ተወልደው ያደጉ ናቸው አሉ ” አለች።

“ ታዲያ ስለባላገሩ ሴቶች ሁኔታ ምን አውቀው ነው፣ የገጠሩን ሴት ሰብስበው ሊያስተምሩ የመጡት? ” አለ ባል በቁምነገር።

“ አይ እሱስ እንኳ ሹማምንቶቹን ያስተዋወቁን ሴትዮ፣ መጀመሪያ ሲናገሩ፣ አምስቱም ሹማምንቶች በሞስኮብ ያጠኑት ትምህርት የገጠሩን ሴቶች የሚመለከት እንደነበርና፣ በሩሲያ በሚገኙ የገጠር መንደሮችም በመዘዋወር ሁሉን የገጠር ሴት ችግር ያጠኑ መሆናቸውን ገልጸውልናል ” አለች ሩብያ፣ እንደ መቅረፀ-ድምፅ ስትቀዳና ስትጠመጥም የዋለችውን ሁሉ መልሳ እየተረተረችለት።

“ አንቺዬ ታድያማ እንቅብና ሠፌድን ሲያመሳስሉ ውለዋል አትይኝም እንዴ!” አለ በስላቅ ውስጥ ውስጡን እየነካካ።

“ ጌትዬ፣ እንቅብና ሠፌድን ደግሞ ምን አገናኟቸው ነው፣ የምትጠቅስልኝ ” አለች፣ ሐሳቡ ይበልጥ እንዲብራራላት እየጐመዠች።

“ አዎ! እንቅብና ሠፌድ፣ እንዳልሽው በጭራሽ አይገናኙም። ቅርፃቸውም ሆነ አገልግሎታቸው ለየቅል ነው። ታዲያ የመስኮብ አካባቢ ገጠሮችና የኛዎቹ ገጠሮች ሁኔታ፣ በየመልኩ የሚለያይ ባሕርያት አሏቸው። በዚያ ስለሚኖሩት የገጠር ሴቶችን ሁናቴ አጥንቶ፣ ለዚህኛው ለኛው የገጠር ሴቶች መጠቅጠቅ፣ እንደሠፌዱና እንደ እንቅቡ ሆኔታ አይመሰል ብለሽ? የቆላና የደጋ ወፍ አይመሳሰል፣ ዘፈኑ እንኳ ለየቅሉ ነው! ደግሞምኮ..... ” ብሎ ሊቀጥል ሲል፣ አፉን በጇ እያመቀች





“ ቆይ ስማኝ እንጅ ጌትዬ! ገና አልጀመርኩምኮ፣ የስብሰባው ዋና እንብርት፣ የሴቶች ግላዊ መብት ጉዳይ ነው ብለው፣ ከሚስቶች የባል እግር ማጠብ አንስተው፣ እስከ ሴት ልጇ በሷ ስም መጠራት አለበት እሚለው ድረስ፣ አምስቱም ተራ በተራ እየተነሱ ሲሰብኩን ዋሉ ” አለችው።

“ ሩብያ፣ ይህ ዐይነቱ ጉዳይ ለኔና ላንቺ እንግዳ ነገር አይደለም። ሴቶች እኩልነታዊ ክብራቸው መጠበቅ እንዳለበት በያጋጣሚው ሁሉ ስንነጋገርበት ቆይተናል። እነ ግራዝማችንና እነ አለቃን፣ የጕዳዩ አስፈላጊነት ባይገባቸው ሌላ ጉዳይ ነው። እኔ ሓሳቡን ሙሉ በሙሉ እንደምደግፍ ደጋግሜ ነግሬሻለሁ። ታውቂዋለሽ። እንኳን በግል ትዳራችን ውስጥ የምናከናውነው ተግባር ሁሉ፣ በሁለታችን የመፈቃቀድና የመከባበር መንፈስ ላይ የተመሠረተ እንጅ፣ ባሕላችን የፈጠረው የታላቅነትና የታናሽነት ስሜት ተፅዕኖ እንዳይደለ አምነንበታል። ግን፣ መሠረታዊውን የባለትዳሮች እኩልነት ለማግዘፍ፣ አስቀድመው መዘጋጀት ያለባቸው የኑሮ ተግባራዊ ድርጅቶች አሉ። እነዚህ ተግባራዊ ድርጅቶች እስካልተሟሉ ድረስ፣ በዚህ ጉዳይ የሚነሣው ሙከራ ሁሉ፣ ባልና ሚስትን ይበልጥ ያሻክራሉ እንጅ፣ መድኅንነት አይኖራቸውም ” አለ።

“ ጌትዬ ልክ ነህ! አንዳንድ ተርብ የሆኑ ሴቶች፣ አሁን አንተ የጠቀስከውን ነጥብ አንስተው፣ በያካባቢው ወፍጮ ቤት ቢቋቋም፣ የውሀ አሸንዳዎች ቢተከሉ፣ የሕፃናት ማሳደጊያ ጣቢያዎች፣ ቢቋቋሙ፣ የመሳሰሉትም የኑሮ አስፈላጊ ድርጅቶች ቢዘጋጁ፣ እነሱ አበክረው የተናገሩለትን የሴቶች እኩልነት መብት ከሞላ ጐደል በሥራ ላይ ለማዋል በተሞከረ ነበር። ይህም ሁኔታ የተግባራት መፈራረቀን በባልና በሚስት መካከል መፍጠር አስችሎ፣ አንድን ተግባር ሴትም ሆነ ወንድ ሊሠራው እንደሚችል

በማረጋገጥ፣ ባሕሉ በዚህ ሳቢያ ያሣደረውን የበታችነትና የበላይነት ስሜታዊ ተፅዕኖ በጥቂት ቀኖች ውስጥ፣ ጨርሶ ማጥፋት እንኳ ባይሆን፣ ማሻሻል ይቻላል፣ ብለው ሐሳባቸውን ያቀረቡ ሴቶች ብዙ ነበሩ ” አለች ሳታመነታ።

“ ልክ ናቸው! በበሬዎቻችን ምትክ ትራክተር፣ በድንጋይ ወፍጮቻችን ምትክ የሞተር ወፍጮ.... በየመስኩም የተሻለ ተግባራዊ የመሣሪያዎች ለውጥ ቢኖር፣ የሚሉት ሁሉ ተግባራዊ ሊሆን በቻለ ነበር። በተረፈ ግን ባል፣ እንጀራ ቢጋግር፣ ወጥ ቢሠራ፣ ጠላ ቢጠምቅ፣ ወፍጮ ቢፈጭ..... እኔ አልቃወምም። ችግሩ ባሕላችን የለመደው፣ የቤትና የውጭ ሥራ አከፋፈል ሁኔታ፣ በሥራ ማከናወኛ መሣሪያዎች ሁኔታ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ፣ የመሣሪያዎቹ አለመለወጥ ባሕሉን ሊሽረው አለመቻሉ ነው የሚያሳዝነኝ! ” አለ ሚስቱን በተቻለ መጠን እኩያው እንደሆነች፣ መንገድ መንገዱን እያሳያት።“ እኛ እንኳ የቤቱ እኩል አዛዦች ነን! ” አለ።

“ አንተዬ! እኛ ጠላችንን እየተጐነጨን የቀኑን ወሬ ስንደልቅ፣ በሬዎቹን ረስተናቸዋል ” አለች፣ ልጧ ከበፊቱ ይልቅ ረገብ እያለ።

“ አይ ሩብያ! የኛ ነገር ያሳዝናል! በሬዎቹ አይናገሩ፣ እንዲያ ሲደክሙ ውለው በማረፊያቸው ሰዓት፣ ከነቀንበራቸው አቁመን አሠቃይተናቸው ኖሯል ” አለና ወዲያው ብድግ ብሎ ይፈታታ ገባ። ወዲያውም፣ ሩቢያ እቃዎቹን አግብታ ቤት እንዳስቀመጠች፣ ከግርግም ውስጥ የሳር ድርቆሽ ለበሬዎቹ እንዳላዘጋጀች ትዝ ኣላትና፣ ስትበር ወደ ሣሩ ክምሮች ሮጠች። ሣሩን በወቅቱ በግርግሙ ውስጥ አለማዘጋጀቷን ባሏ በመመልከቱ፣ ተጨማሪ ቀኑ የፈጠረው ኣዲስ ሁኔታ መሆኑ ተሰማው። “ ዕለታዊ ምድብ ተግ





ባሯን እንዳትሠራ ፣ ስብሰባው ላይ ምን መክረዋት ይሆን? ” እያለ እንደገና ያሰላስል ጀመር። በዚሁ ሓሳብ ላይ ተመሥጦ፣ የዕለቱን ስብሰባ በማስመልከት፣ ሚስቱ ያሳየችውን ጥቂት የተግባር ግድየለሽነት ሁኔታዎች ያወጣ ያወርድ ጀመር። በልቡም እንደ መተከዝ ብሎ “ ለወትሮዋ ከርሻ ስመለስ ከደጅ ተገኝታ ትቀበለኝ ነበር፣ ለወትሮዋ የመቀበያ መጠጥ አዘጋጅታ ትጠብቀኝ ነበር፣ ለወትሮዋ ሲያርሱ ለዋሉ በሬዎቻችን፣ ድርቆሽ ሣር በግርግሙ ወስጥ ታዘጋጅ ነበር። ዛሬ ምን ነክቷት ይሆን እነዚህን ተግባሮች ችላ ያለቻቸው? ነገር አለ! እነዚያ ከመስኮብ ተምረው የመጡ የስብሰባው መሬዎች፣ የመስኮብ አከባቢ የገጠር ገበሬዎች ሚስቶች፣ ለባሎቻቸው እንደዚህ ያለውን ተግባር ኣያደርጉምና፣ እናንተም ለባሎቻችሁ ኣታደርጉ፣ ይህን መሳይ ተግባር ብታከናውኑ፣ የሴትነት መብታችሁንና፣ ከወንድም ጋር እኩል መሆናችሁን ይፃረርባችኋል ብለው ነግረዋት ይሆን? ” እያለ የምሽቱን ሁኔታ እያብላላ ይጨነቃል። ሩብያ ቋጥኛ የሚያህል የሣር ድርቆሽ በኬሻ ጠቅልላ፣ በመጫኛ የጠፈረችውን ኣዝላ ወደ ቤት ለመምጣት ስትዘጋጅ፣ከድርቆሹ ክምር ሳር ላይ ቁጭ ብላ፣ እንደባሏ ውስጥ ውስጧን ጭንቀት ያኙካት ነበር።

“ ዛሬ ባሳየሁት የተግባር ቸልተኛነት ታዝቦኝ ይሆናል። ምን ላድርግ! እኔ ራሴ ኣውቄ የፈጠርኩት ኣይደለም። በጆሮየ ሲጠቀጠቅ የዋለው የሴት ሹማምንት ምክር ጤና ነስቶኝ ነው ያመሸሁት። ይቅርታ እንዲያደርግልኝ እጠይቀዋለሁ። እሱ ለኔ ሲል፣ ፍቅር አስገድዶት ከሞቀ የከተማ እናት ኣባቱ ቤት ተሰዶ፣ የመምህርነት ሥራውን ትቶ በተራ ገበሬነት ሲቆራመድና ሲማቅቅ ኖሯል። እኔ መሠረተ ምክንያቶቹ በሥርዓት ባልተጠኑ፣ በመስኮብ መንፈቅ በተማሩ የሴቶች ሹማምንት የስብሰባ ምክሮች፣ መሸ

በርም ሆነ መነዳት የለብኝም። እሱን የማከብረው ለሰጠኝ ሙሉ ፍቅሩ ስል እንጅ፣ በወንድነቱ ባሕላችን ባስገኘለት የበላይነቱ አይደ ለም። እኔን ብሎ ከኔ ተቈራኝቶ በገጠር ሲማቅቅ የኖረው፣ ፍቅር ባስገኘልን መተሣሠር እንጅ ከተማ ገብቶ ከዚህ የተሻለ ኑሮ መኖር አቅቶት አይደለም። እኔን የገጠሪቱን ልጅ ከነሳዱላዬ በማፍቀሩና ሚስቱም እንድሆነው በመወሰኑ፣ ወላጆቹ “ ዐይንህ ላፈር ” ብለው ረግመው ዳግመኛ ላይገናኙት ከወሰኑ ዐመታት አልፈዋል። በፊት አስተማሪ ሆኖ ገጠር ሳለ አውቆኝ፣ ኋላም ለዘመቻ ሲል መጥቶ አግብቶኝ እንኖራለን። እሱም እኔን ሲል፣ የተወለደበትና ያደገበትን ከተማ እርም ብሎ ትቶ፣ ይኸው በገጠር ገበሬነት ሲን ገላታ ዘመናት አልፈዋል። ዘመዶቹም በሙሉ፣ “ መድኃኒት አድር ጋበት ነው፣ አስደግማበታለች ” እያሉ የማይደረድሩብኝ ሐሜት የለም። እኛ ግን ሁኔታውያን አገናኝተውን በእውነተኛ ፍቅር ተሳስ በን የምንኖር ነን። ለፍቅረኛ ከእኩልነት ላይ የመነጨ ፍቅርን ከመ ስጠት የበለጠ ሌላ ስጦታ የለም። በዕለት ተግባርም ሆነ በሌላ ሁኔታ፣ በፍፁም ቅንነት የምንረዳዳው፣ ከዚሁ ከፍቅራችን ላይ በመ ነጨ መንፈስ አማካይነትና አስገዳጅነት ነው። እኔን ከተራ መሐይ ምነት ሞርዶ ሞርዶ፣ ከአከባቢዬ ባለው አስተሳሰብ አንፃር አዋቂ አድርጎኛል። ፊደል የማላውቀውን ሰው፣ ዛሬ መጻፍና ማንበብ አስችሎኛል። ከዚህ ሁሉ ይልቅ፣ ስግብግቦችን ብቻ አቅፎና አንደ ላቆ በሚኖር ዐለም ውስጥ፣ ለንዋይ መንሠፍሠፍ ሐሳብና ጭን ቀት በሌለበት ነፃ ሕይወት ውስጥ በገጠር ጎጆአችን የተደበቀች ኑራአችንን በሰላም እንኖራለን። ያው ያካባቢን ጭቁን ሕዝብ ያስ መረረውና ጭንቁም ያሠቃየው የኢኮኖሚና የእድገት ኋላ ቀርነት በኛም ላይ ይጫወትብናል እንጅ፣ በሁለታችን መካከል ያለው የባ ልና ሚስት ሰላም ምን ጊዜም መናጋት የሚችል አይደለም። ካቅ





ማችን በላይ በሆነው ባከባቢው የኑሮ ችግር ግን ሕዝቡ እንደ ሆነው እንሆናለን። እኩልነት በሥራ መከፋፈል ላይ የሚመሠረት ከሆነም፣ ሰባኪዎቹ እንዳሉት እኔን ላይመለከት ነው። ጌትዬ፣ ከእንቅልፉ ሌሊት ተነስቶ፣ ወፍጮውን ሳይቀር የሚረዳበት ጊዜ ጥቂት አይደለም። ጊዜ ካለው፣ እኔ ጥጥ ስፈትል ሲያይ፣ እሱ ያዳውራል። እኔ ሊጥ ሳቦካ፣ እሱ ውሃ ይጨምራል። እንጀራም ሳስስ፣ አክምባሎ ይደፋል። ድስት ጥጄ እንደሆነ እንጨት ይቆሰ ቍሳል። ለሙቀጫውም ከሆነ፣ የምነጠቀመው በሁለት ዘነዘናዎች ነው። ልብስ አጠባ ዥረት የወረድን እንደሆነ፣ እኔ ሳሽ፣ እሱ ይረግጣል። እኔ ሳሰጣ እሱ እንዶድ ቆርጦ ይቀጠቅጣል። የምንጠ መዝዘውም፣ የልብሱን ጫፍና ጫፍ ይዘን ነው። የቤታችንን ወለል አዛባ ስለቀልቅ፣ እሱ መደብ መደቡን ይዞ እንደሆን፣ እኔ ወለል ወለሉ ይደርሰኛል። ኧረ ምን የሚቀረው የቤት ሥራ አለ? ..... ” በሐሳብ ሰምጣ ድርቆሹን ለበሬዎቹ ማምጣት ዘንግታ ቁጭ ብላለች። ባሏ ሣር ለማምጣት እንደሔደች ጠርጥሮ፣ ወደ ክም ሮቹ ሲሮጥ ቢሄድ ድርቆሹን በሚገባ በኬሻ ጠቅልላ አዘጋጅታ፣ ካጠገቡ ቁጭ እንዳለች ያገኛታል።

“ ምን ሆንሽ ዘገየሽ? ” አሁንም የዕለቱን ጥርጣሬ ለማው ጣጣት ነው።

“ ኧረ ተወኝ፣ ዛሬ በሐሳቤ የማይወጣ የማይወርድ ነገር የለም! ” አለች።

“ አዎ እኔም ተሰምቶኛል! ነገ ደግመሽ ከስብሰባው አት ሔጅም ”

“ደግሞ ምን ላደርግ! ዛሬ የረበሸኝ አነሰኝ እንዴ! ” ደረቱ ላይ ጠጋ ብላ በመለጠፍ “ ጌትዬ፣ ዛሬ ይቅርታ እንደም ታደርግልኝ አምናለሁ። ለወደፊቱ ግን አይለምደኝም! ” ትለዋለች

ጉንጮቹን እንደተለመደው እየዳሰሰች።

" ለመሆኑ ምን ዐይነት ስሜት ኣሳደሩብሽ ይሆን? " አለ፣ የሆነችውን ለማወቅ።

" ኧረ ድራሽባቸው በጠፉ- ደርሰው የሴት መብት እኩልነት፣ ፍትሕ...... እያሉ ያልተጨማለቁት የለም። በርግጥ ኣዲስ ለውጥ መጥቷል የሚሉን ከሆነ፣ ከነዚህ ሁለተኛ ደረጃ ችግሮቻችን ይልቅ፣ በተቀዳሚ ሊደረጉ የሚገቡትን ነገሮች ባዘጋጁልን ነበር! የኩልነቱን ጉዳይ እኛው በየቤታችንና በየኣደባባዩ ራሳችን በራሳችን እናስተካክለው ነበር። እሱን ትተው፣ ሲመጠምጡን የሚያድሩትን ቅማሎች፣ ቁንጫዎች፣ ቱሐኖች የምናጠፋበትን መድኃኒት በሰጡን! የተዘራውን እህል ሳይቀር የሚያወድሙብንን ኣይጦች፣ አይጠ-ሞገጦች፣ ጃርቶች፣ ቁራዎች፣ የምናጠፋበትን ዘዴ ባዘጋጁልን! እንደልብ የምናነደውን ማገዶአችንን ባልከለከሉን! ለራስ ምታት፣ ለጉንፋን በሽታችን መከላከያ ኪኒና በሰጡን! ለገበሬዎች ኑሮ እንደዋልታና ምሠሦ የሆኑትን ሚስቶቻቸውን ከማነሳሳት ይልቅ፣ በግርድና፣ በሴተኛ ኣዳሪነት፣ በዕቁባት ቅምጥነትና በመሳሰሉትም ችግሮች የሚሰቃዩትን እህቶች ነፃ ለማውጣት ተቀዳሚ ርዳታ ባደረጉላቸው ነበር። እነሱ ባቀረቡት ሐሳብ እንኳ ቢሆን፣ በአስፈፃሚነትም ሆነ በመካሪነት፣ ከነሱ ይልቅ የተሻሉና ችግሩንም በቅርብ የሚያውቁ፣ ከዚሁ ከገጠሩ የተመረጡ ሴቶች ይበልጥ፣ ችግሩን ለመፍታት በቻሉ ነበር! ......

" እምቧ! እምቧ! እምቧ! ... " የተራቡ በሬዎች በግርግም ውስጥ ሣር ባለማግኘታቸው አቤቱታ ማቅረባቸው ኖሯል። ባልና ሚስት ተቃቅፈው ከነበሩበት ከድርቆሹ ክምር አጠገብ፣ የበሬዎቹን ጩኸት በጨረፍታ ይሰማሉ።





" ዛሬ በይበልጥ የተበደሉት በሬዎቻችን ናቸው! " አለ ባል፣ ቶሎ እንዲሔዱ ሚስቱን እያጣደፈና በኬሻ የተጠቀለለውንም ሣር በትከሻው እየተሸከመ።

" ምን ዐይነት፣ ሐሳብ የሚሰርቅ ጣጣ ፈጠሩብን? " አለች ሩብያ ሣር ለበሬዎች ልታመጣ ሔዳ፣ አንድ ሰዓት ያህል ክምሩ አጠገብ በሐሳብ ሰጥማ ቁጭ ብላ መዘግየቷን እያስታወሰች። ከቤት እንደደረሱም፣ ምሽቱ ደንገዝገዝ ብሎ ኖሮ፣ ሩብያ ኩራዝ ለመለኮስ ስትጣደፍ፣ ባሏ ለተራቡ በሬዎቹ ያመጣውን ድርቆሽ፣ ከግርግማቸው ውስጥ ያስቀምጥላቸዋል። ሩብያም ኩራዙን ለኩሳ ከመስቀያው ላይ ካስቀመጠች በኋላ፣

" ጌትዬ፣ ዛሬ መቼም ሳትታዘበኝ ኣልቀረህም!" ትለዋለች።

" አዎ ነካክቶኛል! " ይላታል ሣቅ እያለ።

" ቆይ ዝምበል! የምን ስብሰባ! ሁለተኛ ንክች አላረጋትም! " ትላለችክልቧ መሆኑን፣ በከንፈሮቿ ሳሚያ እያረጋገጠችለት።

" ደግሞ፣ አልተገኘችም ብለው ችግር እንዳይፈጥሩብን! " ይላል ባሏ እንደማቅማማት እየሞከረው።

" የሚያደርጉትን ያድርጉ! እኔና አንተ እኩል እንደሆንን፣ ከኔና ካንተ ይበልጥ እነሱ አያውቁም!" አለች፣ ከምድጃው አጠገብ ካለው መደብ ላይ፣ ከድርቆሹ ጉዝጉዝ አድርጋ ደላገው እያነጠፈች። " እነግራዝማችን እነፊታውራሪን እነካብትሼን እነአመቴን " ይምከሩ።

" መጠንቀቅ አለብን እንደሕዝቡ ካልሔድን ሌላ ችግር ሊመጣብን ይችላል " አለ ባል፣በያጋጣሚው የሆነውን እየተረከላት።

" ጌትዬ! ውሃው እንደወትሮው ባይሞቅም፣ እግሮችህን

ላጥብ ነውና ተዘጋጅ!" አለች፣ በጇ የማሰሮውን ውሃ እየፈተሸች።

" ሩብያ፣ ውነቱን ንገሪኝ! የባሎቻችሁን እግሮች እንዳታጥቡ ብለዋችሁ የለም እንዴ ዛሬ! " እያሸፈ የልቡን መጠየቁ ነበር።

" አንተ ምስጥኮ ነህ! ጌትዬ በምን አወቅኸው! እንዴውም የኩልነታችሁ መፈተኛ ማረጋገጫ ነውና፣ ዛሬ ማታ እንደተመለሳችሁ፣ የባሎቻችሁን እግር እንዳታጥቡ ብለው አስጠንቅቀውናል" አለችው በሣቋ እያስካካች።

" አዎ ጠርጥሬአለሁ! ውሃው ዛሬ አለወትሮው በደንብ አልሞቀም አልሽ፣ ምን ውሃው ብቻ፣ ዛሬ አለወትሮው በደንብ ያልሆነው ውሃው ብቻ አይደለም... " ይላታል፣ በነገር እየነካካት።

" በል እግርህን አምጣ " ትለዋለች? ከማሠሮው ውሃ በብረት ድስት ላይ ቀንሳ እያዘጋጀች!

" ሩብያ! ቆይ የመስኮብ መምህሮችሽን ቃል ለማክበር፣ እኔ መጀመርያ አጥብሽና ኋላ ደግሞ አንቺ በተራሽ ታጥቢኛለሽ። ተስተካከልን ማለት አይደል? " ይላታል ከነበረችበት ቦታ ታቅፎ አንስቶ ለሱ በተዘጋጀ የመደብ መቀመጫ ላይ እያስቀመጠና፣ እግሮቿን ወደ ተዘጋጀው የግር ማጠቢያ ገበቴ እየጐተተ።

" ለኛ ይኸ አዲስ ነገር አይደለም! ሁልጊዜ የምናደርገው ነው!" አለች ሩቢያ መደቧ ላይ እንደተቀመጠች ባሏ ዝቅ ብሎ እግሯን ሲያጥብ።

" ሩብያ! ሩብያ! " ከውጭ የሴት ድምፅ ጥሪ ይሰማል።

" ማነሽ!" ትላለች እንደተቀመጠች ባሏ እግሯን ሲያጥብ።

" ሩብያ! በሩን ክፈችልኝ!እኔ ነኝ! " ይላል የውጭ የሴት ድምፅ።

" አትናገሪም እንዴ! ማነሽ! " ትላለች አንደኛው እግሯ





መታጠቡ አብቅቶ፣ ሁለተኛው ሊጀምር ሲል፣ ከመቀመጫዋ ላይ እንዳለች ባሏ በሩን ሊከፍት ይሔዳል። ሲከፈት ቢያዩ፣ ከነሱ ማዶ መንደር የምትኖር የሩቢያ ወዳጅ ሆና ያገኟታል። እንግዳዪቱም ገብታ ከሩብያ አጠገብ እንደተቀመጠች፣

" ደኅና አይደለሽም እንዴ፣ በምሽት የመጣሽው? " ሩብያ ትጠይቃለች።

" አንቺ የታደልሽ አለመኛ ነሽ! እንዴውም ይኸው ባልሽ እግርሽን ያጥባል፣ እኔ ዛሬ ለምን ስብሰባ ሔድሽ ብሎ፣ ሊገድለኝ ሲሞክር፣ በታዛ ዘልዬ ነው አምልጨው የመጣሁት። ይኸውልሽ በጉማሬው የገሸለጠኝ! " ብላበጀርባዋ ላይ ያጐረበጠውን የጉማሬ ሠንበር ታሣያታለች።አልቆዩም፣ ይህንኑ ጨዋታ ይዘው፣ ጉሽ ጠላቸውን እየከሰከሱ ሲያወሩ፣ ሌላ የሴት ድምፅ ከደጅ ይጣራል።

" ሩብያ! ኧረ ሩብያ! ሩብያ! " ትላለች አዲሲቱ እንግዳ።

" ማን ልበል? " ይላል ባሏ ድምፁን ከፍ አድርጎ።

" እኔ ነኝ ክፈቱልኝ!" ትላለች።

" ደኅናም አላመሸሽ " ይላል ባል በሩን እየከፈተ። ለካስ ይህችም እመቤት ተመሣሣይ የዕለቱ አጋጣሚ ደርሶባት ያባወራ ዱላ ቀምሳ ያመለጠች፣ ከማዶው ባሻገር ባለ ዠረት አጠገብ የምትኖር፣ የሩብያ አብሮ አደግ ጓደኛዋ ኖራለች። ከላይዋ ላይ ያንገት ልብስም ሆነ ነጠላ አልደረበችም። እንዴውም ከምሽቱ ግብ ግብ የተነሣ፣ ባሏ ቀሚሷን ሳይቀር አራት ቦታ ላይ ከላይ እስከታች ተርትሮባት፣ አዶከብሬ ያሳበዳት ወፈፍቱ መስላ ነው የመጣችው። ቀደም ሲል እነሩብያ ቤት፣ ለሸሸት የመጣችውም አብሮ አደግ ጓደኞች በመሆናቸው፣ ገና በሩን ስትገባ የቀሚሷን መቀዳደድ አይታ ሳቋን ለቀቀችው። የጐንና የጐን ሸንጧ ወለል ብሎ ይታያል። የበስተፊቷና የበስተኋላዋማ፣ ሆነ ብሎ የሠሩት ይመስላል።

አፈማገፀኳና ኩስ አምባዋ " እዩኝ! እዩኝ! " የሚል ሆኖ እንዳ ቀረቡት ትርዒት መስሎ ፈጥጦ ይታያል። ደግነቱ ሁሉም ከልብ የሚተዋወቁ በመሆናቸው፤ የዐካሏን ሁለንተና በሚያሳይ ሁኔታ በመምጣቷ፤ አልተፋፈሩም። ሣቃቸው ግን የቤቷን ጣራ ቀድዶ ሊወጣ ምንም አልቀረውም ነበር።

" በጣም ደበደበሽ እንዴ " ትላለች ሩብያ ሣቃቸው ጋብ ሲል።

" ምንም አላስተረፈኝ! " ትላለች እንግዳይቱ፤ ጥብጣብ በመሰለ መልክ በተቀዳደደው ቀሚሷ ውስጥ የቆሰለችውን እያሣየች።

" እሱ ነብርኮ ነው! ዛሬ ስብሰባው ላይ ስሙም ተነስቶ ነበር " አለች ሌላይቱ ለሽሽት ቀደም ብላ የመጣችው ጓደኛቸው።

" ስብሰባው ላይ እንዳትገኝ አልነገረሽም ነበር? " አለ ባል።

" በጣም ስለፈራ፤ ሒጂም ቅሪም አላለም! ያው ትዕዛዝ በመሆኑ፤ ጠዋት ለጉዞው ስዘገጃጅ፤ ፊቱ ተኰማትሮ፤ አይ መስሉ መስሎ ነበር! " አለች ሁኔታውን እየገለጠች።

" ታዲያ ጠዋት ዝም ብሎ ለቆሽ፤ አሁን ምን ሁኚ ነው የሚልሽ? " አለች ሩብያ፤ ሣቋን እየቀጠለች።

" እግሬን እጠቢኝ! ብሏት ይሆናል! " አለች ሌላዪቱ ሽሽታ የመጣች ጓደኛዋ፤ በራሷ ላይ የደረሰውም ትዝ እያላት።

" አለሽ እንዴ! " አለች ሩብያ እያሟሟቀች።

" ኋላሳ! " አለች እንግዳዪቱ፤ የምሽቱ ሁኔታ እየታያት።

" አጅሬት እምቢ ብለሽው ይሆናል! " አለ የሩቢያ ባል።

" ምን በወጣኝ ንክች አላረገውም!ዛሬ ቀን ወጥቶልናል! ባሪያው አድርጐ እንደፈለገው ሲረግጠኝና ሲነዳኝ ኖሯል!





ይበቃዋል! እድሜ ለሴቶች ሹማምንት! ዛሬ ሲያስተምሩን ውለ ዋል! የምን አዛዥነት? የምንስ እግር ማጠብ? ነፃ ወጥተናል። ክብሩን ጠብቆ መኖር ባይፈልግ፤ ዋጋውን የገጠር ማኅበር ይሰ ጠዋል፤ አለያም የመፍታት መብቴ የተጠበቀ ነው! የትም ሠርቼ አድራለሁ!....." አለች፤ የምሽቱ ዱላና፤ የባሏ ግብግብ እጅግ አስመ ርሯትና አበሳጭቷት። በርግጥም ባሏ የታወቀ አክብሩኝ ባይ፤ የቀበ ሌያቸው ጉረኛ ሰው ነው። ድሮም ቢሆን አብዛኛው የባላባት ልጅና የነፍጠኛ ውላጅ ቀብራራዎች ናቸው። ተጀምሮ እስኪ ጨረስ፤እንኳንስ ለሴት፤ ላልመሰላቸውም ወንድ፤ ፊት አይሰ ጡም። የዚያን ዕለቱ የስብሰባ አፈና፤ ያጨለመባቸው ሰዎች ቢኖሩ፤ በእነዚያ መሰሎች ትዕቢተኞችና እብሪተኞች ላይ ነው። ተራውና ጭቁኑ ገበሬ ግን፤ ሚስቱን የሚመለከታትም ሆነ የሚያከብራት፤ ዝቅ ሲል እንደእህቱ፤ እንደሚስቱ፤ ከፍ ሲል እንደ እናቱ ነው። አልፎ አልፎ፤ መጥፎ ባሕሪ የተጣላው፤ ሚስ ቱን ፍፁም ታዛዥ አድርጐ በበላይነት ስሜት ሲያጕላላት የሚገኝ ቢኖር፤ ቍጥሩ እስከዚህም አይደለም። በተረፈ ግን፤ ራሱ የግብ ርናው ዝቅተኛ ኑሮ ተባብሮ መሥራትና መከባበርን የሚጠይቅ በመሆኑ ለመናናቅ ዕድል አይሰጥም። ስለሆነም ፍቅራቸው የእኩ ልነታቸው ምልክት ነው። ሰው ሠራሽና በትዕዛዝ የተገኘ መከባ በር ሳይሆን፤ ከልብ የመነጨ ፍፁምና ተፈጥሮአዊ የሆነ መቀራረብ ነው ያላቸው። በነግራዝማችና በነአለቃ ቤት ያለው የኑሮ መልክ ቅይር ስለሆነ፤ ምናልባት የስብሰባው መብረቅም ሆነ ነጐድጓድ፤ በነሱ አካባቢ ተአምር ይሠራ ይሆናል። የነዚያ መሰሎቹ ባለትዳ ሮች፤ ስለሚስቶቻቸው ያላቸው ስሜት ብቻ ሳይሆን መላ ያስተሰ ሰብ ባሕርያቸው መለወጥ እንዳለበት፤ ሀገር የሚያውቀውና የሚያምንበት ነው። ሚስቱን ሲደበድብ ያመሸ አባወራ ሁሉ፤

የነዚያ ምጥን ቤተ-ሰቦች ዝርያና ዘርፍ ያለው ነው። በነዚህ አካባቢዎች ላይ የሚሽከረከሩ ሐሳቦችን፣ አራቱ ሰዎች ቁጭ ብለው፣ ያንን ጉሽ ጠላቸውን እየቀመቀሙና፣ ያጋም እንጨት እሳታቸውን እየከሰከሱ፣ ይደልቁት ጀመር።

" እኛ ደጃዝማች ምን ውጧቸው ይሆን? " አለች ሩብያ፣ ያውራጃው ሕዝብ ባላባት ትዝ እያላት። ከዛያ ያላነሱ የሴት አገልጋዮች አሏቸው።

" ካብትሼ ነፃ ወጣች አትይኝም እንዴ! እንዲያ የደጃዝማች ዘመድ በሞተ ቍጥር፣ ደረቷን ለመቤቷ ገልጣ በመስጠት በየልቅሶው ላይ ስታስደበድብ የምትውለው! " አለች መጀመሪያ ሽሽታ የመጣችው የሩብያ ጓደኛ።

" እንደክብር ነበርኮ የምትቆጥረው! " አለች ሌላይቱ ጓደኛዋ።

" የምን ክብር እቴ! እሜቴም እንግዲህ የራሳቸውን ደረት ገለጥለጥ አርገው መደብደብ ሊኖርባቸው ነው! " አለች ሩብያ።

" እንደነሱ ላሉት ሁሉ፣ ስብሰባው የለብታ ጠበል ነው። ሌላው ቢቀር ደረታቸውን በሌላ ሰው እጅ የመደብደብ በሽታ ይፈውሳቸው ይሆናል! " አለ ባል፣ ጠላውን እንዲጠጡ፣ የምሽቱን ሁለት ድንገተኛ እንግዶቹን እየጋበዘ። ቀጠልም አድርጎ፣ " ሩብያ ብዙ አላጫወተችኝም። ድው ብሏታል። ስብሰባችሁ እንዴት ነበር? " አለ ባል፣ ሁለቱን እንግዶች፣ ስለቀኑ ሁኔታ ይበልጥ ለማወቅ እየቋመጠ።

" ልቤ ነው የረካው! " አለች ሁለተኛ ላይ የደረሰችው እንግዳ። ዱላው አስደንግጧታል እንጅ፣ ጨዋታ የምትወድ ትመስላለች። ስትናገርም ፎለፎል ናት። ልቤ ነው የረካው! ሴትነቴን ካወቅሁበት ጊዜ ጀምሮ እመኘው የነበረውን ሐሳቤን ነው የሰብሰ





ባው መሪዎች ሲናገሩ የዋሉት። እኛ ሴቶች በገዛ ራሳችን ፍቅር፣ የምንወደውን ፍቅረኛ እንኳ እንደፈለግነው ማነጋገር አንችልም። እኛ ሴቶች፣ ያልተጫነብን የቤት ሙያ የለም። እንፈትላለን- ለማልበስ፣ ወለል አዛባ እንለቀልቃለን - ለማኖር፣ እንፈጫለን፣ እንወቅጣለን እናልባለን እንጋግራለን - ለመመገብና ሕይወት ለመስጠት። ሌላው ቀርቶ፣ የወንዶች ስሜት ሲነሣ እንጅ፣ ስለኛ ስሜት ምንነት ተነግሮም ሆነ ተከብሮ አያውቅም። የቤት ራስ ወንድ ነው እየተባለ፣ ፈላጭ ቆራጭ፣ አድራጊው ፈጣሪው ባል ብቻ ነው። እስታውሳለሁ አምና፣ ዶሮ የሚያርድ ወንድ ጠፍቶ ፋሲካን በደረቁ አሳልፈናል። ኸረ ስንቱ ተነግሮ፣ ሴት ተሳስታ የወንድ ሱሪ አጥልቃ ብትገኝ፣ ያያት ሁሉ ያመናጭቃታል። ከተሜዎች እንኳ በዚህ በዚህ ተለማምደዋል። እኛ ገጠሬዎቹ...." ብላ ልትቀጥል ስትል፣ የሩብያ ባል ነገሯ ከንክኖት አቋረጣትና፣

" የተናገርሽው ትክክል ነው። በተለይም ወንዶችንም ሆነ ሴቶችን የሚመለከት አንድ ነጥብ አንስተሻል። ከተሜዎችና ገጠሬዎች ያልሽው ነው። ሁለት ፍፁም የተለያዩ ቦታዎች ናቸው። እንደየአካባቢያቸው የሥልጣኔ ከፍታና ዝቅጠት፣ በውስጣቸው የሚርመሰመሰው ሕይወትና የኑሮ ዐይነት ይለያያል። ከተሜዎችኮ፣ ባይንዛዛም ያዲሱን ስልጣኔ ገፈት ቀማምሰዋል። ሳይንስ ባስገኘውም ሚሳይ፣ ባይበዛም ተጠቅመዋል። የሥራቸው ዐይነት፣ የሚሠሩበት መሣሪያ፣ የመጓጓዣው፣ የገበያው፣ ሌሎችም የኑሮ አስፈላጊ ነገሮች ሁሉ ከኛ ከገጠሮቹ ይልቅ ይበልጥ የተሻሻሉና የተሟሉ ናቸው። ይህ ሁኔታ በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለውን ልዩነት ብቻ ሳይሆን፣ በከፍተኛና፣ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ መካከል ያሉትን ልዩነቶች፣ ከኛ ከገጠሬዎቹ ይልቅ ያጠብላቸዋል። አንዱን የከተማ ደሀ፣ ገጠርኮ እንደሀብታም አድርጎ የሚያይበት ጊዜ አለ

ከራሱ የገጠር ኑሮ ሁኔታ ጋር እያስተያየው! ከተሜዎች፣ ‘ ከገጠር ንብ የከተማ ዝንብ ይሻላል ’ እያሉ ይተርቱብንስ የለ? ስለዚህ ነገሩን በየመልኩ ካየነው ይበልጥ ሲገባንና መፍትሔ እኛው ራሳችን ልንፈልግለት እንችላለን። ደግሞም.... ” ብሎ ሲቀጥል ሲል ሌላዋ አቋረጠችው።

“ ምነው እባክህ፣ ጉዳያችንን ወደ ከተማ ትወስድብናለህ? እኛ የምናወራው፣ ስለኛ ራሳችን ጉዳይ፣ ስለባሎቻችን አምባገነንነት፣ ጠዋት ማታ፣ ፋታ ስለነሳን የቤት ሙያ ተግባራችን፣ በፍልጥና በጉማሬ በየቀኑ ስለመደብደባችንና ስለመሳሰለው ነው። ከተማ ምን አስሔደን። የኛን የራሳችንን የቤታችንን መራራ ኑሮና ጉዳት ከተናገርን መቼ አነሰን! ተሠቃይተናልኮ..... ምነው አንቺየ! ያንን ውሀ ለመቅዳት እንስራችንን አዝለን ወደ ዥረት ስንወርድ የምንዘፍነውን አታመጭልኝም!” ብላ ለሩብያ ባል እንዲያሰሙት ትጐተጉታቸዋለች። ያንን ጉሽ ጠላ፣ ከደረሰባቸው የምሽት ብስጭት ጋር ሁለት ሦስቱን ቅል ጨላልጠው ስለነበር የልባቸውን ለመናገር፣ ማደፋፈሪያ ሆኗቸዋል።

“ ልክ ነሽ! እናሰማዋለን ” አለች ሚስቱም ከሁለቱ እንግዶች ጋር ተደርባ።

“ የማዳውርበት ጭኔ ተመላልጧል፣
 ውሃ እምቀዳበት ጀርባዬ ተግጧል፣
 የምሸከምበት ትከሻዬ ጐብጧል፣
 ሳፈላ፣ ስቀቅል፣ ስቆላ ስጋግር፣ ያ ዐይኔ ሞጭሙጨዋል፣
 ባሌ የሚገርፈኝ ሰውነቴ ሟልጧል፣
ይህን ሁሉ ሆኜ እንዳለሁት አለሁ።
ቀን የሚያስገኘውን በተስፋ እየጠበቅሁ።---- ” የሚለውን ዘፈን፣ በዚያ በጉሽ ጠላ ፈረሳቸው ሲያረግዱበት ጊዜ፣ ያ የነሩብያ ሰቀላ





ቤት የሠርግ በዓል የሚከናወንበት ትልቅ ዳስ መሰሎ፣ በሴቶቹ እስክስታ አበደ። ሦስቱም ሴቶች ተነስተው፣ የኩራዝ ላምባ ብልጭ ብልጭ እያለ፣ ባበራው ወለል ላይ፣ እስክስታቸውንና ዘፈናቸውን ያቀልጡት ጀመር። ረዢሙን ዘፈናቸውን ባጭር ሙናየ ተኩትና፣

 “ አህያ መጣች ተጭና ማር
 አባወራዬ በል ደኅና ደር!
አህያ መጣች ተጭና ስኳር፣
ወንድና ሴቶች እንከባበር።
 አህያ መጣች ተጭና ኮሦ፣
 ምን ይዋጣቸው እናስገብር ሲሦ!
አህያ መጣች ተጭና ፌጦ፣
ባልነት ቀረ ዐይንን አፍጦ።......” እያሉ ይደልቁት ጀመር። ሩብያም፣ አዛባ የምትለቅምበትን ገረወይና አምጥታ ከበሮዋ በማድረግ፣ ባሎቻቸው ካስመረሯቸው ሁለት ጓደኞቿ ጋር ገጥማ፣ እስክስታውን ታቀልጠው ጀመር። የሩብያ ቤት፣ ባልታሰበ አገጣሚ ተሟሙቆ፣ ጨዋታው እንደደራ፣ መንፈቀ ሌሊት ተገባዶ ኖሯል። እስክስታቸው አድክሟቸው፣ ከመደቡ ላይ ዐረፍ እንዳሉ፣ ቁጭ ብሎ በጥሞና ይመለከታቸው የነበረው፣ የሩብያ ባል፣

“ኧረ ከውጭ ዑዑታ የሰማሁ መሰሎኛል!” አላቸው።

“ የምን ዑዑታ ይሆን ብለው!” አራቱም ተያይዘው ወደ ውጭ ፣ ዑዑታውን ለማዳመጥ ይወጣሉ። ለካስ ከማዶአቸው ባሻገር ላይ ከሚገኝ ቤት ውስጥ ዑዑታ ይቀልጥ ኖሯል።

“ የወንድ ያለህ! ድረሱልኝ! ሊገድለኝ ነው! አድኑኝ! ” የሚል የሴት ድምፅ ከልቅሶ ጋር ይሰማሉ። ሩቅ በመሆኑ ግን፣ ምንም ነገር ማድረግ ስለማይችሉ “ አይ ያቺ ወርቅነሽ ትሆናለች!

" እያሉ ወደቤት ተመልሰው ጨዋታቸውን ቀጠሉ።

" የናንተም አባወራዎች እዚህ ቢመጡኮ፣ እንደወርቅነሽ መሆናችሁ ነው! " አለ የሩብያ ባል እየሣቀ።

" አይ እነሱማ ከቤታቸው አባረውናል! ያውም ደብድበው ነው ያባረሩን! ደግሞ ምን እንሁን ብለው ነው የሚመጡት? " አለች የመጀመሪያዪቱ እንግዳቸው።

" ኧረ አይቃጣቸውም! " አለች ሁለተኛይቱ።

" መምጣትስ አይመጡም፣ እየቀለድሁ ነው። ግን ጥያቄዬን በደንብ አልመለሳችሁልኝም! " ይላል፣ የሩብያ ባል፣ በስብሰባው አማካይነት የሠረፀባቸውን ስሜት ለመገምገም እየተመኘ።

" ስንቱን እንነግርሀለን! በጣም ሰፊ ነው! ሩብያ አላስረዳችህም እንዴ! " አለች ሁለተኛዪቱ እንግዳ።

" እባክሽ እሱ ሰምቶ ሰምቶ አልጠቀመውም! " አለች ሚስት።

" ምን አለፋህ፣ እንደነገሩን ከሆነ ከመሐላችን ውስጥ በቅርብ ጊዜ፣ የሴት ፓትርያርክ፣ የሴት ጀኔራል፣ የሴት ሚኒስቴር፣ የሴት ክፍለ ግዛት አስተዳዳሪ ፣..... ባጠቃላይ በሁሉም መስክ የመሠማራት ዕድል ሊኖረን ይችላል። ለሴቶች ተነፍጎ የኖረውን ቤተ-መቅደስ ሳይቀር፣ በቅርብ ጊዜ ገብተን እንቀድስበታለን። ብዙ ሺህ ሠራዊት ለያዘ የሁለትና ሦስት ባታልዮን ጦር፣ ማርሻልና ጀኔራል የምንሆንበት ጊዜ ሩቅ አይደለም። እነዚህ ምሳሌዎች ይሁኑህ እንጅ፣ ምን አለፋህ፣ በጠቅላላው፣ ወንዶች ከደረሱበት የሥልጣን መሠላል ጫፍ፣ እኛም ሴቶቹ የመውጣትና የመድረስ መብት እንዳለን፣ ባንድ ቀን ትምህርታቸው ብቻ አስረድተው አሣምነውናል " አለች፣ ፎለፈሊቱ ተቀዳሚ እንግዳ።

" እኔን ይበልጥ ደስ ያለኝ " አለች ሁለተኛይቱ እንግዳ " እኔን ያስደሰተኝ፣ ማንኛዪቱም ሴት፣ የፈለገችውን ወንድ መርጣ ማግባት ትችላለች ያሉት ነው። የሴቶችም የፍች መብት በሕግ የተጠበቀ መሆኑንም ነግረውናል። አጅሬን ነገ ጠዋት ጤና ይስጥልኛ ነዋ! " አለች፣ በምሽቱ ዱላ የተደበደበችበት ሠምበሯ፣ እንደ መቀሎል ብሎ ሲጠዘጥዛት እየተሰማት። ሁለቱም የሩብያ የምሽት እንግዶች ለጥቂት ጊዜ ቢሆንም ከተማ ቀመሶች ናቸው።

" የነገራችሁ ሁሉ በሙሉ ትክክል ነው። ሰሐ አይወጣለትም። ለወንዶች የሆነው ሁሉ ፣ለሴቶችም የማይደርስበት ምንም ምክንያት የለም። እንዴውም! ሴቶችኮ የወንዶች እናቶች ናቸው! ማበላለጡ አያመችም እንጅ፣ ወንዶችም የሴቶች አባቶች ናቸውና-ለወንዶች ዘንቦ ያጐረፈው፣ ለሴቶችም ቢያርከፈክፍ አይበዛባቸውም። ግና አያሌ ትውልዶች ለዘመናት ቆይታ፣ ባሕል በሚሉ መጫሚያቸው ረግጠው ያተሙትን አስተሳሰብ ባዲስ መልክ ለማደስ ጊዜና ዘዴ ሳይጠይቅ የሚቀር አይመስለኝም። አንዱ ዘዴ ትምህርት ማሰራጨት ነው፣ በተለይም ለኛ ለገጠሬዎቹ! የጐለመስነውንና ያረጀነውን ሰዎች ማደስ እንኳ ባይችል፣ አዲሱን ታዳጊ ትውልድ፣ ከኋላ ቀር ሐሳቦች ተከላክሎ ማዳን ይቻላል። አሁን እነአለቃ ፍስሐ፣ እንዲያ ወልደው፣ ከብደው፣ ያን ሁሉ ማቲያቸውን አፍሰው፣ ከሚስታቸው ጋር ሲናቆሩ፣ ለሁለቱም የሚጥም ድርጊት አይመስልም። ባጭርም ጊዜ ውስጥ፣ ይህ ትብትብ ችግር በቀላሉ እንዲፈታ፣ ካስፈለገ፣ " የሀገሩን ሠርዶ በሀገሩ በሬ " እንዲሉ፣ ከዚሁ ከቀበሌ የችግሩን ምንነት ሠቅሰቀው በሚያውቁት ገጠሬዎች ቢሞከር ይሻላል እንጅ፣ ስለመስኰብ አካባቢ ገጠሮች ተመሳሳይ ችግር በሚል ዘዴ ለመንፈቅ ዕድሜ ታሽተው በመጡት የሴቶች ሊቃውንት፣ መፍትሔ ማፈላለጉ የሚያዋጣ አይመስለኝም " አለ የሩብያ ባል፤ አራምባና ቆቦ ገብቶ የሚቀባጥረው፣ የሱ

ሚስት በየትኛው ነጥብ ላይ ተነክ ታ ፤ እንዲያ በአንድ ቀን ውስጥ ሻጉራ የሆነችበትን መነሾ፤ ፈልፍሎ ለማግኘት እየሞከረ ነው።

" ግደላችሁም፤ እነዚህ ሰዎች፤ ሌላም ተልእኮ ይኖራቸው ይሆናል! " አለች ሩብያ ድንገት ሌላ የውስጧ ሐሳብ ብልጭ ብሎባት።

" ኧረ እባክሽን ተይ! እኛን ነፃ ለማውጣት ካልሆነ በስተቀር ሌላ የተለየ ዐላማም ሆነ ግብ ያላቸው አይመስለኝም አለች " ያቺ ተቀዳሚቱ እንግዳቸው።

" አቀራረባቸው ያስጠረጥራል!" አለ የሩብያ ባል፤ አስተ ያየት እንዲሰጡት በር እየከፈተና ሐሳባቸውን እንዲሠነዝሩ እየጋበዘ።

" ሌላ ምን ተግባር ይኖራቸዋል ብላችሁ ታስባላችሁ? " አለች ሁለተኛዪቱ እንግዳ።

" ምናልባት፤ በአንደኛ ደረጃ የምንመኛቸውን ፍላጎቶች ለሚሟላት፤ መንግሥት፤ ዐቅምም ሆነ ፈቃደኛነት ስላነሰው፤ እኛ ንና አንድነታችንን፤ በሁለተኛ ደረጃ ፍላጎታችን ላይ ብቻ ትኩረት በማሳረፍ፤ ሊበታትነን ፈልጐ እንደሆነስ ማን ያውቃል? የሴቶች መብት እያለ የዘረጋቸው አውታሮች፤ በቀጥታ በየቤቱ ገብተው የት ዳርን ምሰሦ ለመንቃቀር፤ እየተተበተቡ ናቸው፤ ይኸው እናንተ ዛሬ በኛ ቤት ያለውዴታችሁ ማደራችሁ፤ ያንድ ቀን፤ አንድ ምል ክት ነው። " አለች ሩብያ፤ ከባሏ የተማረችው ይመስላል።

" በአንደኛ ደረጃ የምንመኛቸው ፍላጐቶች የምትዪው፤ እነየትኞቹን ነው? " አለች ያቺ የመጀመሪያዪቱ እንግዳ።

" እዚህ ላይ ሩብያን እኔም እረዳታለሁ። መንግሥት በተቀ ዳሚ በተለይ ለኛ ለገጠሬዎቹ ሊያደርግልን የሚገባውና፤ እኛም ለብዙ ጊዜ ስንመኘው የኖርነው፤ የተሻለ መጠለያ ቤት፤ የተሻለ





ልብስ፤ የተሻለ ምግብ የምንላቸውን ነው። እነዚህን ሊያስገኙ የሚ ችሉ ዘዴዎች ቁጥራቸው ቢበዛም፤ ዐይነተኞቹ ግን ገንዘብና እው ቀት ናቸው። መንግሥት በሰጠን መሬት፤ ሌላ እጅ ባይገባበት፤ ከሚያደርግልን ተጨማሪ እርዳታ ጋር ( መነሻ ሀብት ) ራሳችን ሠርተን ገንዘብ ማግኘት እንችላለን። ካፈር ጋር ለመታገል ደግሞ፤ ጤነኛ ዐካል እንዲኖረን ያስፈልገናልና፤ ሐኪም ቤትና ክሊኒክ ቢያቆምልን አስፈላጊያችን ነው። ከዘመኑ ሥልጣኔ ለመቅሰም ሆነ ጥንታዊ አስተሳሰባችንን ለመለወጥ ደግሞ ዕውቀት ያስፈልገናል። የዕውቀትም ምንጭ ትምህርት ቤትና፤ በተግባር ላይ የምንቀ ስመው የየቀኑ ልምድ ነው። ስለሆነም እኛ ገጠሮቹ ለአከባቢያችን ጠቃሚ የሆነና ሁለ-ገብ የሆነ ትምህርት ቤት ቢቋቋምልን፤ ሌላው የመጠለያችን፤ የልብሳችንና የምግባችን ማሻሻያ ዘዴ ነው! ታዲያ! እነዚህ መቼ አሉን? ይህ እንኳ የማይሆንለት ቢሆን፣ እግር አትጠቡ ከማለት ይልቅ ሴቶች ከተሸጐጡበት ቤት ውስጥ ወደ አደባባይ የሚወጡበትን ስር ነቀል ለውጥ ለማስገኘት የሚያስችሉ ፣ ፕሮግ ራሞች ደረጃ በደረጃ ባዘጋጁ ነበር.... " አለ፤ ከበስተፊቱ ያለውን እሳት እየቆሠቆሠ ።

" ለውጥ አለ ይሉናል ሰማን እንጅ አላየን፤
ባላገር እኛ ግን እንዳለነው አለን፤
ሙቀጫና ወፍጮ፤ ቁናና እንሥራ፤ እያላገጡብን!"...

እያለች ሩብያ ታንጐራጉር ጀመር፤ የባሏን ሐሳብ በመደገፍ።

" ምነዋ ባሎችን ተውሽብን " አለች ሁለተኛዪቱ ሞኛሞኝ ብጤ እንግዳዪቱ። ሩብያ ይህንን ስትሰማ፤ ከመቀመጫዋ ተነስታ፤ ባሏ አንገት ላይ ተጠመጠመችና፤ " የኔ ባል ወተት ነው " እያ ለች ያ እንደሎሚ መጠጣዋን፤ ሁለት ጓደኞቿ እያዩአት ታስነካው ጀመር። ይህን ትርዒት በማየትና በማሳየት ላይ እንዳሉ፤ ከቤቱ

ጣራ ሥር ባለ ቆጥ ላይ የሠፈሩ የሩብያ አራት አውራ ዶሮዎች ደግመው ደጋግመው “ ኩኩሉ! ኩኩሉ! ” እያሉ የሰሚዎ ቻቸውን ጆሮዎች እስኪያደነቍሩ ድረስ ጮኹ።

“ ዛሬ ወፍጮውም መቅረቱ ነው! ጨዋታችንን ይዘን ስን ደልቅ፣ ለካስ ሌሊቱ ሊነጋ ተቃርቦ ኖሯል! ” አለች ሩብያ። ባሏም ከመቀመጫው ተነስቶ ከቤታቸው ውስጥ በስተቀኝ በኩል ካለው ሰፊ የመኝታ ደረቅ መደብ ላይ፣ ድርቆሽ ሣር ይጐዘጉዝ ጀመር።


“ እኛ ቤት ይኸውላችሁ፣ የንጨት አልጋ እንኳ የለንም አለ! ” እንግዶቹን ይቅርታ እየጠየቀ።

“ የሁላችንም ያው መደብ ነው ” አለች ሁለተኛዪቱ እን ግዳ። በየቅል የያዙትን ጠላቸውን ሁሉም ጨላለጡና ኬሻ ብቻ በለበሰ የመደብና የድርቆሽ መኝታቸው ላይ ክልትው አሉ።

በማግስቱ ሁለቱ እንግዶቿ ወደ ስብሰባው ሲያመሩ፣ ሩብያ ሌሊት ያለፈበትን ወፍጮዋን ተያያዘችው። በቀበሌያቸውም ስብሰ ባው ባስከተለው ጦስ፣ ብዙ ሰዎች ተጋደሉ፣ ብዙ ሰዎች ተፋቱ፣ ብዙ ሰዎች ታሠሩ። በየት አምልጠው እንደሔዱ አይታወቅም እንጅ፣ እነዚያ የመጀመሪያውን የስብሰባ ዱብ ዕዳ ገፈት የቀመሱ ሁለት የሩብያ እንግዶች፣ ጂቡቲ ገብተው ” ሴተኛ ኣዳሪ ” ከሆኑ መንፈቅ አልፏቸዋል። ሩብያና ባሏም፣ “ ስብሰባውን ንቆ ባለመ ካፈልና፣ የሴቶችን እኩልነት መብት በማርከስ ” በተሰኙ ሁለት የወ ንጀል ዐይነቶች ተከሠው፣ ጉዳያቸው ፍርድ ቤት ሳይቀርብ፣ ከሚኖ ሩበት ቀበሌያቸው ወደ አውራጃው ዋና እሥር ቤት ተወስደው፣ ያለፍርድ ከታሠሩ፣ ይኸው ሁለት መስቀሎችን ተኩሰዋል።



# “ ዘሲባኖስ ”



መፈጠሬ ብቻ ፣ አርጎኝ ወንጀለኛ፣
ስማቅቅ ኖሬአለሁ ፣ ሆኘለት እስረኛ!

(የጠፍ. ቁ.7)